# ተስፋ አድርግ

## 1ኛ ጴጥሮስ

ጽሑፍ፡ ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

ትርጉም፡ መሐሪ ታደሠ

እርማት፡ ወርቁ ኤጄሬ እና ዮዲት ደገፋ

BIBLE BASED BOOKS

SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

Copyright © 2001 by SIM, Addis Ababa.
Originally published in English under the title of BE HOPEFUL.
Copyright © 1982 by SP Publications, Inc. ChariotVictor Publishing, 4050 Lee Vance View, Colorado Springs, Colorado 80918 U.S.A. All rights reserved.

አሳታሚ፡ የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል
Publisher: SIM Publications Department

ስልክ / Tel: 49 32 52 / 51 29 73/71 11 73
የፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 127

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa - ETHIOPIA

# ማውጫ

መግቢያ ........................................ ገጽ

1. ክርስቶስ ባለበት ሁሉ ተስፋ አለ።
   1ኛ ጴጥሮስ 1፡1፥ 5፡12-14 ........................................ 1
2. የክብር መንገድ !
   1ኛ ጴጥሮስ 1፡2-12 ........................................ 10
3. በቆሻሻ ዓለም ውስጥ በንጽሕና መኖር
   1ኛ ጴጥሮስ 1፡13-21 ........................................ 21
4. የክርስቲያኖች አንድነት
   1ኛ ጴጥሮስ 1፡22-2፡10 ........................................ 31
5. የሚያይህ አለ !
   1ኛ ጴጥሮስ 2፡11-25 ........................................ 40
6. ጋብቻ ወይስ ፍቾ!
   1ኛ ጴጥሮስ 3፡1-7 ........................................ 49
7. ለተሻለው መዘጋጀት!
   1ኛ ጴጥሮስ 3፡8-17 ........................................ 58
8. ከኖኅ እንማር
   1ኛ ጴጥሮስ 3፡18-22 ........................................ 67
9. በቀረው ዘመናችን
   1ኛ ጴጥሮስ 4፡ 1-11 ........................................ 75
10. የማንጠረያው እቶን እውነታዎች
   1ኛ ጴጥሮስ 4፡12-19 ........................................ 85
11. መልካም እረኛ መሆን እንዴት ይቻላል?
   1ኛ ጴጥሮስ 5፡1-4 ........................................ 93
12. ከጸጋ ወደ ክብር
   1ኛ ጴጥሮስ 5፡1-11 ........................................ 101

የጥናት ጥያቄዎች ........................................ 109

# መግቢያ

በመከራና በስደት ለምታልፉ፥ 1ኛ ጴጥሮስ ለእናንተ የሚናገርው አለውና «ተስፋ አድርጉ» ።

ጴጥሮስ ይህንን መልእክት የጻፈላቸው ሰዎች በልዩ ልዩ ፈተና ውስጥ የሚያልፉ ነበሩ። ሐዋርያው ፈተና አይቀሬ መሆኑን ስለተገነዘበ፥ አማኞችን ለዚሁ ሊያዘጋጃቸው ፈለገ። ሕይወት በእኛ ውስጥ የምትፈጽመው በእኛ ውስጥ በምታገኘው ነገር ላይ የተመሠረተ ነው።

በአብዛኛው የምዕራቡ ዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች የምቾትን ኑሮ እያጣጣሙት ሲሆን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ግን በብረት በታጠሩ የወኅኒ ቤቶች ስለ እምነታቸው ዋጋ ከፍለዋል። አሁን ግን ለክርስቶስ ያለንን አቋም የምንገልጽበት ጊዜ መድረሱን የሚያመለክቱ ነገሮች እየታዩ ነው። የተመቻቸ ኑሮ እየኖረ ያለው ክርስቲያን፥ «የሚያመቻምቸው» ብቻ ነው። ይህ ምቾቱም ዋጋ ያስከፍለዋል።

ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኛ ያለው መልእክት ተስፋ አላችሁ! የሚል ነው። «መከራ ወደ ክብር ይመራል። የምትጓዝበት መንገድ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ፥ እንድታከብሩኝ የሚያስፈልጋችሁን ጸጋ ሁሉ እሰጣችኋለሁ!»

የወደፊቱ ዘመን እንደ እግዚአብሔር ተስፋ ብሩኅ ነውና ተስፋ አድርጉ!

ዋረን ዌርዝቢ

# 1.

# ክርስቶስ ባለበት ሁሉ ተስፋ አለ

(1ኛ ጴጥሮስ 1፡1፥ 5፡12–14)

«ሕይወት ባለበት ሁሉ ተስፋ አለ!»

ይህ የድሮው የሮማውያን አባባል እንደ ሌሎች አባባሎች ዛሬም ይጠቀሳል። እውነትነት ቢኖረውም በእርግጠኝነት ለመቀበል ግን ዋስትና የለውም። ተስፋን የሚሰጠን ሕይወታችን ሳይሆን፥ እምነታችን ነው። ክርስቲያን «ሕያው ተስፋ» (1ኛ ጴጥ. 1፡3) አለው፤ ምክንያቱም እምነትና ተስፋው በእግዚአብሔር ላይ ነው (1፡21)። ይህ «ሕያው ተስፋ» ደግሞ የጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክቱ ዋና ጭብጥ ነው። ለአማኞች በሙሉ «ተስፋ ይኑራችሁ!» ይላል።

ይህንን ደስ የሚያሰኝ መልእክት ከማጥናታችን በፊት መልእክቱን ማን እንደ ጻፈውና ለእነማን እንደ ላከው እንዲሁም ለመጻፍ ያነሣሣው ምክንያት ምን እንደነበረ እንወቅ።

## 1. ጸሐፊው

ጸሐፊው ራሱን «የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ» (1፡1) በማለት ያስተዋውቃል። በሐዋርያት ሥራ 4፡13 ላይ ዮሐንስና ጴጥሮስ «መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ» ስለተባሉ እንዴት አንድ ዓሣ አጥማጅ ይህንን መልእክት ሊጽፍ ይችላል? በማለት የሚጠራጠሩ አሉ። ነገር ግን ይህ ምንባብ እነ ጴጥሮስ ትምህርት ቤት ገብተው የሠለጠኑ ፕሮፌሽናል የሃይማኖት መሪዎች መሆናቸውን ባይገልጽም፥ ጴጥሮስ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ለሦስት ዓመታት ያህል ያገኘውን ሥልጠና እና በሕይወቱ ይሠራ የነበረውን የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ መዘንጋት የለብንም። ጴጥሮስ በ1ኛ ቆሮ. 1፡26–31 ለተገለጸው እውነት ትክክለኛ ተምሳሌት ነው።

የመጀመሪያ ስሙ ስምዖን ሲሆን፥ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስ ብሎ ጠራው፥ እርሱም «ዐለት» ማለት ነው (ዮሐንስ 1፡35–42)። ጴጥሮስ የሚለው ስም በአረማይክ ቋንቋ «ኬፋ» ማለት ሲሆን፥ ጴጥሮስ ሦስት ስሞች ነበሩት። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለአምሳ ጊዜ ያህል «ስምዖን» ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ አንዳንድ ጊዜም «ስምዖን ጴጥሮስ» ተብሎ ተጠቅሷል። ምናልባትም እነዚህ ሁለት ስሞች፥ የክርስቲያኖችን ሁለት ባሕርይ ያሳያሉ፥ አንደኛው ውድቀትን የተላበሰው አሮጌው ባሕርይ (ስምዖን) ሲሆን፥ ሁለተኛው ድልን የሚያጎናጽፈው አዲሱ ባሕርይ

ደግሞ «ጴጥሮስ» ነው። ስምዖን በመሆኑ እንደ ሸክላ ተሰባሪ ሰው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከውስጡ ዐለትን አወጣ።

ጴጥሮስና ጳውሎስ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ግንባር ቀደም ሐዋርያት ነበሩ። ጳውሎስ አሕዛብን ጴጥሮስ ደግሞ አይሁድን እንዲያገለግሉ ተሹመው ነበር (ገላ. 2:10)። ጌታ፥ ጴጥሮስ ወንድሞችን እንዲያበረታታና (ሉቃ. 22:32) መንጋውን እንዲጠብቅ (ዮሐ. 21:15-17፤ 1ኛ ጴጥሮስ 5:1-4) ስላዘዘው ይህ መልእክት የዚህ ዓይነቱ አገልግሎት አንደኛው አካል ነው። ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹ እንደ ጻፈው፥ ይህ መልእክት የማበረታቻና የራሱን ምስክርነት ያካተተ ነው (1ኛ ጴጥሮስ 5:12)። የመጀመሪያ ዓመት የኮሌጅ ተማሪዎች በየክፍለ ትምህርት ዘመኑ የሚያዘጋጁቸው ጽሑፎች የሚጻፉት በመጻሕፍት ላይ ተመረኩዘው ሲሆን፥ ይህ መልእክት ግን የተገኘውና የጎለበተው ለእግዚአብሔር ክብር ከሚኖር ሕይወት ነው። በጴጥሮስ ሕይወት ያለፉት ብዙ ነገሮች በዚህ መልእክት ውስጥ እንደ ድርና ማግ ተሳስረዋል።

ይህ መልእክት ከሲላስም (ስልዋኖስ፥ 5:12) ጋር የተያያዘ ነው። እርሱ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ከነበሩት «ከዋነኞቹ» አንዱ ሲሆን (የሐዋ. ሥራ 15:22)፥ ነቢይም ነበረ (15:32)። ይህም እርሱ የእግዚአብሔርን መልእክት ለምእመናን በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ መናገሩን ያመለክታል (1ኛ ቆሮ. 14ን ይመልከቱ)። ሐዋርያትና ነቢያት በጋራ ሆነው የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ከጣሉ በኋላ (ኤፌ. 2:20)፥ ሥራቸውን ፈጽመው አልፈዋል። በአዲስ ኪዳን ወቅት የነበሩት ዓይነት ሐዋርያትና ነቢያት በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን የሉም።

ሲላስ በአገልግሎት ከጴጥሮስ ጋር መጠቀሱ የሚያስደስት ነገር ነው። ምክንያቱም በርናባስን ተክቶ ከጳውሎስ ጋር ሄዶአል (የሐዋ. ሥራ 15:36-41)። ጴጥሮስ ዮሐንስ የተባለውን ማርቆስንም ጠቅሶታል። በማርቆስ ምክንያት ጳውሎስና በርናባስ ተለያይተው ነበር (1ኛ ጴጥሮስ 5:13)። ጴጥሮስ ማርቆስን ወደ ጌታ መርቶት ስለነበር («ልጄ ማርቆስ»)፥ ለማርቆስ ግድ ይለው ነበር። ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም በነበረው የእነ ማርቆስ ቤት ይሰባሰቡ እንደነበር አይጠረጠርም (የሐዋ. ሥራ 12:12)። በመጨረሻም ጳውሎስ ማርቆስን ይቅር ብሎ ጠቃሚ ረዳቱ አድርጎ ተቀብሎታል (2ኛ ጢሞ. 4:11)።

ጴጥሮስ እንዳመለከተው ይህን መልእክት የጻፈው፥ የአማኞች ጉባኤ ካለበት ከባቢሎን ነበረ (1ኛ ጴጥሮስ 5:13)። የቤተ ክርስቲያን ታሪክም ሆነ ትውፊት ጴጥሮስ በዚያ ወቅት ብዙ አይሁድ በነበሩባት በጥንቷ ባቢሎን ሄዶ ስለማገልገሉ ፍንጭ አይሰጡም። በግብፅ ምድር

የምትገኝ «ባቢሎን» የምትባል ከተማ ብትኖርም፥ ጴጥሮስ ወደዚህች ከተማ ስለመሄዱ መረጃ የለም። ምናልባትም ጴጥሮስ በሮም ስላገለገለና ፍንጭም ስላለን እንዲሁም በሮም እንደ ተሠዋ ስለሚናገር «ባቢሎን» የተባለችው ሮም ትሆን ይሆናል። በዮሐንስ ራእይ 17፡ 5 እና 18፡10 ላይ ሮም «ባቢሎን» ተብላ ተጠርታለች። በስደት ይኖሩ ለነበሩ ለዚያ ዘመን አማኞች በምሥጢር ቃላት መጻጻፍ የተለመደ ነበር።

ይህንን በማለታችን ጴጥሮስ ካደረገው በላይ አንናገርም። ጴጥሮስ በሮም ያለችውን ቤተ ክርስቲያን አልመሠረተም። የመጀመሪያውም መጋቢ ሆኖ አላገለገለም። ሌላ ሐዋርያ ባገለገለበት ቦታ አለማገልገል የጳውሎስ መመሪያ ስለነበር (ሮሜ 15፡20)፥ ጴጥሮስ በመጀመሪያ ሮም ደርሶ ቢሆን ኖሮ፥ ጳውሎስ በሮም አያገለግልም ነበር። ጴጥሮስ ወደ ሮም የተጓዘው ምናልባት ጳውሎስ በ62 ዓ.ም. አካባቢ ከእስር እንደ ተፈታ ይሆናል። 1ኛ ጴጥሮስ የተጻፈው በ63 ዓ.ም አካባቢ ነው። ጳውሎስ በ64 ዓ.ም የተሠዋ ሲሆን፥ በዚያው ዓመት ወይም ደግሞ ከዓመት በኋላ ጴጥሮስ ሕይወቱን ለክርስቶስ ሠውቷል።

## 2. የመልእክቱ ተቀባዮች

ጴጥሮስ «መጻተኞች» (1ኛ ጴጥሮስ 1፡1) በማለት የጠራቸው ሲሆን፥ ትርጉሙም በእንግድነት ነዋሪዎች ማለት ነው። በ1ኛ ጴጥሮስ 2፡11 ላይ «እንግዶችና መጻተኞች» ተብለው ተጠርተዋል። እነዚህ ሰዎች በክርስቶስ አምነው የመንግሥተ ሰማይ ዜጎች በመሆናቸው፥ በምድር ላይ ለዘላለም ነዋሪዎች አልነበሩም (ፊልጵ. 3፡20)። እንደ አብርሃም የእምነት ዓይናቸውን በእግዚአብሔር ከተማ ላይ ተከሉ (ዕብ. 11፡8–16)። በዓለም ነበሩ ከዓለም ግን አልነበሩም (ዮሐ. 17፡16)።

በዚህ ዓለም ክርስቲያኖች «እንግዶች» ስለሆኑ፥ በዓለም እይታ እንደ «መጻተኛ» ይቆጠራሉ (1ኛ ጴጥሮስ 4፡4)። ክርስቲያኖች ከዓለም የተለዩ እሴቶች አሏቸው። ይህም በመመስከርና በመንፈሳዊ ውጊያ እንዲሳተፉ ዕድል ይሰጣቸዋል። መልእክቱ የተጻፈላቸው አማኞች ከዓለም በተለየው አኗኗራቸው ምክንያት መከራ ሲቀበሉ እናያለን።

እነዚህ አማኞች «የተበተኑ» ወይም «መጻተኞች» ነበሩ። «ለተበተኑት» ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል «ዲያስፖራ» የሚለው ሲሆን ከፓለስታይን ውጭ የሚኖሩትን አይሁድ ያመለክታል። ይህ ቃል በዮሐንስ 7፡35 እና ያዕቆብ 1፡1 ላይም የተጠቀሰ ሲሆን ጴጥሮስ ይህንን ቃል በመጠቀሙ መልእክቱን የጻፈው ለአይሁድ ክርስቲያኖች ብቻ እንደነበረ አያመለክትም። ምክንያቱም የመልእክቱ አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮች ከአንባቢዎቹ

መካከል አንዳንዶቹ ከአረማዊነት ወደ ክርስትና የተለወጡ መኖራቸውንም ይጠቁማል (1፡14፥18፥ 2፡9-10፤ 4፡1-4)። የመልእክቱ ተቀባዮች በአብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ አይሁድና የአረማውያን ቅይጥ መሆናቸው አያጠራጥርም። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ በርከት ያሉ የብሉይ ኪዳን ማጠቀሻዎችን እንመለከታለን።

እነዚህ ክርስቲያኖች ለአምስት የሮማ ግዛተ ዐፄ ክልል በሰሜናዊው የእስያ አካባቢ ማለትም በአሁኗ ቱርክ ተበታትነው ይኖሩ ነበር። መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ በቢታንያ እንዳያገለግል ስለከለከለው (የሐዋ. ሥራ 16፡17)፥ ይህንን ሥራ ጀመረ። በዕለተ ጴንጤቆስጤ ከጳንጦስና ከቀጰዶቅያ የመጡ አይሁድ ስለነበሩ፥ ምናልባት ወንጌሉን ወደ አጎራባች አውራጃዎች ሳያደርሱ አልቀሩም (የሐዋ. ሥራ 2፡9)። በጴጥሮስ አገልግሎት ሥር የነበሩት አይሁድ ክርስቲያኖች፥ ወደ እነዚህ ከተሞች መጓዛቸው አይቀሬ ነው። በዚያ ዘመን ሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ የሚዘዋወሩ ሲሆን ትጉሕ ክርስቲያኖችም ይመሰክሩ ነበር (8፡4)።

ስለ «ተበተኑት መጻተኞች» ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር በመከራና በስደት ጊዜ ውስጥ እያለፉ መሆናቸውን ነው። ጴጥሮስ በዚህ መልእክት ውስጥ ቢያንስ አሥራ አምስት ጊዜ «መከራ» የሚለውን ቃል የተጠቀመ ሲሆን፥ ስምንት የተለያዩ የግሪክ ቃላትን ደግሞ መከራን በተመለከተ ተጠቅሟል። ከእነዚህ ክርስቲያኖች አንዳንዶቹ የተሠቃዩት እግዚአብሔርን የሚያስደስት መልካምና ትክክለኛ ሕይወት ስለኖሩ ነው (1ኛ ጴጥሮስ 2፡19-23፤ 3፡14-18፤ 4፡1-4፤ 15-19)። ሌሎች ደግሞ የተሠቃዩት፥ የተነቀፉትና በማያምኑ ሰዎች የተሰደቡት ስለ ክርስቶስ ስም ብለው ነበር (4፡14፤ 3፡9-10)። ጴጥሮስ የጻፈላቸው ለሚያሠቃዩዋቸው መልካም ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ ነው። እንዲሁም የሚቀበሉት መከራ ወደ ክብር እንደሚያደርሳቸው በማስታወስ ሊያበረታታቸው ፈልጎ ነው (1፡6-7፤ 4፡13-14፤ 5፡10)።

ሆኖም ጴጥሮስ ሌላም ዓላማ ነበረው። «እንደ እሳት የሚያነጥረው ፈተና» ከሮማ መንግሥት እንደሚነሣ አውቆ ነበር (4፡12)። ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም በተጀመረች ጊዜ፥ ከአይሁድ እምነቶች እንደ አንዱ «ቤተ እምነት» ተቆጥራ ነበር። የመጀመሪያዎቹ አማኞች አይሁዶች ሲሆኑ፥ የሚገናኙትም በቤተ መቅደስ ነበረ። የአይሁድ እምነት ተቀባይነት ስለነበረው፥ የሮማ መንግሥት በክርስቲያኖች ላይ ይሄ ነው የሚባል ርምጃ አልወሰደም። ነገር ግን ክርስትና ከአይሁድ እምነቶች አንዱ ክፍል ያለ መሆኑን ሲያውቅ የሮማ መንግሥት እርምጃ መውሰድ ጀመረ።

ይህንን እንደ «እሳት የሚያነጥር ፈተና» ያፋጠኑ ብዙ ነገሮች ተከናውነው ነበር። ጳውሎስ በሮማ ፍርድ ቤት ስለ ክርስትና እምነት ለመሟገት ቀርቦ ነበር (ፊልጵ. 1፡12-24)። ለትንሽ ጊዜ ተፈትቶ እንደገና ታሥሯል፤ የኋላ ኋላም ሙግቱ ሳይሳካለት ቀርቶ መሥዋዕት ሆኗል (2ኛ ጢሞ. 4፡16-18)። በሁለተኛ ደረጃ እንደ ዕብድ በሚቆጠረው ንጉሥ ኔሮ በሮም ተነሥቶ የነበረውን የእሳት ቃጠሎ በክርስቲያኖች ላይ በማሳበብ እንደ ማምለጫ መንገድ ተጠቀመባቸው። ምናልባትም ጴጥሮስ በዚህ ወቅት በሮም ስለነበር ጳውሎስን በገደለው በኔሮ ሳይገደል አይቀርም። ኔሮ ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረው በሚኖርበት አካባቢ ቢሆንም፥ ቀስ በቀስ እየተስፋፋ ሳይሄድ አልቀረም። በዚያም ሆነ በዚህ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያናትን ለማዘጋጀት ፈለገ።

በዚያ ግዛት የነበሩ ክርስቲያናት በሙሉ በአንድ ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ በስደት ውስጥ ያልፉ ነበር የሚል አስተሳሰብ ሊኖረን አይገባም። ስደትና ተቃውሞ በየስፍራው ቢኖርም፥ ይዘቱ ከቦታ ቦታ ይለያይ ነበር (1ኛ ጴጥሮስ 5፡9)። ኔሮ ክርስቲያኖችን በግልጽ ማሳደዱን በመጀመሩ፥ ከእርሱ በኋላ የተነሡትም ነገሥታት የእርሱን አርአያ ተከተሉ። የጴጥሮስ መልእክት በትራጃን (98-117 ዓ.ዓ.)፥ በሃድርያን (117-138 ዓ.ዓ.) እና በዳዮክሊስያን (284-305 ዓ.ዓ.)፥ የግዛት ዘመን መከራን ይቀበሉ ለነበሩት ክርስቲያኖች ታላቅ ጠቀሜታ ነበረው። በአሁኑ ዘመን የሚኖሩ ክርስቲያኖች የጴጥሮስን መልእክት በሚገባ የሚረዱት እምነት ፈታኝ መከራና በራሳቸው ሕይወት ሲደርስ ነው። ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን በመከራ ዘመን እንደማታልፍ ባምንም የመጨረሻው ዘመን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ብዙ መከራና ስደት እንደሚያመጣ አምናለሁ።

ምናልባትም ይህንን መልእክት እንደ ጸሐፊ በእጁ የጻፈውና በየስፍራው ለነበሩ ክርስቲያኖች ያደረሰው ሲላስ ሊሆን ይችላል።

## 3. መልእክቱ

አንደኛው የጴጥሮስ መልእክት ማበረታቻ ነው (5፡12)። በመልእክቱ ውስጥ «መከራ» መሪ አሳብ ነው፤ እንደዚሁም ደግሞ «ክብር» መሪ አሳብ ነው (1፡7-8፥11፥21፤2፡12፤ 4፡11-16፤ 5፡1፥4፥10-11)። ጴጥሮስ በመከራ ለሚያልፉት ቅዱሳን ከሰጣቸው ማበረታቻዎች አንዱ፥ አንድ ቀን መከራቸው ወደ ክብር የሚለወጥ መሆኑን ማረጋገጥ ነው (1፡6-7፤4፡13-14፤5፡10)። ይህ የሚሆነው ደግሞ አዳኛችን ስለ እኛ መከራን ተቀብሎ፥ ወደ ክብሩ ስለገባ ነው (1፡11፤ 5፡1)። የክርስቶስ መከራ በዚህ መልእክት ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል (1፡11፤ 3፡18፤ 4፡1፥ 13፤ 5፡1)።

ዮሐንስ *የፍቅር ሐዋርያ*፥ ጳውሎስ ደግሞ *የእምነት ሐዋርያ* እንደሆኑ ሁሉ ጴጥሮስ ደግሞ *የተስፋ ሐዋርያ* ነው። ሕያው በሆነው በክርስቶስ ስለምናምን አማኞች «ሕያው ተስፋ» አለን (1:3)። ይህ ተስፋ ክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም እስኪገለጥ ድረስ ሕሊናችንን በመቆጣጠር እስከ ፍጻሜው እንድንጠብቅ ያስችለናል (1:13)። በእኛ ስላለ ተስፋ መልስ ለመስጠት የተዘጋጀን መሆን አለብን እንጂ ማፈር የለብንም (3:15)። እንደ ሣራ ክርስቲያን ሚስቶች በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይችላሉ። መከራ ክብርን ስለሚያመጣ፥ ኢየሱስም ተመልሶ ስለሚመጣ ተስፋ አለን።

ነገር ግን መከራ ወዲያውኑ ለእግዚአብሔር ክብርን፥ ለሰዎች ደግሞ በረከትን አያመጣም። የተወሰኑ አማኞች በፈተና ዝለውና ወድቀው ለክርስቶስ ስም ነቀፋን አምጥተዋል። በመከራ ወቅት እግዚአብሔርን ማክበር የምንችለው በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ብቻ ስንደገፍ ነው። ጴጥሮስም በመልእክቱ ለእግዚአብሔር ጸጋ አጽንዖት ሰጥቷል። «እየመከርኳችሁና የምትቆሙባት ጸጋ እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ እንድትሆን እየመሰከርኩላችሁ . . . ጽፌላችኋለሁ» (5:12)።

«ጸጋ» የሚለው ቃል በ 1ኛ ጴጥሮስ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ተጠቅሷል (1:2፥ 10፥ 13፤ 2:19፤ 2:20፤ 3:7፤ 4:10፤ 5:5፥ 10፥12)። ጸጋ ማለት እግዚአብሔር ለማይገባቸው ኃጢአተኞችና ነዳያን ቅዱሳን በቸርነቱ የሚሰጠው ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ ስንታመን መከራንና ፈተናን ታግሠን ወደ ድል እንለውጣቸዋለን። እኛን የሚያድነን ጸጋ ብቻ ነው (ኤፌ. 2:8-10)። የእግዚአብሔር ጸጋ በፈተና ወቅት ብርታትን ይሰጠናል (2ኛ ቆሮ. 12:1-10)። ጸጋ በብዙ ችግሮች ውስጥ አልፈን እግዚአብሔርን እንድናገለግል ያስችለናል (1ኛ ቆሮ. 15:9-10)። በእግዚአብሔር ጸጋ የተጀመረ ነገር ሁሉ፥ ፍጻሜው ክብር ነው [መዝ. (84):11፤ 1ኛ ጴጥ. 5:10]።

የመጀመሪያውን የጴጥሮስ መልእክት ስናጠና የ«መከራ»፥ የ«ጸጋ»ና የ«ክብር» መሪ አሳቦች አንድ ላይ ተዋህደው በፈተናና በስደት ውስጥ ለሚያልፉ አማኞች እንዴት ያለ የሚያጽናና መልእክት እንዳዘሉ እናያለን። እነዚህ መሪ አሳቦች በ 1ኛ ጴጥሮስ 5:10 በጥቅሉ የሰፈሩ ሲሆን፥ በቃል ማጥናቱ ይጠቅመናል።

ታዋቂው አርታኢና ጸሐፊ ኤች. ኤል. ሜንከን በአንድ ወቅት ተስፋን እንዲህ ብሎታል። «የማይቻለው ይለወጣል ብሎ የሚጠብቅ የፍርሃት እምነት ነው»። ነገር ግን ይህ አባባል በአዲስ ኪዳን ለተስፋ ከተሰጠው ትርጉም ጋር ይጻረራል። የክርስትና ተስፋ ከ«ላም አለኝ

በሰማይ» በእጅጉ የበለጠ ነው። ለወደፊቱ ክብርና በረከት አስተማማኝ ዋስትና የሚሰጥ ነው።

የብሉይ ኪዳን አማኝ፥ እግዚአብሔርን «የእስራኤል ተስፋ» (ኤር. 14፡8) ሲል ጠርቶታል። የአዲስ ኪዳን አማኝም ክርስቶስ ኢየሱስ ተስፋው እንደሆነ አረጋግጧል (1ኛ ጢሞ. 1፡1 ና ቆላ. 1፡27)። ያልዳነ ኃጢአተኛ «ተስፋ የለውም» (ኤፌ. 2፡12)። ያለ ክርስቶስም ከሞተ ለዘላለም ተስፋ ቢስ ይሆናል። ጣሊያናዊው ባለቅኔ ዳንቴ «ዲቫይን ኮሜዲ» (መለኮታዊ ቀልድ) በሚለው ጽሑፉ፥ በሙታን ዓለም ላይ «እዚህ የምትገቡ በሙሉ ተስፋችሁን ተዉ!!» የሚል የተቀረጸ ጽሑፍ አስፍሯል።

ይህም አስተማማኝ ተስፋ ለዕለት ኑሮአችን የሚያስፈልገንን ማበረታቻና ኃይል ይሰጠናል እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመጣ እያላዘንን የምንቆይበት ዥዋ ዥዌ ላይ አያስቀምጠንም። በዚህ ፋንታ ጦርነት በበዛበት ሸክም ባጎበጠን ወቅት ወደ መንፈሳዊ ውጊያና ትርፋማ ወደምንሆንበት ሕይወት ያመጣናል። «ተስፋ» ማደንዘዣ አይደለም። ነገር ግን ደማችን ውስጥ የተቀየጠ ኃይል ነው። ልክ እንደ መልኅቅ በክርስቶስ ያለን ተስፋ፥ በሕይወት ማዕበል ውስጥ ያረጋጋናል (ዕብ. 6፡18–19) ነገር ግን ከመልኅቅ በሚጻረር መልኩ ተስፋችን ወደፊት ያራምደናል እንጂ ወደ ኋላ አይጎትተንም።

የጴጥሮስን የአሳብ ባቡር መከተል አያዳግትም። ሁሉም ነገር የሚጀምረው፥ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት በሚፈጸመው ደኅንነት ነው። ክርስቶስ አዳኝ እንደሆነ ካመንን፥ ተስፋ አለን! ተስፋ ካለን ደግሞ በቅድስናና በሰላም እንኳዛለን። ለኅብረተሰባችን፥ ለቤተሰባችንና ለቤተ ክርስቲያን ለመታዘዝ አንቸገርም። ደኅንነትና መታዘዝ መከራን ለመቀበል የምናደርጋቸው ዝግጅቶች ናቸው። ሆኖም ዓይናችንን በክርስቶስ ላይ ካደረግን፥ እናሸንፋለን፤ እግዚአብሔርም መከራን ወደ ክብር ይለውጥልናል።

1ኛ ጴጥሮስን እንደሚከተለው ልንከፋፍለው እንችላለን

1. የእግዚአብሔር ጸጋና ድኅነት 1፡1–2፡10

ሀ. በተስፋ ኑሩ 1፡1–12

ለ. በቅድስና ኑሩ 1፡13–21

ሐ. በሰላም ኑሩ 1፡22–2፡10

2. የእግዚአብሔር ጸጋና መታዘዝ 2፡11–3፡12

ሀ. ለባለሥልጣናት ተገዙ 2፡11–17

ለ. ለጌቶቻችሁ ተገዙ 2፡18–25

ሐ. በቤተሰባችሁ ተገዙ 3፡1–7

መ. በቤተ ክርስቲያን ተገዙ 3፡8–12

## 3. የእግዚአብሔር ጸጋና መከራ 3፡13–5፡11

ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ አድርጉት 3፡13–22

ለ. የክርስቶስ ልብ ይኑራችሁ 4፡1–11

ሐ. የክርስቶስን ስም አክብሩ 4፡12–19

መ. የክርስቶስን ምጽአት ተጠባበቁ 5፡1–6

ሠ. በክርስቶስ ጸጋ ቁሙ 5፡7–11

*ተጨማሪ ማስታወሻዎች፡ 1ኛ ጴጥሮስና የኤፌሶን መልእክት*

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በኤፌሶን መልእክትና በ1ኛ ጴጥሮስ ያሉትን ትይዩ አሳቦች አስተውለዋል። እነዚህም ትይዩ አሳቦች ጴጥሮስና ጳውሎስ የተለያየ መልእክት ሰብከዋል የሚለውን አሳብ ዋጋ ቢስ ያደርገዋል። በእርግጥ ጴጥሮስ ራሱ (በ2ኛ ጴጥሮስ 3፡15–16) መልስ ሰጥቶበታል። ጳውሎስና ጴጥሮስ በተለያየ የአገልግሎት ዘርፍ ቢሰማሩም፥ አንድ ወንጌል ሰብከዋል፥ አንድ ጌታም አክብረዋል። እነዚህን ትይዩ ምንባቦች በግላችሁ ልትመለከቷቸው ትችላላችሁ።

| *ኤፌሶን* | *1ኛ ጴጥሮስ* |
|---|---|
| 1፡3 | 1፡3 |
| 3፡5፥10 | 1፡12 |
| 3፡6፥21 | 4፡11 |
| 3፡8 | 1፡8 |
| 4፡2 | 3፡9 |
| 4፡7፥ 11 | 4፡10 |
| 4፡13፥15 | 2፡2 |

የእግዚአብሔር ቃል ፍጹምና ስሕተት የሌለበት ነው። መንፈስ ቅዱስ እንዲጻፍ ያደረገው ሁሉ እውነት ነው። የሚቃረንም ነገር የለውም። 1ኛ ጴጥሮስን ስታጠኑ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ የተጠቀሱትን ቁጥሮች

በማጣቀስ በዚህ ርእስ ሌሎች ምንባቦች ምን እንደሚሉ ልታዩ ትችላላችሁ።

*1ኛ ጴጥሮስና ወንጌላት*

ጴጥሮስ የክርስቶስን ቃል ጠቅሶ በዚያ ወቅት ስለተፈጸሙት ጉዳዮች በወንጌላት ከተጻፉት እንዲያዛምድ ትጠብቁ ይሆናል። ቀጥለው የተዘረዘሩት ለጥናታችሁ የሚጠቅሙ ናቸው።

| *1ኛ ጴጥሮስ* | *ወንጌላት* |
|---|---|
| 1፡16 | ማቴዎስ 5፡48 |
| 1፡17 | ማቴዎስ 22፡16 |
| 1፡18 | ማርቆስ 10፡45 |
| 1፡22 | ዮሐንስ 15፡12 |
| 2፡19 | ማቴዎስ 5፡39፤ ሉቃስ 6፡32 |
| 3፡9 | ማቴዎስ 5፡38 |
| 3፡14 | ማቴዎስ 5፡10 |
| 4፡11 | ማቴዎስ 5፡16 |
| 4፡13 | ማቴዎስ 5፡10 |
| 4፡18 | ማቴዎስ 24፡22 |
| 5፡3 | ማቴዎስ 20፡25 |
| 5፡5 | ዮሐንስ 13፡1 |
| 5፡7 | ማቴዎስ 6፡25 |
| 5፡8 | ሉቃስ 22፡31 |

# 2

# የክብር መንገድ

(1ኛ ጴጥሮስ 1፡2–12)

በአንድ ነፋሻማ የክረምት ቀን እኔና ባለቤቴ በእንግሊዝ አገር ከዊንድሰር ግንብ አቅራቢያ ስቶክ ፖጅስ መንደር ውስጥ በሚገኝ በዓለም ታዋቂ ወደሆነ የመቃብር ስፍራ ለጉብኝት ሄድን። በዚህ ስፍራ ቶማስ ግሬይ በትምህርት ቤት ወይም በሌላ አጋጣሚ ያነበብነውን ታዋቂውን «በገጠር ቤተ ክርስቲያን የመቃብር ሥፍራ የሚገኘውን የኀዘን መግለጫ» ጽፎአል።

በጥንታዊ መቃብሮች መሃል በጸጥታ ቆመን ሳለን የዚህ ግጥም አካል የሆነው ክፍል ታወሰን፡

> የመልእክተኛው ጉራ የኃይሉ ማሸብረቅ
>
> የሀብት ቋጠሮ የውበት መደምደሚያ
>
> የማይቀረውን ሰዓት ስትጠብቁ
>
> የክብር መንገዶች ወደ መቃብር ይመራሉ።

የሰው ክብር ዘላቂ አይደለም። የእግዚአብሔር ክብር ግን ዘላለማዊ ነው። ይህንንም ክብሩን ለእኛ ሊያካፍለን ፈቅዷል። በመልእክቱ የመጀመሪያ ክፍል፥ ጴጥሮስ ስለ እግዚአብሔር ክብር የተገነዘባቸውን አራት ድንቅ እውነታዎች አካፍሎናል።

## 1. ክርስቲያኖች የተወለዱት ለክብር ነው (1፡2–4)

በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ አማኞች የእግዚአብሔር ክብር ላለበት ሕያው ተስፋ «ዳግመኛ ተወልደዋል»። ነገር ግን «የእግዚአብሔር ክብር» ስንል ምን ማለታችን ይሆን?

የእግዚአብሔር ክብር ማለት የእግዚአብሔር ማንነቱና ድርጊቱ በአንድ ላይ ተጣምረው ነው። «ክብር» ከቅድስናው፥ ከጥበቡና ከምሕረቱ የተለያየ የእግዚአብሔር ባሕርይ አይደለም። የእግዚአብሔር ማንነቱና ድርጊቱ በአጠቃላይ ክብሩ ነው። በጥበብና በኃይል ክቡር ስለሆነ፥ የሚያስበውና የሚያከናውነው ሁሉ የክብሩ ምልክት ነው። ክብሩን በፍጥረት ገልጧል (መዝ. 19)። ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በነበረው ግንኙነትና የጠፉ ኃጢአተኞችን ለማዳን ባለው ልዩ ዕቅድ ተገልጧል።

በመጀመሪያ ስንወለድ የተወለድነው ለክብር አልነበረም (ከኢሳይያስ 40፡6 ጠቅሶ ጴጥሮስ በ1ኛ ጴጥ. 1፡24 እንደ ጻፈው) «ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነው።» ሰው የቱንም ያህል ታላቅ ክብር ቢኖረው፥ ቀስ በቀስ እየደበዘዘ ይጠፋል። የእግዚአብሔር ክብር ግን ዘላለማዊ ነው። ለእግዚአብሔር ክብር የተሠሩ የሰው ሥራዎች እስከ ወዲያኛው ይዘልቃሉ፤ ይሸለማሉም (1ኛ ዮሐንስ 2፡17)። ነገር ግን የስግብግብ ኃጢአተኞች ሥራዎች ሁሉ አንድ ቀን ደግሞ ሳይታወሱ ይጠፋሉ። ኢንሳይክሎፒድያ የምናዘጋጀው ዛሬ ስለተረሱት ቀደም ሲል ግን ዝነኞች ስለነበሩ ሰዎች ለመማር ነው። ጴጥሮስ ስለ ክብር እውነታዎችን በተሻለ ሁኔታ እንድንገነዘብ የሚረዱንን ሁለት መግለጫዎች ሰጥቶናል።

*ሀ. የክርስቲያን ልደት (1፡2–3)*

ይህ ተአምር የሚጀምረው በእግዚአብሔር ነው። የተመረጥነው በእግዚአብሔር ነው (ኤፌ. 1፡3–4)። ይህም የተፈጸመው ጥልቅ በሆነው በዘላለም ምክሩ ሲሆን፥ በእግዚአብሔር ቃል እስካልተነገረን ድረስ አናውቀውም ነበር። በስፍራው ስላልነበርን፥ ይህ ምርጫ የተካሄደው እኛ በሠራነው ሥራ ላይ ተመሥርቶ ወይም እኛ ወደፊት የምንሆነውና የምንፈጽመውን ሥራ እግዚአብሔር አመዛዝኖት የተደረገ አይደለም። የእግዚአብሔር ምርጫ የተመሠረተው ሙሉ በሙሉ በጸጋውና በፍቅሩ ላይ ነው። ለመግለጽ ቢያዳግተንም በዚህ መደሰት ይገባናል (ሮሜ 11፡33–36)።

«የቅድመ–እውቀት» አመለካከት እግዚአብሔር እኛ እንደምናምን አውቆ መረጠን የሚለውን አሳብ አይደግፍም። እንዲህ ቢሆንማ ኖሮ፥ «ክርስቶስን ለመከተል ያስወሰነን ማን ነው?» የሚለውን ጥያቄ በማስነሣት ደኅንነታችንን ከእግዚአብሔር እጅ ያወጣዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ «ቅድመ–እውቀት» የሚለው ቃል ትርጉም «ፍቅርን በአንድ ሰው ወይም በብዙዎች ላይ ማኖር» ሲሆን ይህም በአሞጽ 3፡2 ተጠቅሷል። «እኔ ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን አውቄአችኋለሁ»። እግዚአብሔር የመምረጥ ፍቅሩን በእስራኤል ሕዝብ ላይ አደረገ። «ማወቅ» የሚለውን ቃል የተጠቀሙ ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው –1ኛ ቆሮንቶስ 8፡3፤ ዮሐንስ 10፡14፥27፤ ማቴዎስ 7፡23 ና መዝሙር 1፡6።

ሆኖም የደኅንነት ዕቅድ ከአብ የምርጫ ፍቅር የሚበልጥ ነገር አለው። ኃጢአተኛውን ስለ ኃጢአቱ በመውቀስ በክርስቶስ ወዳለ እምነት የሚያመጣውን የመንፈስ ቅዱስንም ሥራ ያካትታል። ይህንን የበለጠ የሚያብራራልን 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13–14 ነው። ከዚህ

በተጨማሪ የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአታችን ባይሞት ኖሮ፥ ደኅንነት የተባለ ነገር አይኖርም ነበር። እኛም በአብ ተመርጠናል፤ በልጁ ተገዝተናል። በመንፈሱም ተለይተናል። እውነተኛ ደኅንነትን ለማግኘት የሦስቱም ተሳትፎ ወሳኝ ነው።

እግዚአብሔር አብን በተመለከተ የምድር መሠረቶች ከመጣላቸው በፊት በክርስቶስ በተመረጥሁበት ጊዜ ድኛለሁ። የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ በሞተልኝ ጊዜ ድኛለሁ። በመንፈሱ ደግሞ ወንጌልን ሰምቼ ክርስቶስን በተቀበልኩበት ግንቦት ወር 1945 (እ. ኤ. አ.) አንድ ምሽት ድኛለሁ። ሁሉም በአንድነት እንዲሁም እያንዳንዱ ግላዊ መለኮት ወደ ደኅንነት አምጥቶኛል። እነዚህን አገልግሎቶች ለመለያየት ብንሞክር መለኮታዊ ሉዓላዊነትንና የሰውን ኃላፊነት እንክዳለን፤ ይህም ወደ ስሕተት ይመራናል።

ጴጥሮስ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ለማዳን ባለው ዕቅድ ውስጥ ያለውን የሰዎች ድርሻ አልካደም። በ1ኛ ጴጥሮስ 1፡23 እንዳብራራው ወንጌል ለእነዚህ ሰዎች ተሰበከ፤ እነርሱም ሰምተው አመኑ (1፡12ን ይመልከቱ)። ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ቀን ያደረገው ሁሉንም «እግዚአብሔር ያደርገዋል» ብለን መተው እንደሌለብንና የጠፉ ኃጢአተኞችንም ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ ማቻኮል እንደሌለብን ምሳሌ ይሰጠናል (የሐዋ. ሥራ 2፡37-40)። ፍጻሜውን ማለትም ደኅንነታችንን የወሰነ ጌታ ወደዚህ ፍጻሜ የምንደርስበትን፥ የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል የምንሰማበትን መንገድ ያዘጋጃል።

*ለ. የክርስቲያን ተስፋ (1፡3-4)*

ይህ ተስፋ ሕያው ተስፋ ነው። ምክንያቱም የተመሠረተው ሕያው በሆነው በእግዚአብሔር ቃልና (1፡23) ሕያው ሆኖ ከሙታን መካከል በተነሣው በእግዚአብሔር ልጅ አማካይነት ነው። «ሕያው ተስፋ» ሕያው በመሆኑ፥ ለእኛም ሕይወትን ይሰጠናል፤ ሕይወት ስላለው ደግሞ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ እያደገና እየተዋበ ይሄዳል። ጊዜ ብዙ ተስፋዎችን ያጨልማል። ቀስ በቀስ ይዝሉና ይሞታሉ። ነገር ግን የጊዜ ርዝመት የክርስቲያንን ተስፋ ባለ ብዙ ክብር ያደርገዋል።

ጴጥሮስ ይህንን ተስፋ ርስት በማለት ጠርቶታል (1፡4)። እንደ ንጉሥ ልጅነታችን የእርሱን ርስት በክብር እንጋራለን (ሮሜ 8፡17-18፤ ኤፌ. 1፡9-12)። በክርስቶስ የመጨረሻ ኑዛዜና ኪዳን ስለተካተትን ከእርሱ ጋር ክብር እንጋራለን (ዮሐንስ 17፡22-24)። ርስቱን በተመለከተ የተሰጠውን ማብራሪያ በደንብ አስተውሉ፤ ከማንኛውም ምድራዊ ርስት የተለየ ነው። አንደኛ፡- የማይጠፋ ነው ማለትም ማንም ሊያጠፋው አይችልም። የማይጠፋ በመሆኑ በምንም ዓይነት

መልኩ ሊረክስ ወይም ሊበከል አይችልም። ዘላለማዊ ስለሆነ፥ መቼም ቢሆን አያረጅም፥ አይበላሽም፥ ስለዚህም አያሳዝነንም።

በቁጥር 5 እና 9 ይህ ርስት «ደኅንነት» ተብሏል። አማኝ በክርስቶስ በማመን ድኗል (ኤፌ. 2፡8–9)። ነገር ግን የደኅንነታችን ፍጻሜ የአዳኙን መመለስ ይጠብቃል። ያኔ አዲስ አካል ለብሰን ወደ አዲስ አካባቢ ወደ ሰማያዊቱ ከተማ እንገባለን። ቁጥር 7 ላይ ጴጥሮስ ይህንን ተስፋ «የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ» ሲለው፥ ጳውሎስ ደግሞ «የተባረከው ተስፋችን» ብሎታል (ቲቶ 2፡13)።

ለክብር የተወለድን መሆናችንን ማወቅ የቱን ያህል አስደሳች ነገር ነው! ዳግም በተወለድን ጊዜ የሚያልፈውን የሰውን ክብር፥ በማያልፈው የእግዚአብሔር ክብር ለውጠናል።

## 2. ክርስቲያኖች ለክብር ተጠብቀዋል (1፡5)

ክብር፥ ለእኛ «የተጠበቀልን» ብቻ ሳይሆን እኛም ለክብር ተጠብቀናል። ለአገልግሎት ስጓዝ አንዳንድ ጊዜ ወደ ማረፊያ ሆቴል ስሄድ የያዝኩት ማረፊያ ተይዞ እንደሆነ ለማረጋገጥ እጠይቃለሁ። ወደ መንግሥተ ሰማያት ስንሄድ ግን እንዲህ ያለ ችግር አይገጥመንም። ምክንያቱም የዘላለም መኖሪያችንና ርስታችን ዋስትና ያለውና ለእኛ የተጠበቀ ነው።

«ሳይሆንልን ቢቀርስ?» ብሎ ፈሪ አማኝ ይጠይቅ ይሆናል። አማኞች ሁሉ «በእግዚአብሔር ኃይል የተጠበቁ» ስለሆኑ እንገባለን። «መጠበቅ» የሚለው ቃል የጦር ሠራዊት ቋንቋ ሲሆን «ታጥሮ በጋሻ መከለልን» ያመለክታል። የግሡንም ጊዜ አመልካች ስናየው ያለማቋረጥ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እየተጠበቅን እንዳለን የሚያመለክት ሲሆን ይህም ያለምንም ስጋት መንግሥተ ሰማይ በሰላም እንደምንደርስ ዋስትና ይሰጠናል። ጳውሎስ ሲያመልጥ በደማስቆ የነበሩት ወታደሮች ዙሪያውን ይጠብቁ እንደነበር ለመግለጽ ይህንን ቃል ተጠቅሞበታል (2ኛ ቆሮ. 11፡32)። በተጨማሪም ይሁዳ 24–25 ንና ሮሜ 8፡28–39ን ይመልከቱ።

አማኞች የተጠበቁት በራሳቸው ኃይል ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ኃይል ነው። በክርስቶስ ላይ ያለን እምነት ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረን ስላደረገን ኃይሉ ይጠብቀናል፤ ይመራናልም። እኛ የተጠበቅነው በራሳችን ብርታት ሳይሆን፥ በእርሱ ታማኝነት ነው። እስከ መቼ ነው የሚጠብቀን? ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ የታላቅ ማዳኑን ሙሉ መገለጥ እስክናይ ድረስ። ይህ እውነት በቁጥር «9» ላይ ተደግሟል።

«ለክብር መጠበቃችንን» ማወቅ የሚያበረታታ ነገር ነው። በሮሜ 8፡30 መሠረት፥ አሁንም ከብረናል። የምንጠብቀው የዚህን ክብር በይፋ መገለጥ ነው (ሮሜ 8፡18–23)። አንድ አማኝ ቢጠፋ የእግዚአብሔርን ክብር ያስዘርፋል ማለት ነው። እግዚአብሔር ክብሩን እንደ ዋስትና አድርጎ የሰጠን፥ መንግሥተ ሰማይ እንደምንገባ እርግጠኛ ስለሆነ ነው (ዮሐ. 17፡24፤ ኤፌ. 1፡13–14)።

ዛሬ የመንግሥተ ሰማይ ዋስትና እኛን ይረዳናል። ዶክተር ጀምስ ኤም. ግሬይ በመዝሙሩ እንደገለጸው «መንገዱ ወደ ቤት እስከመራን ድረስ፥ ስለ ጉዞው የሚያስብ ማን ነው?» የዛሬ መከራ ትርጉም የነገ ክብር ከሆነ፥ መከራ ለእኛ በረከታችን ይሆናል ማለት ነው። ያልዳኑት «ክብራቸውን» አሁን ያገኙ ሲሆን፥ ፍጻሜው ከእግዚአብሔር ክብር ተለይቶ ለዘላለም መሠቃየት ነው (2ኛ ተሰ. 1፡3–10)። በዚህ ብርሃን 2ኛ ቆሮ. 4፡7–18 ትኩረት ሰጥታችሁ በማንበብ ተደሰቱ!

## 3. ክርስቲያኖች ለክብር የተዘጋጁ ናቸው (1፡6–7)።

ማስታወስ ያለብን እግዚአብሔር በዚህ ዓለም እያለን ያቀደውና የሚያደርገው ሁሉ በመንግሥተ ሰማይ እግዚአብሔር ለእኛ ስላለው ነገር ሊያዘጋጀን ነው። በዚያ ስላለው ሕይወትና አገልግሎት እያዘጋጀን ነው። በላይ ያዘጋጀልንን ማንም የሚያውቅ የለም። ሆኖም ግን የምናውቀው ነገር ቢኖር የዛሬው ሕይወታችን እግዚአብሔር ወደፊት ላዘጋጀልን በዘላለማዊ ሕይወት ውስጥ ለምንሰጠው አገልግሎት እኛን የሚያሠለጥንበት ነው። ይህም በሕይወታችን መከራ የመኖሩን ምሥጢር ገላጭ ነው። እነርሱ በክርስትና የተመከሮ ትምህርት ቤት ውስጥ የትምህርት መርጃ መጣሪያዎችና መጻሕፍት ናቸው።

ክርስቲያኖች በማያምኑት መካከል ሲኖሩ የሚያጋጥሟቸውን ጠቅላላ ችግሮችን በሚመለከት ጴጥሮስ መከራ ወይም ስደት ከሚለው ቃል ይልቅ ፈተና የሚለውን ቃል መጠቀም መርጧል። ስለ ፈተናም በርካታ ሐቆችን አስፍሯል።

*ሀ. ፈተናዎች ጉድለታችንን ያሟሉልናል።* በፈተና ውስጥ ማለፍ ለእኛ አስፈላጊ የሚሆንበትን ልዩ ልዩ ጊዜያት እግዚአብሔር ያውቃቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ፈቃድ አንታዘዝም ስንል በፈተና ውስጥ አልፈን ተቀጥተን እንስተካከላለን [መዝ. (119)፡67] ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ፈተና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ ያዘጋጀናል። እግዚአብሔርን እንዳንበድልም ይረዳናል (2ኛ ቆሮ. 12፡1–9)።

የትኛው ጉድለታችን በመስተካከል ላይ እንዳለ ሁልጊዜ ባናውቀውም እንኳን እግዚአብሔር ለእኛ የሚበጀንን ነገር እንዲያደርግ ልንታመንበት እንችላለን።

*ለ. ፈተናዎች የተለያዩ ናቸው።* ጴጥሮስ ክርስቲያኖችን ስለሚያጋጥሙ ፈተናዎች ሲጽፍ ‹ልዩ ልዩ› የሚል ገላጭ ቃል ተጠቅሟል። ይህንኑ ቃል በምዕራፍ 4፡10 ላይ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመግለጽ የተጠቀመበት ሲሆን የጥሬ ቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ‹ባለ ብዙ ቀለም› ማለት ነው። ሰማያዊ ሰኞ ወይም ግራጫ ማክሰኞ በተለያዩ ችግሮች የቀለሙ ቀኖች ሊኖሩን ቢችሉም፥ እያንዳንዱን ቀን ማለፍ የምንችልበት የተለያየ የእግዚአብሔር ጸጋ አለን። ይሁን እንጂ አንዱን ዓይነት ፈተና በድል ስላለፍነው ሁሉንም ዓይነት ፈተና ወዲያውኑ እናሸንፋለን ብለን ማሰብ የለብንም። ይህ የሆነበት ምክንያት ፈተናዎች ልዩ ልዩ ስለሆኑ ነው። እግዚአብሔር ፈተናን የሚሰጠን ከአቅማችንንና ከፍላጎታችን ጋር አመጣጥኖ ነው።

*ሐ. ፈተናዎች ቀላል አይደሉም።* ጴጥሮስ ፈተናን በግድየለሽነት እንድንመለከት አላሳሰበንም። ምክንያቱም መከራን በዚህ መልክ ማየት አሳሳች ነገር ነው። ፈተና ትካዜ የሚያመጣ፥ የሚያስቆዝም፥ የሚያሠቃይ ነው። «ትካዜ» የሚለው ቃል ጌታ ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የተሰማውን የሥቃይ ስሜት ለመግለጽ ተጠቅሷል (ማቴ. 26፡37)። በሌላ ስፍራ ደግሞ ቅዱሳን የሚወዱቸው ሰዎች ከእነርሱ በሞት ሲለዩ የሚሰማቸውን ኀዘን ወይም ትካዜ ለመግለጽ ይህ ቃል ተጠቅሷል (1ኛ ተሰ. 4፡13)። ፈተናዎች ኀዘን የሞላባቸው መሆናቸውን መካድ የባሰውን አስከፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች በሕይወት ውስጥ አስቸጋሪ ገጠመኞች የመኖራቸውን እውነታ መቀበል አለባቸው እንጂ መከራን በድፍረት የሚጋፈጥ ብርቱ መንፈሳዊ መስለው በመታየት ማስመሰል የለባቸውም።

*መ. ፈተናዎች በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ናቸው።* ፈተና ለጊዜው እንጂ ለዘላለም የሚቆይ አይደለም። እግዚአብሔር ልጆቹ በእቶን እሳት ውስጥ እንዲያልፉ ሲፈቅድ በዓይኑ ሰዓቱን በእጁ ደግሞ የትኩሳቱን ልክ እየተቆጣጠረ ነው። የምናምጽ ከሆነ፥ የፈተናውን ሰዓት ያስረዝመዋል፤ እሺ ብለን የምንገዛለት ከሆነ ግን፥ ለተጨማሪ አንድ ደቂቃም ቢሆን ሥቃያችን እንዲረዝም አይፈቅድም። እግዚአብሔር በፈተና ውስጥ እንድናልፍ የሚፈልግበት ቁም ነገር ሊያስተምረን የሚፈልገውን ነገር እንድንማርና በመጨረሻም ክብርን ለእርሱ ብቻ እንድናመጣ ነው።

ጴጥሮስ ይህንን የመፈተን እውነት ከወርቅ አንጥረኛ ሥራ ጋር ያመሳስለዋል። ማንም አንጥረኛ ንጹሕ ወርቅ እንዲበላሽ አያደርግም። አንጥረኛው ቆሻሻው ከወርቁ እስከሚወገድ ድረስ በወርቅ ማንጠሪያው እሳት ውስጥ ያስቀምጠዋል። በእሳት ከነጠረው ንጹሕ ወርቅ የተዋበና ዋጋ ያለው ጌጥ ያዘጋጃል። የምሥራቅ ወርቅ አንጥረኞች የወርቁ ብረት ፊታቸውን እስከሚያሣይ ድረስ ከእሳት ውስጥ እንደሚያግሉት ይነገራል። የእኛም ጌታ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን ውበትና ክብር እስከምናንጸባርቅ ድረስ በመከራ እሳት ውስጥ እንድንቆይ ያደርገናል።

ማስታወስ ያለብን ጠቃሚ ነገር ቢኖር፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ለቤተ ክርስቲያን እስከሚመለስላት ድረስ ገና ሙሉ በሙሉ አለመገለጡን ነው። ዛሬ የሚያጋጥሙን ፈታኝ ልምምዶች ለነገ ክብር ያዘጋጁናል። ዛሬ በሚያጋጥሙን የሕይወት ፈተናዎች ውስጥ ታማኞች ብንሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ፊት ለፊት በምናይበት ቀን ምስጋናንና ክብርን ይዘንለት እንቀርባለን (ሮሜ 8፥17-18)። ጴጥሮስ ደስታን ከመከራ ጋር አያይዞ ያቀረበበት ምክንያትም ይኸው ነው። በዙሪያችን የከበበንን ፈተና እያየን መደሰት ባንችልም እንኳን፥ ከፊታችን ያለውንና የሚጠብቀንን ክብር ተመልክተን መደሰት እንችላለን። በቁጥር 6 ላይ «በዚህም» የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቁጥር 5 ላይ «መዳን» (በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ በተዘጋጀ መዳን) የሚለውን ነው።

አንጥረኛ ወርቁ ንጹሕ ወይም ሐሰተኛ መሆኑን ለመለየት እንደሚፈትን ሁሉ፥ በሕይወታችን የሚመጡት ፈተናዎች የእምነታችንን ትክክለኛነት የሚፈትሹ ናቸው። መፈተን ያልቻለን እምነት ለመታመን አይቻልም። ክርስቲያኖች እንደሆኑ የሚናገሩ ሰዎች እውነተኛ ያልሆነው እምነታቸው የሚገለጠው ሕይወታቸው ሲፈተን ነው። በጭንጫ ላይ የወደቀው ዘር ፈጥኖ በቀለ ግን ሥር ስላልነበረው ፀሐይ ሲወጣ ደረቀ (ማቴ. 13፥1-9፥ 18፥23)። በምሳሌው ፀሐይ የሚወክለው መከራ ወይም ስደትን ነው። እምነቱን በመከራ የጣለው ደግሞ ከጅምሩም እምነት እንዳልነበረው ያረጋግጣል።

ኢዮብ በእግዚአብሔር ፈቃድ በተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ በሚያልፍበት ጊዜ ሕይወትን ስለሚያጠራው እሳት መረዳት ነበረው። ‹የምሄድበትን መንገድ ያውቃል! ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ› (ኢዮብ 23፥10)። እንደተናገረውም ሆነለት።

እኛም ለክብር እንደተወለድን፥ ለክብር እንደተጠበቅን፥ ለክብር እንደምንዘጋጅ ማወቁ የሚያበረታታ ነው።

ነገር ግን ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹ ያካፈለው አራተኛው ግኝት ከሁሉም ይልቅ አስደሳች ሊሆን ይችላል።

## 4. ክርስቲያኖች አሁን እግዚአብሔር ባዘጋጀላቸው ክብር መደሰት ይችላሉ (1፡8-12)።

የክርስቲያኖች የሕይወት ፍልስፍና ‹ላም አለኝ በሰማይ› አይደለም። አሁን ባለንበት ምድር በእምነታችን ውስጥ መከራን ወደ ክብር የሚለውጥ ኃይል አለ። ጴጥሮስ በመከራ ውስጥ ሆነንም የምንከብርበትን አራት መንገዶች አስቀምጧል።

*ሀ. ኢየሱስ ክርስቶስን መውደድ (1፡8)።* ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለን ፍቅር የተመሠረተው በአካላዊ እይታ ላይ አይደለም። እስከአሁንም አላየነውም። ነገር ግን ፍቅራችን የተመሠረተው ከእርሱ ጋር ባለን መንፈሳዊ ግንኙነትና የእግዚአብሔር ቃል ስለ እርሱ ባስተማረን እውነት ላይ ነው። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍቅር በልባችን ያፈስሰዋል (ሮሜ 5፡5)። እኛ ደግሞ ያንኑ ፍቅር ለእርሱ መልሰን እንሰጣለን። በምትፈተኑበትና በምትጎዱበት ጊዜ፥ በእውነተኛ ፍቅርና በአምልኮ ወዲያውኑ ልባችሁን ወደ ክርስቶስ አንሡ። ለምን? ምክንያቱም ይህን ማድረግ ምሬትን ከውስጥ አውጥቶ የፈውስ መድኃኒት ይተካል።

ሰይጣን የሕይወትን ፈተና ተጠቅሞ ሕይወታችንን ሊያጎሳቁል ይፈልጋል። እግዚአብሔር ግን የሕይወትን ፈተና ከሕይወታችን መልካም ነገርን ለማውጣት ይጠቀምበታል። ከኢየሱስ ክርስቶስ ይልቅ ራሳችንን የምንወድ ከሆነ፥ ክብሩን አንለማመድም። እሳቱ የሚያቃጥለን እንጂ የሚያጠራን አይሆንም።

*ለ. በኢየሱስ ክርስቶስ ታመን (1፡8)።* በእምነት እንጂ በማየት መኖር የለብንም። አንድ ወይዘሮ በክረምት የሚካሄደውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲከታተሉ ሳሉ ወድቀው እግራቸው ተሰበረ። በኋላ ሊጎበኛቸው ወደ እርሳቸው ለሄደው መጋቢ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ «እግዚአብሔር ወደ ስብሰባው እንደመራኝ አውቃለሁ፤ ለምን እግሬ እንደተሰበረ ግን አልገባኝም። ከዚህ ምን ዓይነት በጎ ነገር ሊገኝ እንደሚችል ማየት ያስቸግረኛል።» መጋቢውም «ሮሜ 8፡28 ሁሉ ነገር ለበጎ እንዲደርግ እናያለን ሳይሆን እናውቃለን ነው ያለው» በማለት ጥበብ በተሞላበት መንገድ መለሰላቸው።

እምነት ማለት ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠትና በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ለቃሉ መታዘዝ ነው። እምነትና

ፍቅር በአንድነት ተስፋን ያጠናክሩታል። እምነትና ፍቅር ካገኘህ ስለ ወደፊቱ ሁኔታ በመተማመን ትኖራለህ።

በመከራና በፈተና ጊዜ፥ እንዴት በእምነት ማደግ እንችላለን? የእግዚአብሔርን ቃል ስንመገብ በእምነት እናድጋለን (ሮሜ 10፡17)። ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በቃሉ በኩል የሚኖረን ኅብረት እምነታችንን ማጠንከር ብቻ ሳይሆን፥ ለእርሱ የጠለቀ ፍቅር እንዲኖረንም ያደርጋል። እግዚአብሔር በሚፈትነን ጊዜና ሰይጣን በፈተና ሊጥለን በሚፈልግበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ቃል ብዙ ጊዜያችንን መስጠት መሠረታዊ የሆነ የክርስትና ሕይወት መመሪያ ነው።

*ሐ. በኢየሱስ ክርስቶስ ተደሰቱ (1፡8)።* በሁኔታዎች ላትደሰቱ ትችላላችሁ፥ ግን ልባችሁን እና አሳባችሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በማድረግ በመከራዎቻችሁ መደሰት ትችላላችሁ። በመከራ ውስጥ የሚኖረን እያንዳንዱ ልምምድ ስለ አዳኛችን አዲስና አስደናቂ የሆኑ ነገሮችን እንድንማር ይረዳናል። አብርሃም ልጁን ለመሥዋዕት ባቀረበበት ተራራ ላይ ስለ እግዚአብሔር አዲስ እውነት አገኘ (ዘፍ. 22)። ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጎም ሦስቱ የአይሁድ ወገኖች በእቶን እሳት ውስጥ ሲገቡ የእግዚአብሔርን ቅርብነት ተገነዘቡ (ዳን. 3)። ጳውሎስ በሥጋው መውጊያ ሲሠቃይ የእግዚአብሔርን ጸጋ ብቃት ተማረ (2ኛ ቆሮ. 12)።

አስተውሉ እግዚአብሔር የሚሰጠን ደስታ ‹የማይነገርና በክብር የተሞላ ነው›። ይህ ደስታ አስደናቂና ጥልቅ ከመሆኑ የተነሣ ለመግለጽ እንኳን አንችልም። ቃላቶች ያጥሩናል። ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሴንና ኤልያስን ባነጋገረበት ተራራ ላይ የተለወጠውን የጌታን ክብር አየ።

*መ. ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ መቀበል (1፡9)* ‹ማመን. . . መቀበል. . .› እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ነገር የሚያሟላበት መንገድ ነው። ጌታን የምንወደው፤ የምናምነው እና በእርሱ ደስ የሚለን ከሆነ፥ ፈተናን ወደ ድል በመለወጥ የሚያስፈልገንን ሁሉ ከእርሱ ልንቀበል እንችላለን። ቁጥር 9 ‹በእርሱ አምናችሁ የእምነታችሁን ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ› ይላል። ይህ ማለት የወደፊቱን ክብር ዛሬ በዚህ ምድር እንለማመደዋለን ማለት ነው። ቻርለስ ስፐርጂን ‹ታናሽ እምነት ነፍስህን ወደ መንግሥተ ሰማይ ታደርሰዋለች፥ ታላቅ እምነት ደግሞ መንግሥተ ሰማይን ወደ አንተ ያመጣዋል› በማለት ይናገር ነበር። በመከራ ጊዜ የእግዚአብሔርን መንግሥት መናፈቅ በቂ አይደለም።

ይህንን ማንም ሊያደርገው ይችላል። ጴጥሮስ አንባቢዎቹ ፍቅርን፥ እምነትንና ደስታን እንዲለማመዱ ያሳስባል። ምክንያቱም ይህን በማድረግ በመንግሥተ ሰማይ ያለውን ክብር አሁን በዚህ ምድር በመከራ ውስጥ መለማመድ እንዲችሉ ነው።

አስደናቂው ነገር ይህ «ደኅንነት» ማለትም «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ» እግዚአብሔር ከዘላለም ጀምሮ ለእኛ ያቀደው ነገር ነው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለዚህ ነገር ጽፈዋል፤ እግዚአብሔር የገለጸላቸውንም ነገር በጥንቃቄ አጥንተውታል። የመሢሑ መከራና የሚከተለውን ክብር አይተዋል። ይሁን እንጂ በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ አልተገነዘቡም። እንደ እውነቱ ከሆነ በአንዳንድ ትንቢቶች የመሢሑ መከራና ክብር በአንድ አንቀጽ ወይም ቁጥር ውስጥ በአንድ ላይ ተገልጸዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመጣ፥ የአይሁድ መምህራን የእስራኤል ጠላቶችን ድል ነሥቶ ለዳዊት የተገባለትን የክብር መንግሥት የሚመሠርት ነፃ አውጭ መሢሕ ይጠብቁ ነበር። ሌላው ቀርቶ ደቀ መዛሙርቱ እንኳን በመስቀል የመሞቱ አስፈላጊነት ግልጽ አልሆነላቸውም ነበር (ማቴ. 16፡13–28)። ከትንሣኤውም በኋላ ገና ስለ አይሁድ መንግሥት ይጠይቁ ነበር (የሐዋ. ሥራ 1፡1–8)። ደቀ መዛሙርቱ የእግዚአብሔር ዕቅድ ግልጽ ካልሆነላቸው የብሉይ ኪዳን ነቢያት ምሕረት ሊደረግላቸው ይችላል።

እግዚአብሔር፥ ነቢያት መጭውን ትውልድ እንደሚያገለግሉ ነግሯቸዋል። በመሢሑ መከራና በክብር ምጽአቱ መካከል፥ «የቤተ ክርስቲያን ዘመን» አለ። ስለ ቤተ ክርስቲያን ያለው እውነት በብሉይ ኪዳን ዘመን «ምሥጢር» ነበር (ኤፌ. 3፡1–13)። የብሉይ ኪዳን አማኞች በእምነት አሻግረው ሁለት የተራራ ቁንጮዎችን ተመለከቱ። አንደኛው ተራራ መሢሑ የሚሠቃይበትና የሚሞትበት ሲሆን (ኢሳ. 53)፥ ሌላው ደግሞ በክብር የሚመለስበት የደብረ ዘይት ተራራ ነው (ዘካ. 14፡4)። ነቢያት በመካከል ያለውን ሸለቆ የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ማየት አልቻሉም።

መላእክትም ቢሆኑ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እና በእርሷ በኩል ምን እንደሚሠራ ለማወቅ ይጓጓሉ። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን በኩል እንዴት መላእክትን እንዳስተማረ በ1ኛ ቆሮንቶስ 4፡9 እና በኤፌሶን 3፡10 ላይ ማየት ይቻላል።

የብሉይ ኪዳን ነቢያት የመዳንን እውነት በትጋት ቢፈልጉም፥ የተረዱት በጥቂቱ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት የተቀበልን እኛ ደግሞ ስለ ደኅንነት ለማወቅ እንዴት አብዝተን መትጋት

አይገባንም! ነቢያትን ያስተማረ፥ በእነርሱ በኩል ቃሉን ያስተላለፈ ያ መንፈስ ቅዱስ፥ በቃሉ ውስጥ ያለውን እውነት ያስተምረናል (ዮሐ. 16፡12−15)።

ይህንን እውነት በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ልናገኘው እንችላለን። በማንኛውም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠቅሶ እናገኛለን (ሉቃስ 24፡25−27)። ስለ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን የሕግ፥ የቅኔ፥ የመዝሙርና የነቢያት መጻሕፍት ላይ ማግኘቱ ምን ያህል ያስደስታል። በፈተና ጊዜ ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማበረታቻና ለትምህርት የሚሆነንን ነገር ማግኘት እንችላለን።

እርግጥ ነው ለክርስቲያን ሁሉም መንገድ የክብር ነው! በክርስቶስ ባመንን ጊዜ ለክብር ተወለድን። ለሚመጣው ክብር ደግሞ ተጠብቀናል። ጌታን ስንታዘዝና በመከራ ውስጥ ስናልፍ ለክብር በመዘጋጀት ላይ ነን። ጌታችንን ስንወደው፤ ስንታመንበት፤ በእርሱ ደስ ስንሰኝ ክብሩን አሁን በዚህ ምድር እንለማመዳለን።

ክብር የሞላበት ሊነገር የማይችል ደስታ!

# 3

# በቆሻሻው ዓለም ውስጥ በንጽሕና መኖር

(1ኛ ጴጥሮስ 1፡13–21)

በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያ ክፍል ላይ፥ ጴጥሮስ አጽንኦት የሰጠው በተስፋ ስለመኖር ነበር። አሁን ደግሞ ትኩረቱ በቅድስና ስለመኖር ነው። ሁለቱም አብረው ይሄዳሉ። «በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል» (1ኛ ዮሐ. 3፡3)።

ቅዱስ የሚለው ቃል የተተረጎመበት ሥርወ ቃሉ፥ «የተለየ» ማለት ነው። ቅዱስ ሰው ማለት ከሰው የማይገጥም ወይም የማይስማማ ሰው ማለት አይደለም። ቅዱስ ሰው ማለት ግን ከሌላው የተለየ ብቃት ያለው ሰው ማለት ነው። «አኗኗሩ» የሚለየው ከቀድሞ ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ካሉ ከማያምኑት ሰዎች «የአኗኗር ዘይቤ» ጭምር ነው። የአማኞች የተቀደሰ ሕይወት የሚጠፉትን ሰዎች ያስደንቃቸዋል (1ኛ ጴጥሮስ 4፡4)። ለሌሎች አማኞች ግን በቅድስና መኖር የሚያስደንቅ አይደለም።

ይሁን እንጂ በዚህ ዓለም በቅድስና መመላለስ ቀላል ነገር አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር የሚቃረነው እና መጽሐፍ ቅዱስ «ዓለም» ብሎ የሚጠራው በዙሪያችን የሚገኘው የአኗኗር ዘይቤ ዓለማዊ ኑሮ እንድንኖር ጫና ያደርግብናል። በኃጢአት በተበከለ ዓለም ውስጥ አማኞች የተለየና የተቀደሰ የኑሮ ዘይቤ እንዲኖራቸው የሚያበረታቱ አምስት መንፈሳዊ እውነቶችን ጴጥሮስ ለመልእክቱ አንባቢዎች አቅርቧል።

## 1. የእግዚአብሔር ክብር (1፡3)

«የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ» የሚለው ሐረግ «ሕያው ተስፋ» እና «የኢየሱስ ክርስቶስ መታየት» የሚገለጽበት ሌላው መንገድ ነው። የአማኞች ተግባርና ውሳኔ የሚመራው በወደፊት ተስፋቸው ላይ ነው። እጮኛሞች ያላቸውን የወደፊት ዕቅድ የሚያወጡት ከሚፈጽሙት የጋብቻ ጊዜያቸው አንጻር እንደሆነ ሁሉ፥ ክርስቲያኖችም የሚገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን በማሰብ ዛሬን ይኖራሉ።

«የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁ» ማለት «አሳባችሁን አጠቃሉ! በሥርዓት የሚመራ አእምሮ ይኑራችሁ!» ማለት ነው። መጎናጸፊያ

የለበሰ ሰው ደኅና አድርጎ መሮጥ እንዲችል ወገቡ ላይ ይታጠቃል። አሳባችሁን በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ላይ ስታደርጉ፥ እንደ ፈቃዱ ስትኖሩ፥ አሳባችሁን ከሚይዙና የመንፈሳዊ ሕይወት እድገታችሁን ከሚገቱ ዓለማዊ ነገሮች ሁሉ ታመልጣላችሁ። አይሁዶች በግብጽ ባደረጉት የፋሲካ በዓል ፈጥነው መብላትና ለጉዞም መዘጋጀት ነበረባቸው (ዘፀ. 12፡11)። ጴጥሮስም አሳቡን የወሰደው ከዚህ ክፍል ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም በቁጥር 19 ላይ ክርስቶስን በበግ ምሳሌ ጠቅሶታል።

አመለካከት ፍጻሜን ይወስናል። የውስጥ ዝንባሌ ደግሞ ድርጊትን ይወስናል። የእግዚአብሔርን ክብር የሚፈልጉ ክርስቲያኖች የጌታን መመለስ በተስፋ ከማይጠባበቁት ክርስቲያኖች ይልቅ በመታዘዝ እንዲኖሩ የሚያነቃቃ ምክንያት አላቸው። ይህም በአብርሃምና በሎጥ ሕይወት ውስጥ ተንጸጽሯል (ዘፍጥ. 12–13፤ ዕብ. 11፡8–16)። አብርሃም የእምነት ዓይኑን ያሳረፈው በሰማያዊዋ ከተማ ላይ ስለነበር፥ ለምድራዊው ርስት አይጓጓም ነበር። የዚህን ዓለም ደስታ በግብጽ የቀመሰው ሎጥ ግን ቀስ በቀስ ወደ ሰዶም ወርዶ አብርሃም በረከትን ወደ ቤቱ ሲያመጣ ሎጥ ግን ፍርድን አመጣ። አመለካከት ፍጻሜን ይወስናል።

በሥርዓት የሚመራ አእምሮ ብቻ ሳይሆን፥ የተረጋጋ አእምሮም ሊኖረን ይገባል። የተረጋጋ አእምሮ ማለት «ነገሮችን የሚያመዛዝን፥ ራሱን የሚገዛ፥ ሰላም የሰፈነበት፥ ጭምት፥ የማይናወጥ» ማለት ነው። እንደ አጋጣሚ ሆኖ አንዳንድ ሰዎች በትንቢት ጥናት ስለተወሰዱ፥ መንፈሳዊ ሚዛናቸውን አጥተዋል። የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት እንደ ባለ አእምሮ እንድናስብ ያበረታታናል (1ኛ ጴጥሮስ 4፡7)። ሰይጣን የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ መዞሩ በንቃት እንደ ባለ አእምሮ ለመኖር ሌላው ምክንያት ነው (5፡8)። የትንቢትን ቃል በማጥናታቸው ያለ ሥርዓት የሚኖሩና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ስለሚንኮታኮት የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት እንዳልተረዱት ማረጋገጫው ይኸው ነው።

ከፊታችን መልካም ነገር እንዳለ የሚያምን ልብ ሊኖረን ይገባል። «እስከ መጨረሻው ተስፋ አድርግ» ማለት፥ «ሙሉ በሙሉ ተስፋ አድርግ፥ ተስፋ የሞላበት አመለካከት ይኑርህ» ማለት ነው። አንድ ቀን ጓደኛዬ «ከጨለማው የተነሣ ወደ ውጭ መመልከት ካልቻልክ፥ ወደ ላይ ተመልከት።» የሚል ማስታወሻ ላከልኝ። በእውነት መልካም ምክር ነው! ከዋክብት የሚወጡት ሲጨልም ነውና።

የዚህ መንፈሳዊ አመለካከት ውጤቱ አማኞች የእግዚአብሔርን ጸጋ በሕይወታቸው እንዲለማመዱ ማድረጉ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ ዛሬም መመለሱን ስንጠባበቅ ጸጋን እንቀበላለን። በጸጋ ድነናል። በእያንዳንዱ ደቂቃ በዚህ ጸጋ ላይ እንደገፋለን (1፡10)። የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ መጠባበቁ በመከራ ቀን እምነታችንን እና ተስፋችንን ያጠነክረዋል። ይህም የእግዚአብሔር ጸጋ እንዲበዛልን ያደርጋል። በጸጋ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳየን ሌላ ክፍል ቲቶ 2፡10–13 ነው።

## 2. የእግዚአብሔር ቅድስና (1፡14–15)

በዚህ ክፍል ያለው የመፍትሔ አሳብ ግልጽና ሥነ አመክንዮአዊ ነው። ልጆች የወላጆቻቸውን ባሕርይ ይወርሳሉ። እኛም የቅዱስ እግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን፥ በቅድስና መኖር ይገባናል የሚል ነው። እኛ የመለኮታዊው ባሕርይ «ተካፋዮች» በመሆናችን (2ኛ ጴጥሮስ 1፡4)፥ ይህንን ማንነታችንን በተቀደሰ አኗኗራችን ማሳየት ይገባናል።

ጴጥሮስ የመልእክቱን አንባቢዎች በክርስቶስ ከማመናቸው በፊት ምን እንደነበሩ ያስታውሳቸዋል። የዐመጻ ልጆች ነበሩ (ኤፌ. 2፡1–3)። አሁን ግን ታዛዥ ልጆች ሊሆኑ ይገባ ነበር። እውነተኛ ደኅንነት መታዘዝን ያስከትላል (ሮሜ 1፡5፤ 1ኛ ጴጥ. 1፡2)። ከዚህ በፊት ዓለምን የሚኮርጁ ነበሩ። ራሳቸውም ለዚህ ዓለም ደስታና ኑሮ የተመቻቹ ነበሩ። በሮሜ 12፡2 ላይ «ይህን ዓለም መምሰል» ይላል። ያልዳኑት «ነጻና የተለዩ» ሰዎች መሆን እንደሚፈልጉ ይነግሩናል፤ ነገር ግን አንዱ ሌላውን ሲከተልና ሲኮርጅ ይታያል።

ያልዳኑ ሰዎች መንፈሳዊ እውቀት ይጎድላቸዋል። አለማወቃቸው ደግሞ ለሥጋዊና ለዓለማዊ ኑሮ ዳርጎአቸዋል (የሐዋ. ሥራ 17፡30 እና ኤፌ. 4፡17 ይመልከቱ)። የተወለድነው ከወደቀው ባሕርይ ጋር ስለነበር፥ በኃጢአት መኖር ለእኛ ተፈጥሮአዊ ነበር። ፍላጎታችንንና ድርጊታችንን የሚወስነው ተፈጥሮአዊ ማንነታችን ነው። ውሻና ድመት አንድ ዓይነት ባሕርይ አያሳዩም። ይህ የሆነበት ምክንያት የተለያየ ተፈጥሮ ስላላቸው ነው።

የእግዚአብሔር ጸጋ ባይኖር፥ እስከ ዛሬ ድረስ እኛም በዚያ በኃጢአተኛ ተፈጥሮአችን ውስጥ እንኖር ነበር! አንድ ቀን ኢየሱስ ጴጥሮስንና ጓደኞቹን «በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ» አላቸው (ማርቆስ 1፡17)። ለጥሪውም በእምነት ምላሽ በመስጠታቸው ሕይወታቸው ፍጹም ተለወጠ።

ጴጥሮስም ብዙ ጊዜ በመልእክቱ «ተጠራን» የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ምክንያት ይህ ሳይሆን እንደማይቀር ይገልጽልናል። ምክንያቱም ለመቀደስ ተጠርተናል (1፡15)። ከድቅድቅ ጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃንም ተጠርተናል (2፡9)። መከራን እንድንቀበልና የክርስቶስን ፈለግ እንድንከተል ተጠርተናል (2፡21)። በስደት መካከል «በረከትን እንድንወርስ» ተጠርተናል (3፡9)። ከሁሉም የሚበልጠው ደግሞ ወደ «ዘላለም ክብሩ» ተጠርተናል (5፡10)። እኛ ደኅንነትን ስጠን ብለን ከመጠየቃችን በፊት፥ እግዚአብሔር ጠራን። ደኅንነታችን ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ ነው።

እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ቅዱሳን የማድረግ የጸጋ ምርጫው ምንጊዜም፥ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ነው። በክርስቶስ የመረጠን «ቅዱስና ያለነቀፋ እንድንሆን ነው» (ኤፌ. 1፡4)። እግዚአብሔር ለእርሱ መርጦናል። ስለዚህ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ፥ ቅዱስ መሆን አለብን። ጴጥሮስ ይህንን የጠቀሰው ከብሉይ ኪዳን ሕግ ነው (ዘሌ. 11፡44–45፥ 19፡2፥ 20፡7፥ 26)።

ቅድስና የእግዚአብሔር ዋነኛ ባሕርይ ነው። «እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም» (1ኛ ዮሐ. 1፡5)። በባሕርያችን የምናሳየው ቅድስና ከእርሱ የተገኘ መሆን አለበት። በመሠረቱ «መቀደስ» ማለት «ለእግዚአብሔር ደስታና መጠቀሚያነት መለየት» ማለት ነው። ለዚህ ደግሞ ርኩስ ከሆነው ነገር ተለይቶ ራስን ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መስጠትን ይጠይቃል (2ኛ ቆሮ. 6፡14–7፡1)። በባሕርያችንና በንግግራችን በመቀደስ የእግዚአብሔርን ቅድስና በሁሉ ነገር ማሳየት ይኖርብናል።

ራሱን ለጌታ ለሰጠ አማኝ ይህን ለ«ዓለም» ይህን ደግሞ ለ«ቅድስናዬ» ሳድርገው የሚለው ነገር አይኖረውም። ለእግዚአብሔር ክብር ስንኖር ሁሉም የሕይወታችን ክፍል ይቀደሳል። ሌላው ቀርቶ እንደ መብላትና መጠጣት ያሉ የዕለት ተዕለት ተግባራት ጭምር ለእግዚአብሔር ክብር ሊደረጉ ይገባል (1ኛ ቆሮ. 10፡31)። ለእግዚአብሔር ክብር የማይደረግ ነገር ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን ማረጋገጥ እንችላለን።

## 3. የእግዚአብሔር ቃል (1፡16)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰይጣንን ለመቃወም የእግዚአብሔርን ቃል ተጠቅሟል (ማቴ. 4፡1–11)። እኛም እንደዚሁ በእግዚአብሔር ቃል ሰይጣንን እንቃወማለን (ኤፌ. 6፡17)። «በቃሉ ተጽፎአል!» የሚለው ለአንድ አማኝ ትልቅ ሥልጣን የያዘ መልእክት ነው። የእግዚአብሔር ቃል በጦር ሜዳ የሚመዘዝ ሰይፍ ብቻ ሳይሆን፥ በጨለማው ዓለም

ውስጥ የሚመራን ብርሃናችን ነው [2ኛ ጴጥሮስ 1፥19፤ መዝ. (119)፥105]። የእግዚአብሔር ቃል የሚያበረታን ምግብ (ማቴ. 4፥4፥ 1ኛ ጴጥ. 2፥2)፥ የሚያነጻን ውኃ ነው (ኤፌ. 5፥25-27)።

የእግዚአብሔር ቃል በተሰጠ አማኝ ሕይወት ውስጥ፥ የመቀደስን ሥራ ይሠራል (ዮሐ. 17፥17)። በእግዚአብሔር ቃል የሚደሰቱ፥ የሚያሰላስሉት እና ሊታዘዙት የሚሹ ሁሉ፥ ምሪትንና በረከትን ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ (መዝ. 1፥1-3)። ቃሉ፥ የእግዚአብሔርን አሳብ ስለሚገልጥ ልንማረው ይገባል፤ የእግዚአብሔር ልብ ስለሆነ እንውደደው፤ የፈቃዱ መግለጫ ስለሆነ እንኑረው። አሳባችን፥ ፈቃዳችን፥ ልባችን፥ በአጠቃላይ ሁለንተናችን በእግዚአብሔር ቃል ቁጥጥር ሥር ሊሆን ይገባል።

ጴጥሮስ ዘሌዋውያን መጽሐፍ «እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ ቅዱሳን ሁኑ» (11፥44) የሚለውን ቃል ጠቅሶታል። የብሉይ ኪዳን ሕግ በአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ሥልጣን ያለው ሊኖሩት የሚገባ ቃል ነውን? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን። መዘንጋት የሌለብን ነገር ቢኖር፥ የጥንት ክርስቲያኖች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አልነበራቸውም። እግዚአብሔር ሕይወታቸውን ለመምራትና ለመመገብ የሚጠቀምበት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ነበር። የአዲስ ኪዳን አማኞች ለእስራኤል የተሰጡትን ሥርዓታዊ ሕጎች መጠበቅ አያስፈልጋቸውም። ይሁን እንጂ በሕጉ መንፈሳዊና ሥነ ምግባራዊ መመሪያዎች ተገልጸው እናያለን። ከአሥርቱ ትእዛዛት ዘጠኙ በመልእክቱ ውስጥ ተደግመዋል። ስለዚህ ልንታዘዛቸው ይገባናል። (ሰንበትን የማክበር ትእዛዝ ግን በተለይ የተሰጠው ለእስራኤል ስለሆነ፥ እኛ ልንጠብቀው አያስፈልገንም። ሮሜ 14፥1-9ን ይመልከቱ)። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ስናነብና ስናጠና ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ሥራ ብዙ እንማራለን፤ እንዲሁም በተምሳሌቶችና በትምህርቶች የተገለጹትን እውነቶች እናያለን።

በኃጢአት በጎደፈ ዓለም ውስጥ በንጽሕና ለመኖር የመጀመሪያው እርምጃ «መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?» ብሎ መጠየቅ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ጠቃሚ ምክሮችን፥ መመሪያዎችንና ተስፋዎችን እናገኛለን። በእውነት ፈቃዱን ለማድረግ ብንወድ፥ እርሱ እውነትን ያሳየናል (ዮሐ. 7፥17)። እግዚአብሔር የሚሠራበት መንገድ ከዘመን ወደ ዘመን ሊቀያየር ይችላል፤ ባሕርይው ግን አይቀየርም። መንፈሳዊ መመሪያዎቹም አይቀያየሩም። የምናጠናው መጽሐፍ ቅዱስን ለማወቅ ብቻ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱሳችንን የምናጠናው እግዚአብሔርን በተሻለ መልኩ ለማወቅ ነው። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እግዚአብሔርን ከማወቅ ይልቅ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጡትን

ገለጻዎችና ዝርዝር ሁኔታዎች በማወቅ ይደሰታሉ። እግዚአብሔርን ግን ለማወቅ አይጥሩም። ቃሉን ማወቅ መልካም ነው። የቃሉን ጌታ የበለጠ ለማወቅ ይጠቅመናል።

## 4. የእግዚአብሔር ፍርድ (1:7)።

የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን መጠን፥ ስለ ኃጢአትና ስለ ተቀደሰ አኗኗር ጠንቃቃ መሆን አለብን። የሰማዩ አባታችን ቅዱስ እና (ዮሐ. 17:11)፥ ጻድቅ ነው (17:25)። እግዚአብሔር በኃጢአት አያመቻምችም። መሐሪና ይቅር ባይ ቢሆንም፥ ልጆቹ ኃጢአት እንዲያደርጉ የማይፈቅድ ባሕርይ ያለው፥ በፍቅር የሚቀጣ አምላክ ነው። ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሞት ያደረገው ኃጢአት ነው። እግዚአብሔርን «አባት» ብለን የምንጠራው ከሆነ፥ በሕይወታችን ባሕርዩን ማንጸባረቅ አለብን።

ጴጥሮስ የጻፈው ስለ ምን ዓይነት ፍርድ ነው? የአማኞች ሥራ የሚፈረድበት ፍርድ ነው። ከደኅንነት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ደኅንነት መልካም ሥራ ለመሥራት የሚያስችል መሆን አለበት (ቲቶ 1:16፤ 2:7፥ 12)። በክርስቶስ ባመንን ጊዜ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ብሎ በልጁ በኩል ጽድቃችንን አውጇል (ሮሜ 5:1–10፥ 8:1–4፤ ቆላ. 2:13)። ኃጢአታችን በመስቀል ላይ ተፈርዶበታል (1ኛ ጴጥሮስ 2:24)፤ ስለዚህ ዳግም አይታሰብብንም (ዕብ. 10:10–18)።

ጌታችን ዳግም በሚመለስበት ጊዜ፥ «የክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት» የሚባል የፍርድ ቀን አለ (ሮሜ 14:10–12፤ 2ኛ ቆሮ. 5:9–10)። እያንዳንዳችን ለሠራነው ሥራ መልስ እንሰጥበታለን፤ ተገቢ ሽልማታችንንም እንቀበላለን። ይህ እግዚአብሔር በልጆቹ መካከል የሚያደርገው «የቤተሰብ ፍርድ» ነው። በግሪክ ፍርድ ማለት «መልካም ነገርን ለማግኘት የሚደረግ ውሳኔ» ማለት ነው። እግዚአብሔር ልባችንን ይመረምራል። እርሱን ለማገልገል የፈለግንበትን ምክንያት ይመረምራል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ዓላማ በሕይወታችን እና በአገልግሎታችን መከበር መሆኑን ያረጋግጥልናል። «. . . በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል» (1ኛ ቆሮ. 4:5)። እንዴት የሚያበረታታ ነገር ነው!

በመንፈሳዊ ሕይወታችን እያደግን በሄድን ቁጥር፥ እግዚአብሔር ብዙ ጸጋዎችን ይሰጠናል። ያለ መታዘዝና ኃጢአት የመሥራት ነጻነት ግን ፈጽሞ አይሰጠንም። ልጆቹ ያለ ሥርዓት እንዲኖሩ አያደርግም። እግዚአብሔር «በፍርድ የማያደላ፥ መማለጃም የማይቀበል ነውና» (ዘዳ. 10:17)። «እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያደላምና» (ሮሜ 2:11)።

ሰውን ከሰው አበላልጦ ክብር አይሰጥም። የዓመታት ታዛዥነት የአንድ ሰዓት አለመታዘዝን አይገዛም። ከልጆቹ አንዱ ባይታዘዝ፥ እግዚአብሔር ይቀጣዋል (ዕብ. 12፡1-13)፤ ለሚታዘዘውና በፍቅር ለሚያገለግለው ልጁ ግን ሽልማቱን ያዘጋጅለታል።

ጴጥሮስ፥ አንባቢዎቹ በምድር ላይ «እንግዶች» ብቻ መሆናቸውን ያሳስባቸዋል። ሕይወት አጭር በመሆኗ ባለመታዘዝና በኃጢአት ኑሮ የሚባክን ጊዜ የለም (1ኛ ጴጥሮስ 4፡1-6)። ሎጥ ቅድስናውንና ምስክርነቱን ያጣው የእንግድነት ሕይወቱን አቁሞ የሰዶም ቋሚ ነዋሪ በሆነበት ጊዜ ነው። በሕይወቱ የኖረለት ነገር ሁሉ ጭስ ሆኖ ወደ ሰማይ በነነ! በዚህ ምድር ላይ «እንግዶችና መጻተኞች» መሆናችሁን ዘወትር አስታውሱ (1፡1፥ 2፡11)። አባት ልጆቹን በፍቅር እንደሚቀጣና ወደ ፊት ሥራቸውን እንደሚፈርድ በማወቅ ንጹሕ ፍርሃትን በውስጣችን ማሳደግ አለብን። ፍርሃታችን ባሪያ በጌታው ፊት እንደሚንቀጠቀጠው ዓይነት ፍርሃት ሳይሆን፥ ልጅ በአባቱ ፊት የሚያሳየው የፍቅር ፍርሃት ነው። ይህ ፍርሃት ፍርድን በመፍራት አይደለም (1ኛ ዮሐ. 4፡18)፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን የማሳዘንና በፍቅሩ ላይ በማመጻችን የሚከሰት ፍርሃት ነው። ይህ ፍርሃት «የእግዚአብሔር ፍርሃት» ነው (2ኛ ቆሮ. 7፡1)፤ ለእግዚአብሔር እንደ አባት እውነተኛ አክብሮት መስጠት ነው።

በዚህ ዘመን ስለ እግዚአብሔር የምንናገርበት ሁኔታም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በምንነጋገርበት ጊዜ፥ በግዴለሽነት እንደሆነ ይሰማኛል። ከብዙ ዓመታት በፊት ቢ. ኤፍ. ዌስት ኮት «ሰዎች በየዓመቱ በመንፈሳዊ ነገር ላይ የሚናገሩት የድፍረት ቃል ያስፈራኛል» ብሏል። ይህ የእግዚአብሔር ሰው ዛሬ ስለ እግዚአብሔር የሚባለውን በሰማ! አንዲት ተዋናይ እግዚአብሔርን «ፎቅ ላይ ያለው ሰው» ብላ ጠርታዋለች። የቤዝቦል ተጫዋች ደግሞ እግዚአብሔርን «በሰማይ ላይ ያለው ትልቁ ያንኪ» በማለት ጠርቶታል። የብሉይ ኪዳን አይሁድ እግዚአብሔርን ከመፍራቱ የተነሣ ቅዱስ ስሙን በአፉ እንኳን አይጠራም ነበር። ዛሬ ግን እኛ ስለ እግዚአብሔር አክብሮት በጎደለውና በግዴለሽነት እንናገራለን። አንዳንዴ በጉባኤ ስንጸልይ፥ ልመናችንን ለእግዚአብሔር እያቀረብን ይሁን፥ ወይም ለእግዚአብሔር ያለንን ቅርበት ለማሳየት እንደሆነ ምን ማድረግ እንደፈለግን ለማወቅ አድማጮቻችን ይቸገራሉ።

## 5. የእግዚአብሔር ፍቅር (1፡18-21)።

በተቀደሰ ሕይወት ለመኖር በከፍተኛ ሁኔታ የሚቀሰቅሰን የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። ጴጥሮስ አንባቢዎቹን ስለ ደኅንነታቸው

ያስታውሳቸዋል። ይህን ማስታወስ ለሁላችንም ዘወትር ያስፈልገናል። ጌታችን የጌታ ራት ሥርዓትን የሰጠው የእርሱ ሕዝቦች ስለ ኃጢአታቸው እንደሞተላቸው እንዲያስታውሱ ነው። ጴጥሮስ እነርሱ ማን እንደነበሩ ያስታውሳቸዋል።

በመጀመሪያ ነፃ መውጣት የሚያስፈልጋቸው ባሮች ነበሩ። «ተዋጃችሁ» የሚለው የሥነ መለኮት ቃል በ1ኛው ክፍለ ዘመን በሮማ ግዛት ለሚኖሩ ሰዎች የተለየ ትርጉም አለው። በግዛቱ ወደ 50 ሚሊዮን የሚሆኑ ባሮች ነበሩ! ብዙ ባሮች ክርስቲያን ሆነው በአጥቢያ ስብሰባ ላይ ይካፈላሉ። አንድ ባሪያ በቂ ገንዘብ መክፈል ከቻለ ወይም ጌታው ለሌላ ሰው ከሸጠውና ያ ሰው ዋጋውን ከከፈለለት ነፃ መውጣት ይችላል። በዚያ ዘመን መቤዠት የከበረ ነገር ነው።

የኃጢአት ባሪያ መሆንን ፈጽሞ መርሳት የለብንም (ቲቶ 3፡3)። ሙሴ እስራኤላውያንን በግብፅ ባሪያ የነበሩበትን ዘመን እንዳያስታውሱ ይለምናቸዋል (ዘዳግ. 5፡15፤ 16፡12፤ 24፡18፥ 22)። በምድረ በዳ ያለቀው ትውልድ በግብፅ ያሳለፉትን የባርነት ቀንበር ዘንግተው ዘወትር ወደ ኋላ መመለስ ይፈልጉ ነበር!

እኛ የነበረን የባርነት ሕይወት ብቻ ሳይሆን፥ የከንቱነት ሕይወትም ነበር። ጴጥሮስ «ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ. . .» (1፡18) በማለት የከንቱነትን ዘመን ይገልጸዋል። ይህንን በተለየ መልኩ በ 4፡1–4 ላይ ገልጾታል። እነዚህ ሰዎች፥ ከንቱና ኀዘንተኞች ሆነው ሳሉ፥ ሙሉና ደስተኞች እንደሆኑ ያስቡ ነበር። ያልዳኑ ሰዎች ዛሬ በጭፍን እውነተኛ ደስታቸውን በሌላ ነገር ተክተው ይኖራሉ።

በካናዳ በማገለግልበት ጊዜ፥ በመጀመሪያ የተለወጠች በኋላ ግን በመዋለል ዓለም ውስጥ የገባች ሴት አገኘሁ። ዓለም ለእርሷ ጊዜያዊ ደስታ የሚሰጣትና ሥጋዊ ፍላጎቷን የሚያሟላላት ነበር። አንድ ቀን ወደ ጭፈራ ቤት ለመሄድ መኪናዋን ስታሽከረክር በአጋጣሚ የክርስቲያን ሬድዮ ጣቢያ ከፈተች። ሰባኪው «አንዳንድ ሴቶች ከመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ይልቅ ስለ ጭፈራ ቤቶች ብዙ ታውቃላችሁ!» አለ። እነዚህ ቃላት ከጆሮዋ ጥልቅ አሉ። እግዚአብሔር ለልቧ ተናገራት፤ ወደ ቤቷም ተመለሰች፤ ከዚያን ጊዜ ጀምራ ሕይወቷ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሆነ። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሚኖር ኑሮ ከንቱና ትርጉም አልባ መሆኑንም ተመለከተች።

ጴጥሮስ እነርሱ ማን እንደነበሩ ብቻ ሳይሆን፥ ክርስቶስ ምን እንዳደረገላቸውም አሳስቧቸዋል። እኛን ለመዋጀትና ከኃጢአት ባርነት ለዘላለም ነፃ ለማውጣት የከበረ ደሙን አፈሰሰ። «መዋጀት» ማለት «ዋጋ ከፍሎ ነፃ ማውጣት» ማለት ነው። አንድ ባርያ በገንዘብ ነፃ

ሊወጣ ይችላል። በኃጢአቱ የጠፋን ሰው ግን በምንም ያህል ገንዘብ ቢሆን ነፃ ማውጣት አይቻልም። ሊዋጀን የሚችለው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

ጴጥሮስ የኢየሱስ ክርስቶስ የመከራው ምስክር ነው (5፡1)። በመሥዋዕትነት መሞቱንም በዚህ መልእክት ውስጥ ደጋግሞ ጠቅሶታል (2፡21፤ 3፡18፤ 4፡1፥ 13፤ 5፡1)። ክርስቶስን «በግ» ብሎ ሲጠራው አንባቢዎቹ ለጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የነበረውን ዛሬም ለእኛ እጅግ ጠቃሚ የሆነውን የብሉይ ኪዳንን ትምህርት እያስታወሳቸው ነበር። ይህ የ«መተካት» አስተምህሮ ነው። ኃጢአት የሌለበት ንጹሕ በኃጢአተኛው ፈንታ ሕይወቱን ይሰጣል።

የመሥዋዕት አስተምህሮ በዘፍጥረት 3 ላይ ይጀምራል። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ለማልበስ እንስሳትን በገደለበት ጊዜ፥ መሥዋዕት ተጀመረ። በይስሐቅ ፈንታ በግ ሞተለት (ዘፍ. 22፡13)። የፋሲካ በግ በእያንዳንዱ አይሁድ ቤት ታርዶ ነበር (ዘጸ. 12)። መሲሑ በኢሳይያስ 53 ላይ እንደ ንጹሕ በግ ቀርቧል። ይስሐቅ «በጉ የት አለ?» (ዘፍጥ. 22፡7) ብሎ ጠየቀ። መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ኢየሱስ አመልክቶ «እነሆ፥ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ » (ዮሐ. 1፡29) በማለት መልሶታል። በሰማይ የተዋጁትና መላእክት «በጉ ክብርና ምስጋና በረከትም ሊቀበል ይገባዋል» እያሉ ይዘምራሉ (ራእይ 5፡11–14)።

የኢየሱስ ክርስቶስ መሞት በአጋጣሚ የሆነ ነገር ሳይሆን፥ ዓለም ሳይፈጠር በእግዚአብሔር የተወሰነ መሆኑን ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ ላይ በግልጽ አስቀምጦታል (የሐዋ. 2፡23)። በሰው ልጆች አመለካከት ጌታ በጭካኔ ተገድሏል፥ በመለኮት አመለካከት ግን ሕይወቱን ለኃጢአተኞች ሰጥቷል (የሐዋ. 10፡17–18)። አሁን ግን ከሞት ተነሥቷል! በእርሱ የሚያምን ሁሉ ለዘላለም ይድናል። የክርስቶስን መሥዋዕትነት ስናስብ ለእግዚአብሔር በመታዘዝና በቅድስና ለክብሩ መኖር ይገባናል። አንድ ጊዜ ፍራንሲስ ሪድሌይ የተባለች ወይዘሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎ ከሚታይበት ሥዕል ሥር የሚከተለው ተጽፎበት አየች። «እኔ ለእናንተ ይህን አድርጌአለሁ። እናንተስ ለእኔ ምን አደረጋችሁልኝ?» ይላል። ወይዘሮዋ ወዲያውኑ አንድ ግጥም ጻፈች፤ ግጥሙ ጥሩ ስላልመሰላት ግን መልሳ እሳት ውስጥ ወረወረችው። በአጋጣሚ ወርቀቱ ብዙም በእሳቱ ሳይጎዳ ወጣና በኋላ አባቷ ስላበረታቷት ግጥሙ ታትሞ እንዲወጣ አደረገችው። እነሆ ዛሬ እኛ እንዘምረዋለን።

እኔ ለእናንተ ሕይወቴን ሰጠሁ

የከበረ ደሜን አፈሰስኩላችሁ

እናንተ እንድትድኑ፥ ከሞት እንድትነቁ

ሕይወቴን ለእናንተ ሰጠሁ

እናንተስ ለእኔ ምን ትሰጣላችሁ?

በእውነት ጥሩ ጥያቄ ነው! ለጌታ ትክክለኛ ምላሽ እንደምንሰጠው እርግጠኛ ነኝ።

*ተጨማሪ ማስታወሻ፡-* *ጴጥሮስ «የሚጠፋ» እና «የከበረ»* እንዲሁም «የሚጠፉ» እና «የማይጠፉ» የሚሉትን ቃላቶች ደጋግሞ እንደተጠቀመባቸው አስተውል። 1ኛ ጴጥሮስ 1፡4፥ 18፥23፤ 3፡4። የከበረ የሚለውን ቃል ደግሞ በ1ኛ ጴጥሮስ 1፡19፤ 2፡4፥ 6፡7፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1፡1፥4 ተጠቅሞበታል።

# 4

# የክርስቲያኖች አንድነት

## (1ኛ ጴጥሮስ 1፥22–2፥10)

በሕይወት ውስጥ ካሉ አሳዛኝ ገጠመኞች አንዱ፥ የእግዚአብሔር ሰዎችም የማይስማሙባቸው ጊዜዎች መኖራቸው ነው። በተስፋና በቅድስና የሚኖሩ ሰዎች ዘወትር ያለችግር ተስማምተው ሊኖሩ የሚችሉ ይመስላችሁ ይሆናል። ነገር ግን ይህ የማይሆንበትም ጊዜ አለ። በእግዚአብሔር መለኮታዊ እይታ አንድ አካል ብቻ ነው ያለው (ኤፌ. 4፥4–6 ይመልከቱ)። እኛ በሰብአዊ ዓይናችን የምንመለከተው ግን፥ ቤተ ክርስቲያን ተከፋፍላ አንዳንዴም በጦርነት ውስጥ ሆና ነው። በዚህ ዘመን መንፈሳዊ አንድነት በጣም ያስፈልገናል።

ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ውስጥ ትኩረት የሰጠው ለመንፈሳዊ አንድነት ነው። ይህንን አሳብ አራት ጠንካራ የቤተ ክርስቲያን ተምሳሌቶች በመጠቀም አስቀምጦታል።

## 1. የአንድ ቤተሰብ ልጆች ነን (1፥22–2፥3)

የዚህን እውነት ጽንሰ አሳብ ስታስተውሉ በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል አንድነትን ለመገንባትና ለመጠበቅ ትበረታታላችሁ።

*ሀ. ሁላችንም ከማይጠፋ ዘር ተወልደናል (1፥23–25)*። የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል መሆን የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ መንፈሳዊ ልደት ነው። ይህም የሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው (ዮሐ. 3፥1–16)። በሥጋ ለመወለድ ሁለት ወላጆች እንደሚያስፈልጉ ሁሉ በመንፈስም ለመወለድ ሁለት ወላጆች ያስፈልጋሉ፤ እነርሱም፦ የእግዚአብሔር መንፈስ (3፥5–6) እና የእግዚአብሔር ቃል (1፥23) ናቸው። አዲስ ልደት አዲስ ተፈጥሮ ይሰጠናል (2ኛ ጴጥ. 1፥4)፥ እንዲሁም አዲስ እና ሕያው ተስፋ ይሰጠናል (1ኛ ጴጥ. 1፥3)።

በመጀመሪያ የተወለድነው ከሥጋ ነው፤ ሥጋ ደግሞ የሚበሰብስ ነው። ከሥጋ የተወለደ ሁሉ መሞትና መበስበስ ተወስኖበታል። የሰው ልጅ ሥልጣኔ እንዳለ ሊቆይ የማይችለው፥ ጠፊ በሆነው ሰው ሥጋዊ ተፈጥሮ ላይ ስለተመሠረተ ነው። በፀደይ ወራት ፈክቶ እንደሚታይ አበባ የሰው ሥራ ስኬታማ መስሎ የሚታየው ለጊዜው ነው፤ ጥቂት ቆይቶ ግን ሟችና ፈራሽ ነው። በዘፍጥረት 11 ላይ ከተጠቀሰው ከባቢሎን ግንብ በራእይ 17 እና 18 ላይ እስከተጠቀሰችው «ታላቂቷ

ባቢሎን» ድረስ፤ የሰው ልጅ አንድ ለመሆን ያደረገው ሙከራ ሁሉ፥ ሳይሰካለት ቀርቷል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን አንድነት በመጀመሪያው ልደታችን በሥጋ ለመገንባት ብንሞክር አይሳካልንም። በአዲሱ ተፈጥሮአችን ኅብረታችንን ብንገነባ ግን ይከናወንልናል። በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ የሚኖረው አንድ መንፈስ ቅዱስ ነው (ሮሜ 8፡9)። የምንጠራውም አንዱን አባት ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡17)። መለኮታዊ ባሕሪውንም እንካፈላለን። የምናምነው ቃል አንድ ነው። ይህ ቃል ደግሞ የማይበሰብስ ወይም የማይጠፋ ነው። በአንድ ወንጌል አምነን ከአንድ መንፈስ ተወልደናል። ለዘላለም አንድ ካደረገን መንፈስ ጋር ሲወዳደር፥ የሚከፋፍሉን ውጫዊ ነገሮች ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም።

*ለ. አንድ ዓይነት ፍቅር እናሳያለን (1፡22)።* ጴጥሮስ ፍቅርን ለመግለጽ የተጠቀመው ሁለት ዓይነት ቃል ነው። አንደኛው «ፍላደልፊያ» የሚል ሲሆን «የወንድማማችን ፍቅር» የሚገልጽ ነው። ሌላው «አጋፔ» የሚል ሲሆን «የእግዚአብሔር ዓይነት መሥዋዕትነት የሚጠይቅ» ፍቅር ነው። ሁለቱም ዓይነት ፍቅር ያስፈልገናል። በጌታ ወንድም እና እኅት በመሆናችን የወንድማማችን ፍቅር መከፋፈል ያስፈልገናል። የእግዚአብሔር በመሆናችን ደግሞ ልዩነታችንን ሊያስወግድ የሚችለውን የእግዚአብሔር ዓይነቱን ፍቅር መካፈል ይኖርብናል። በተፈጥሮ ሁላችንም ራስ ወዳድ ነን። እግዚአብሔር ለእኛ ፍቅርን ለመስጠት ተአምር ሠርቷል። እውነትን በመንፈስ ስለታዘዝን እግዚአብሔር ነፍሳችንን አንጽቶ ፍቅሩን በልባችን አፈሰሰው (ሮሜ 5፡5)። ለወንድሞች ያለን ፍቅር በእውነት ከእግዚአብሔር ለመወለዳችን ማስረጃ ነው (1ኛ ዮሐ. 4፡7–21)። አሁን «የሚታዘዙ ልጆች ነን» (1ኛ ጴጥ. 1፡14)፤ ከእንግዲህ አሮጌ በሆነው ሥጋዊ መሻት መኖር የማንፈልግ ነን።

ሰዎች ከልብ ያልሆነ አፍአዊ ተራ ፍቅር ለማሳየት ሲሞክሩ ማየት በጣም ያሳዝናል። «አፉ ከቅቤ ይልቅ ለዘበ፥ በልቡ ግን ሰልፍ ነበር» [መዝ. (55)፡21]። ለወንድሞቻችን የምናሳየው ፍቅር ከእግዚአብሔር መንፈስ ያገኘነው ሊሆን ይገባል። እንደ ሬድዮ ስንፈልግ የምንከፍተውና የምንዘጋው ሳይሆን፥ ዘወትር በሕይወታችን የሚኖር ኃይል ነው።

ይህ ፍቅር መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን፥ *እውነተኛም* ነው። የምንወደው በንጹሕ ልብ ነው። ፍላጎታችን መስጠት እንጂ መቀበል አይደለም። በዚህ ዘመን ከሌላው የሚፈልጉትን ለማግኘት ሰውን

የማታለል ዘዴ «ስኬት በሥነ አእምሮ» የሚባል ነገር አለ። ፍቅራችን እውነተኛና ከንጹሕ ልብ የመነጨ ከሆነ፥ ሰዎችን ለራሳችን ትፍር አንጠቀምባቸውም።

ይህ ፍቅር *የሚተጋ* ፍቅር ነው። ስፖርተኛ ችሎታውን ለማዳበር በትጋት እንደሚለማመድ ሁሉ፥ ፍቅርም በትጋት የምንሠራውና የምንለማመደው ነገር ነው። የክርስቲያን ፍቅር ስሜት አይደለም፤ የፈቃድ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር ለእኛ እንደሚያደርግልን ለሌሎች ስናደርግ፥ ያኔ ፍቅርን እናሳያለን። እግዚአብሔር ይቅር እንደሚለን ሌሎችን ይቅር እንላለን። እግዚአብሔር ለእኛ መልካም እንደሆነ፥ እኛም ለሌሎች መልካም እንሆናለን። ይህ የፈቃድ ጉዳይ እንጂ ስሜት አይደለም። በፍቅር ውጤታማ ለመሆን አዘውትረን ልንለማመደው ይገባል።

ይህንን ስናደርግ ሁለት ግሩም ረዳቶች አሉን፥ እነርሱም፦ የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ናቸው። የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ያመንበትና የታዘዝነው እውነት የሚያሳድገንና ኃይልን የሚያስታጥቀንም ነው። *እውነትን መውደድና ወንድምን መጥላት አብረው መሄድ የማይችሉ ነገሮች ናቸው።* በሕይወታችን «የመንፈስን ፍሬዎች» እንድናፈራ የሚያደርገን የእግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን ከፍሬዎቹም የመጀመሪያው ፍቅር ነው (ገላ. 5፡22–23)። በእግዚአብሔር ቃልና (ቆላ. 3፡16) በእግዚአብሔር መንፈስ (ኤፌ. 5፡18) ስንሞላ፥ የእግዚአብሔርን ፍቅር በየዕለት ተዕለት ኑሮአችን እንገልጸዋለን።

*ሐ. አንድ ዓይነት ምግብ እንመገባለን (2፡1–3)።* የእግዚአብሔር ቃል ሕይወት አለው፤ ሕይወት ይሰጣል፤ ሕይወትን ይመግባል። አዲስ እንደተወለደ ሕፃን ቃሉን ልንራብ ይገባል! ያልተሸቃቀጠው ንጹሑ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ያሳድገናል። በልጅነቴ እኔ ወተት መጠጣት አልወድም፤ አባቴ ግን በቦርደን የወተት ኃብት ልማት ውስጥ ሠራተኛ ነበር። እናቴ እኔ ወተት እንድለምድላት፥ ለወተቱ ልዩ ጣዕም ለመስጠት የተለያዩ ቅመሞችን ትጨምርበት ነበር። አልተሳካላትም። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል የመመገብ ፍላጎት ሲያጡና በተለያዩ የአምልኮ ሥርዓቶች ረሃባቸውን ሲያስታግሱ ማየቱ በጣም ያሳዝናል። በእምነት ስናድግ ቃሉ ለሕፃናት ወተት፥ ለበሰሉት ደግሞ ጠንካራ ሥጋ መሆኑን እናውቃለን (ዕብ. 5፡11–14፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡1–4)። ቃሉ እንጀራ ነው (ማቴ. 4፡4)፥ ማርም ነው [መዝ. (119)፡103]።

አንዳንድ ጊዜ ልጆች ያልሆነ ነገር ስለሚመገቡ፥ የምግብ ፍላጎታቸው ይጠፋል። ጴጥሮስም አንባቢዎቹን ትክክለኛ ያልሆነ ልብና

ዝንባሌ መንፈሳዊ እድገታቸውንና ቃሉን የመመገብ ፍላጎታቸውን ስለሚገታ «አስወግዱት» ይላቸዋል። «ክፉ»ና «ተንኮለኞች» ሆነን ሳለ፥ በአስመሳይ የሸንገላ ቃላትና ተግባራት ማንነታችንን ለመሸፈን ስንሞክር «ግብዞች» እንሆናለን። ሁልጊዜ ለመጥፎ ድርጊት የሚያነሣሣው ምቀኝነት ነው፤ ምቀኝነት የሚገለጥበት አንድ መንገድ ደግሞ ሐሜተኝነት ነው። እነዚህ መጥፎ ዝንባሌዎችና ተግባራት በሕይወታችን ካሉ ንጹሕ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል የመመገብ ፍላጎት እናጣለን። ቃሉን መመገብ ካቆምን ደግሞ እድገታችን ይቆማል፤ ከጌታም የምንቀበለውን ጸጋ እናጣለን። ክርስቲያኖች በቃሉ ሲያድጉ አስታራቂዎችና ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርጉ እንጂ ችግር ፈጣሪዎች አይሆኑም።

## 2. የአንድ ሕንፃ ድንጋዮች ነን (2:4-8)

አንድ አዳኝ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ አንድ መንፈሳዊ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን አለች። ኢየሱስ ክርስቶስ ሕንፃውን በአንድነት የሚያጋጥም የማዕዘን ራስ ነው (ኤፌ. 2:20)። እርስ በርሳችን ብንስማማም ባንስማማም፥ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ የሕንፃው ድንጋዮች ነን።

ጴጥሮስ ኢየሱስ ክርስቶስን ሲገልጸው፥ ሞትን አሸንፎ በድል ስለተነሣ *ሕያው ድንጋይ* ነው፤ በአባቱ *የተመረጠና የከበረ ድንጋይ* ይለዋል። ጴጥሮስ ኢሳይያስ 28:16ን እና መዝሙር (118):22ን በመጥቀስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰዎች ዘንድ የተናቀ ቢሆንም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ከብሯል። አይሁዶች የሚጠብቁት ዓይነት መሢሕ ስላልሆነላቸው ተሰናከሉበት። ኢየሱስ ክርስቶስ ከአይሁድ መሪዎች ጋር ሲከራከር፥ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጠቅሶአል [ማቴ. 21:42 እና መዝ. (118):22ን ይመልከቱ]።

የአይሁዶች መሰነካከል ምክንያቱ ለቃሉ መገዛትን አሻፈረኝ ማለታቸው ነው (1ኛ ጴጥ. 2:8)። ቃሉን አምነውና ታዘው ቢሆን ኖሮ፥ መሢሑን ተቀብለው በዳኑ ነበር (1ኛ ጴጥ. 2:8)። ዛሬም ቢሆን ብዙዎች በክርስቶስና በመስቀሉ ይሰናከላሉ፤ በእርሱ የሚያምኑ ግን አያፍሩም (1ኛ ቆሮ. 1:18)።

ኢየሱስ ስለ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ ጊዜ የተናገረው ከሕንፃ ጋር በማወዳደር ነው፤ «ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ» (ማቴ. 16:18)። አማኞች በሕንፃው ውስጥ ያሉ ሕያዋን ድንጋዮች ናቸው። አንድ ሰው ወደ ጌታ ሲመጣ ሌላ አንድ ድንጋይ ከኃጢአት ጉድጓድ ውስጥ ተስቦ ወጥቶ በእግዚአብሔር የጸጋ ሲሚንቶ በሕንፃው ውስጥ ገብቶ ይሠራል። ቤተ ክርስቲያን ቁልል መስላ ትታየን ይሆናል፤

እግዚአብሔር ግን አጠቃላይ የተሟላ መዋቅሯንና በማደግ ላይ መሆኗን ነው የሚያየው (ኤፌ. 2፡19-22)። የመንፈስ ማደሪያ የሆነችው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በመሆናችን ምን ያህል ዕድለኞች ነን!

ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈው በተለያዩ አምስት አውራጃዎች ለሚኖሩ አማኞች ቢሆንም ሁሉም የአንድ «መንፈሳዊ ቤት» አባል መሆናቸውን ይነግራቸዋል። የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነት በአጥቢያና በቤት ከሚካሄዱ ስብሰባዎችና የአንድነት ጊዜዎች የሚያልፍና የሚበልጥ ነው። የክርስቶስ በመሆናችን አንዳችን የሌላው ነን። ይህንን ስንል ግን የተለያዩ ቤተ እምነቶችና አስተምህሮቶች አይኖሩም ማለት አይደለም። እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ መማር ይኖርበታል። ልዩነታችን በክርስቶስ ያገኘነውን መንፈሳዊ ኅብረታችንን እንዲያጠፋው መፍቀድ የለብንም። ላለመስማማት መስማማት የሚያስችል ብስለት ይኑረን።

በሚችጋን ያለ አንድ ሕንፃ ተቋራጭ የሚገነባው ሕንፃ የመጀመሪያ ፎቅ በሰላም ተጠናቀቀ። ሁለተኛውን ፎቅ ሲጀምሩ ግን ከችግር በስተቀር የተረፈው ነገር አልነበረም። ምክንያቱም ከተከማቹት የሕንፃ መሥሪያ ጥሬ ዕቃዎች መካከል ለሕንፃው በትክክል የሚስማማ በመጥፋቱ ነበር። በኋላ ግን ለዚህ ሁሉ ችግር መንሥኤ የሆነው በሁለት የተለያዩ የሕንፃ ዲዛይኖች እየተሠራ በመቆየቱ መሆኑ ተረጋገጠ። ከዚያም የቀድሞውን አሮጌ ዲዛይን አስወግደው ያማረ ሕንፃ ሠሩ።

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች የተሳሳተ ቢጋር ሲከተሉ የቤተ ክርስቲያንን እድገት ይገታሉ። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሲሠራ ሠራተኞቹ ሁሉንም ነገር በቢጋሩ መሠረት ነበር የሠሩት (1ኛ ነገሥ. 6፡7)። ሁላችንም እግዚአብሔር በቃሉ ለሕይወታችን የሰጠውን መመሪያ ብንከተል ቤተ ክርስቲያንን በመስማማትና በአንድነት ለእግዚአብሔር ክብር እናንጽ ነበር።

## 3. የአንድ ቤተ መቅደስ ካሕናት ነን (2፡5÷9)

እኛ «ቅዱስ ካህናት» እና «የንጉሥ ካህናት» ነን። ይህ ጌታ በሰማይ ሊቀ ካህን ከመሆኑ ጋር አብሮ ይሄዳል። ክርስቶስ ንጉሥም ካህንም ነው (ዕብ. 7)። በብሉይ ኪዳን ዘመን በእስራኤል ውስጥ ካህን ሆኖ ያገለገለ አንድም ንጉሥ አልነበረም። አንድ ጊዜ የክህነት አገልግሎትን ለመፈጸም የሞከረውም ተቀስፎአል (2ኛ ዜና 26፡16-21)። የጌታችን ሰማያዊ ዙፋን እርሱን በማገልገልና በፈቃዱ በመኖር የሚያስፈልገንን ሁሉ ጠይቀን የምናገኝበት የጸጋ ዙፋን ነው (ዕብ. 4፡14-16)።

በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ካህናት ነበሯቸው። አሁን ግን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ራሳቸው ካህናት ናቸው። እያንዳንዱ አማኝ በእግዚአብሔር ፊት የመቅረብ መብት አለው (ዕብ. 10፡19–25)። በምድር ላይ ባለ በማንም ሰው በኩል ወደ እግዚአብሔር አንቀርብም፥ መካከለኛ በሆነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ካልሆነ በስተቀር (1ኛ ጢሞ. 2፡1–8)። እርሱ ሕያው ሆኖ በክብር ስለሚኖር እና ስለ እኛ ስለሚማልድ እኛ እንደ ቅዱስ ካህናት ማገልገል እንችላለን።

ስለዚህ በእግዚአብሔር መቅደስ ካህናት እንዳሉ ሰዎች መኖር ይገባናል። በእውነቱ ካህን ሆኖ ማገልገል ትልቅ ዕድል ነው። በእስራኤል ከሌዊ ወገን የተወለደ ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው በመሠዊያው ላይ ማገልገል፥ ወደ መቅደሱ አደባባይ ወይም ወደ ቅዱሳኑ መግባት አይችልም ነበር። እያንዳንዱ ካህን እና ሌዋዊ የሚያከናውኑት የተለያዩ ተግባራት ቢኖራቸውም፥ ሁሉም በሊቀ ካህኑ ሥር በአንድነት ሆነው ለእግዚአብሔር ክብር ያገለግሉ ነበር። እኛም እንደ እግዚአብሔር ካህናት በሊቀ ካህናችን ምሪት በአንድነት ማገልገል ይኖርብናል። ለክብሩ የምናደርገው እያንዳንዱ ሥራ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው አገልግሎታችን ነው።

ጴጥሮስ «መንፈሳዊ መሥዋዕቶች» በማቅረብ የተሰጠንን ዕድል ጠቅሶታል። የብሉይ ኪዳን አማኞች እንዳደረጉት እንስሳትን መሥዋዕት አድርገን አናቀርብም። ለእግዚአብሔር የምናቀርባቸው ሌሎች መሥዋዕቶች ግን አሉን። *ሰውነታችንን* ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርገን እናቀርባለን (ሮሜ 12፡1–2)፤ *የምስጋናን መሥዋዕት* በማቅረብ (ዕብ. 13፡15)፥ *ለሌሎች በማካፈል* (ዕብ. 13፡16) መሥዋዕትን እናቀርባለን። ለመንፈሳዊ ሥራ ገንዘባችንን እና ሌሎች ነገሮችን ስንሰጥ ይህም መንፈሳዊ መሥዋዕት ነው (ፊልጵ. 4፡10–20)። ወደ ጌታ የምናመጣቸው *ሰዎችም* የክብሩ መሥዋዕት ናቸው (ሮሜ 15፡16)። እነዚህን ሁሉ መሥዋዕቶች በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እናቀርባቸዋለን። ምክንያቱም እንደ መንፈሳዊ መሥዋዕት ተቀባይነት የሚያገኙት በእርሱ በኩል ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን «የመንግሥት ካህናት» (ዘጸ. 19፡6) ሆነው በዙሪያቸው ላሉት ሕዝቦች እግዚአብሔርን የመፍራት አርአያ እንዲሆኑ ፈልጎ ነበር። እስራኤላውያን ግን ለሌሎች አሕዛብ መልካም ምሳሌ በመሆን ፈንታ የአሕዛብን ልማድ ወረሱ። ጣዖት በማምለካቸው እግዚአብሔር ደጋግሞ ቢቀጣቸውም እነርሱ ግን በኃጢአታቸው ጸኑ። ዛሬ እስራኤል ቤተ መቅደስም ካህንም የላትም።

እንደ እግዚአብሔር ካህናት በዓለም ላይ ያለንን የተለየ ቦታ መጠበቅ ያስፈልገናል። መለየት ማለት ግን መገለል ማለት አይደለም፤ በኃጢአት ሳይረከሱ ዓለም የምትፈልግብንን አርአያነትና ምስክርነት ማሳየት ነው።

እያንዳንዱ አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘቱና መንፈሳዊ መሥዋዕት ማቅረቡ እራስ ወዳድና «ግለኛ» እንዲሆን ሊያበረታታው አይገባም። ሁላችንም አንዱን ሊቀ ካህን በአንድ መቅደስ ውስጥ የምናገለግል ካህናት ነን። አንድ ሊቀ ካህንና ሰማያዊ መካከለኛ መኖሩ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለውን አንድነት ያመለክታል። ከእግዚአብሔር ጋር በግል የምናደርገው ጉዞ ከሌሎች ክርስቲያን ወገኖቻችን ጋር ያለንን ኅብረት ቸል እንድንል ወይም እንድንተው ሊያደርገን አይገባም።

ብዙ የማኅበረሰብ ሳይንቲስቶች «ውስብስቡ እኔ» በዘመናዊው ማኅበረሰብ ውስጥ በሚል ዙሪያ መጻሕፍትን ጽፈዋል። በዚህ ዘመን ያለው ትኩረት ለራስ በማሰብ ሌሎችን መርሳት ነው። እንደተመለከትኩት ከሆነ፥ ይህ አመለካከት ወደ ቤተ ክርስቲያንም ዘልቆ እየገባ ነው። ብዙ ዘመናዊ የቤተ ክርስቲያን ዝማሬዎች የሚያተኩሩት በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ላይ ሳይሆን፥ በግል ሕይወት ላይ ነው። ብዙ መጻሕፍትና የስብከት መልእክቶችም ሁሉንም አካል ማገልገል ቸል ብለው ትኩረታቸው በግል ልምምድ ላይ ሆኗል። ሌሎችን ለመርዳት እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ማሰብ እንዳለበት አውቃለሁ፥ ነገር ግን ሚዛናዊነት ሊኖር ይገባል።

## 4. የአንድ አገር ዜጎች ነን (2፡9–10)

በዚህ ክፍል ቤተ ክርስቲያን የተገለጸችበት አገላለጽ በዘጸአት 19፡5–6 እና በዘዳግም 7፡6 ላይ እስራኤል ከተገለጸችበት ጋር ይመሳሰላል። በማይታዘዙት የእስራኤል ሕዝቦች ፈንታ ዛሬ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተመረጡና ቅዱስ ሕዝብ ናቸው። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን ጉዳይ ጨርሷል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን ቃል ኪዳንና ተስፋ ጠብቆ የተስፋውን መንግሥት ይመሠርታል ብዬ አምናለሁ። ይህ ማለት ግን የቤተ ክርስቲያን ቦታ ቀድሞ እስራኤል በእግዚአብሔርና በዓለም ዘንድ እንደነበራት ዓይነት አይደለም።

እኛ *የተመረጠ ትውልድ* ነን፤ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ጸጋ ያሳያል። እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጠው ስለወደዳቸው እንጂ ታላቅ ሕዝብ ስለነበሩ አይደለም (ዘዳ. 7፡7–8)። እግዚአብሔር

በጸጋውና በፍቅሩ ብቻ መርጦናል። «እኔ መርጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም» (ዮሐ. 15፡16)።

እኛ *ቅዱስ ሕዝብ* ነን። የእግዚአብሔር ብቻ ለመሆን ተለይተናል። ዜግነታችንም ሰማያዊ ነው (ፊልጵ. 3፡20)። ስለዚህ ሰማያዊ የሆኑ ሕጎችን በመታዘዝ፥ ሰማያዊ የሆነውን ጌታችንን እናስደስታለን። እስራኤል ቅዱስ ሕዝብ መሆኗን ዘንግታ ልዩ የሚያደርጋትን ግድግዳ ማፈራረስ ጀመረች። እግዚአብሔር «በተቀደሰውና ባልተቀደሰው በእርኩሱና በንጹሑም» መካከል እንዲለዩ አዟቸው ነበር (ዘሌ. 10፡10)። እነርሱ ግን ልዩነቱን ቸል በማለት ለእግዚአብሔር አልታዘዙም።

እኛ *የእግዚአብሔር ሕዝቦች* ነን። ደኅንነት ባላገኘንበት ጊዜ፥ የሰይጣንና የዓለም እንጂ የእግዚአሔር ሕዝቦች አልነበርንም (ኤፌ. 2፡1–3፥ 11–19)። አሁን ግን በክርስቶስ በማመናችን የእግዚአብሔር ሕዝብ ወገኖች ሆነናል። እግዚአብሔር በገዛ ልጁ ደም ስለገዛን (የሐዋ. ሥራ 20፡28) «ለርስቱ የተለየን ሕዝቦች ነን።»

እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች አንድ ትልቅ ኃላፊነት ይዘዋል፤ እርሱም ለጠፊው ዓለም የእግዚአብሔርን በጎነት መግለጥ ነው። «እንድትነግሩ» ማለት «እንድታስተዋውቁ» ማለት ነው። ዓለም በጨለማ ውስጥ በመሆኗ ሰዎች የእግዚአብሔርን ትልቅነት አያውቁትም። ስለዚህ ታላቅነቱን በሕይወታችን ሊያዩት ይገባል። እያንዳንዱ ሰማያዊ ዜጋ የእግዚአብሔር ባሕርይና የክርስቲያኖች በረከት ሕያው «ማስታወቂያ» ነው። እግዚአብሔር በጸጋው «ወደ ሚደነቅ ብርሃን» ጠርቶናል፥ ይህን ብርሃን ደግሞ በኑሮአችን ልናንጸባርቀው ይገባል።

ምሕረትን ያገኘነው ከእግዚአብሔር ነው። በምሕረቱ ባይሆን ኖሮ፥ ጠፍተን ወደ ዘላለም ፍርድ ባመራን ነበር። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ያዳናቸው እንዲያገለግሉትና እንዲያከብሩት ለመሆኑ ደጋግሞ ያስታውሳቸው ነበር። እነርሱ ግን ይህን ሁሉ ፈጥነው በመዘንጋት፥ ወደ ኃጢአት መንገዳቸው ይመለሱ ነበር። እኛ በእግዚአብሔር ምሕረት የተመረጡ ሕዝቦች ነን። መመረጣችንም ለእርሱ ታማኝ ሊያደርገን ይገባል።

በጠላት ግዛት ውስጥ ስለምንኖር ጠላት ደግሞ እኛን የሚያጠቃበት አጋጣሚ ይፈልጋል። እንደ ሰማያዊ ዜጋ አንድ እንሁን። በአንድነት የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት የሠራውን ነገር ለዓለም ማሳየት አለብን። ይህን በምጽፍበት ጊዜ አንድ ጋዜጣ ከአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጋር አብረው በሚሠሩ ሰዎች መካከል ያለውን

አለመግባባት ይዘግብ ነበር። እነዚህ ሰዎች በመፈረካከሳቸው ሕዝቡ ተረብሾ ነበር። ሰማያዊ ዜግነት ያላቸው የእግዚአብሔር ባሪያዎች እርስ በርሳቸው ሲጣሉ ሲያዩ፥ የማያምኑት ሰዎች ምን ሊያስቡ ይችሉ ይሆን?

እነዚህ አራት ሥዕላዊ መግለጫዎች በአንድነትና በመስማማት ላይ አተኩረዋል። ሁላችንም የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ነን፤ አንድ መለኮታዊ ባሕርይም ተካፍለናል። በአንድ ሕንፃ ውስጥ የተጋጠምን ድንጋዮችና በአንድ መቅደስ የምናገለግል ካህናት ነን። ሁላችንም የሰማያዊ አገር ዜጎች ነን። የዚህ አንድነት ምንጭና ማዕከል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ትኩረታችንን እና ፍቅራችንን በእርሱ ላይ ካደረግን አብረን መጓዝና መሥራት እንችላለን። በራሳችን ላይ ብናተኩር ግን የምናተርፈው መከፋፈልን ብቻ ነው።

አንድነት ልዩነትን አያጠፋም። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሁሉም ልጆች አንድ ዓይነት አይደሉም። በሕንፃ ውስጥ ያሉት ድንጋዮችም እንደዚሁ አንድ ዓይነት አይደሉም። ለነገሩ ለቤተሰብም ሆነ ለሕንፃው ውበት የሚሰጠው ልዩነት ነው። ልዩነት የለም ማለት *አንድነት* አለ ማለት አይደለም። ይልቁንስ አንድ ዓይነት ነገር ብቻ መሆኑ አሰልቺ ይሆናል። ዘማሪዎች በአንድነት መዘመራቸው ጥሩ ቢሆንም፥ እኔ የማደንቀው ግን በስምምነት መዘመራቸውን ነው።

ክርስቲያኖች ልዩነታቸው ተጠብቆ አብረው መሄድ ይችላሉ። «አንድ እምነት» ያላቸውና «አንድ ጌታ» ለማክበር የሚሹ በፍቅር አብረው መጓዝ ይችላሉ (ኤፌ. 4፡1-6)። እግዚአብሔር ለተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ሊጠራን እናም የተለያዩ አሠራሮችን ልንጠቀም እንችላለን፤ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን በፍቅርና በአንድነት ለዓለም መመስከር እንችላለን።

አንድ ቀን ሁላችንም በሰማይ እንሆናለን (ዮሐ. 17፡24)። ስለዚህ መዋደድን ከዚሁ ጀምረን መማር አለብን!

ቅዱስ አገስቲን «መሠረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ አንድነት፥ መሠረታዊ ባልሆኑ እና የግል ውሳኔን በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ነጻነት፥ በሁሉም ነገር ቸርነት።» ብሏል።

## 5

# የሚያይህ አለ!

(1ኛ ጴጥሮስ 2፡11–25)

መካከለኛ የሆነው የመልእክቱ ክፍል (2፡11–3፡12) በአማኝ ሕይወት ውስጥ ስለሚሆን መታዘዝ አጽንዖት ይሰጣል። ሕግ የለሽነትና ራስ ወዳድነት በሰፈነበት በዚህ ዘመን ይህ ተወዳጅ ርእስ ባይሆንም አስፈላጊ ነው። ጴጥሮስ መገዛት የሚለውን ጭብጥ ከአማኞች የዜግነት ሕይወት (2፡11–17)፥ ከሥራቸው ጋር (2፡18–25)፥ ከትዳራቸው ጋር (3፡1–7)፤ ከአማኞች ጋር ከሚኖራቸው ኅብረት ጋር (3፡8–12) ያዛምደዋል።

መገዛት ባርነት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በሕይወታችን ያለውን ሥልጣን መቀበል ነው። እግዚአብሔር ቤተሰብን፥ መንግሥትን፥ ቤተ ክርስቲያንን ስለመሠረተ እነዚህ ተቋማት እንዴት መመራት እንዳለባቸው የመንገር መብት አለው። እግዚአብሔር እያንዳንዳችን በሥልጣናችን እንድንጠቀም ቢፈልግም፥ በሥልጣናችን ከመጠቀማችን በፊት ከሥልጣን ሥር መገዛት አለብን። ሰይጣን ለአዳምና ለሔዋን ሥልጣን የሌለውን ነጻነት ስለሰጣቸው፥ የነበራቸውን ሥልጣንና ነጻነት አጥተውት አረፉ። አባካኙ ልጅ የአባቱን ውርስ ካገኘ በኋላ ነጻነቱን አጣ።

ጴጥሮስ አንባቢዎቹ ለእግዚአብሔር ሥልጣን እየተገዙ የተሰጠና ታዛዥ የክርስትና ሕይወት የሚኖሩበትን ሦስት አነቃቂ ምክንያቶች ያሳያቸዋል።

## 1. ለጠፋት ሲባል (2፡11–12)

እንደ ክርስቲያን፥ ማንነታችንን ደጋግመን ማስታወስ አለብን፤ ጴጥሮስም በቁጥር 11 ማንነታችንን ያስታውሰናል። እኛ የእግዚአብሔር ውድ ልጆች ነን። በሁለቱ መልእክቶቹ ውስጥ ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹ ስምንት ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ነግሯቸዋል (1ኛ ጴጥ. 2፡11፤4፡12፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡7፤ 3፡1፥8፥14–15፥17)። እግዚአብሔር የወደደን «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ባለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንጂ እኛ በራሳችን ምንም ሊወደድ የሚችል ነገር የለንም። በክርስቶስ በማመናችን «በውድ ልጁ» በኩል ተቀበለን (ኤፌ. 1፡6)።

እግዚአብሔርን በማይፈራ ዓለም ውስጥ በቅድስና ለመኖር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለን «የፍቅር ኅብረት» በቂ ምክንያት ነው።

እርሱ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» ብሏል (ዮሐ. 14፡15)። የምንታዘዘው ግዴታ ስለሆነብን ሳይሆን፥ ጌታን ስለምንወደው ነው። ጌታችን «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል» (ዮሐ. 14፡23) ብሏል።

እኛ ለእግዚአብሔር የተወደዱ ልጆች ብቻ ሳንሆን፥ የሰማያዊ አገር ዜጎችና በዚህች ምድርም እንግዶችና መጻተኞች ነን። እንደ ቀደሙት አባቶቻችን ወደ ሰማያዊቷ አገር እየተጓዝን ሳለ፥ በዚህች ምድር ያለን ሕይወት ጊዜያዊ ነው (ዕብ. 11፡8−16)። በባዕድ አገር ኖረን ከሆነ፥ የአገሪቱ ዜጎች እንዴት የጎሪጥ እንደሚመለከቷችሁ ታውቃላችሁ። እውነቱን ለመናገር ከሆነ፥ በአገራችን ለሚኖሩ የውጭ አገር ዜጎች ያለን አመለካከት ትችት የተሞላበት ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት በገፍ የተሸጠው «የተከፋው አሜሪካዊ» የተሰኘው ልብ ወለድ መጽሐፍ አንድ አሜሪካዊ የአንድ የውጭ ዜጋን ፍላጎት በማሟላትና ከአሜሪካዊ አቻዎቹም ጋር ያለውን ኅብረት ለመጠበቅ ቢሞክርም መጥፎ አጋጣሚ ሆኖበት አሜሪካውያን ጓደኞቹ ሊገነዘቡት አለመቻላቸውን የሚገልጽ ታሪክ ነበር።

*ወታደሮች ስለሆንን፥ በመንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ እንሳተፋለን።* ክፉ ምኞት እየተቃወመ ሊያሸንፈን ይፈልጋል (ገላ. 5፡16−26ን ይመልከቱ)። ጦርነታችን በዙሪያችን ካሉ ሰዎች ጋር ሳይሆን በውስጣችን ካሉ ፍላጎቶች ጋር ነው። ዲ.ኤል. ሙዲ «ከማውቀው ከማንም ሰው በላይ የሚያስቸግረኝ ዲ.ኤል. ሙዲ ነው» ብሏል። በሥጋ ምኞት የምንገዛ ከሆነ፥ በዙሪያችን እንዳሉት እንደማያምኑት መኖር እንጀምራለን፤ ይህ ደግሞ ምስክርነታችንን ያጎድፈዋል። «ጦርነት» የሚለው ቃል «ወታደራዊ ዘመቻ» ከሚለው አሳብ ጋር ይገናኛል። በኃጢአት የምንኖር ከሆነ፥ በአንድም ጦርነት ላይ ድል አንቀዳጅም! ጦርነቱ የማያቋርጥ ስለሆነ ራሳችንን እንጠብቅ። ከሁሉም በላይ እኛ በማያምኑት ሰዎች ምስክሮች ነን። «አሕዛብ» የሚለው ቃል ስለ «ዘር» አይናገርም «ያልዳኑ ሰዎች» ከሚለው ሐረግ ጋር ተመሣሣይነት አለው (1ኛ ቆሮ. 5፡1፤ 12፡2፤ 3ኛ ዮሐ. 7)። የማያምኑ ሰዎች ይከታተሉናል፤ ያሙናል፥ ወንጌልን የሚቃወሙበትን ምክንያት ከእኛ ያፈላልጋሉ (1ኛ ጴጥ. 3፡16፤ 4፡4)።

*ለጠፉት ሰዎች የምንመሰክር ከሆነ፥* አኗኗራችን እውነተኛ ሊሆን ይገባል። ይህ ዓለም እውነትን ከመናገርና ትክክለኛውን ነገር ከመሥራት ያለፈ የውበትንና የአድናቆት አሳብም የያዘ ነው።

በከንፈራችን ብቻ አንመሰክርም። «ንግግራችን» በ«ኑሮአችን» ሊደገፍ ይገባል። በማያምኑት ዘንድ ክርስቶስና ወንጌሉ እንዲነቀፍ የሚያደርግ አንዳች ነገር በባሕርያችን ሊኖር አይገባም። መልካም ሥራዎቻችን መልካም ቃላቶቻችንን የሚደግፉ ይሁኑ። ይህ ኢየሱስ

በማቴዎስ 5፥16 ላይ የተናገረውና በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፈው እውነት ነው።

ከሠላሳ ዓመታት በላይ በሚሆነው አገልግሎቴ የክርስቲያኖች የተቀደሰ ሕይወትና ፍቅር የተሞላበት ምስክርነት በማያምኑት ላይ ያለውን በጎ ተጽዕኖ አይቻለሁ። በሌላ መልኩ ደግሞ በአፋቸው እናምናለን በሚሉ ሕይወታቸው ግን በማይመሰክር ሰዎች ተሰናክለው የጠፉትን አንዳንድ ሰዎች በቅሬታ አስታውሳቸዋለሁ።

ጴጥሮስ አንባቢዎቹን እግዚአብሔር አንድ ቀን ሊጎበኛቸውና ሊያድናቸው ስለሚችል፥ ለማያምኑት ሰዎች በቃልና በሥራ ምስክር እንዲሆኑ ያበረታታቸዋል። «የመጎብኘት ቀን» ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመለስ ምላስ ሁሉ ጌታ መሆኑን የሚመሰክርበት ቀን ነው። እኔ እንደማስበው ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ውስጥ የጠቀሰው «መጎብኘት» እግዚአብሔር ያልዳኑትን ሰዎች በመጎብኘት በጸጋው የሚያድንበትን ቀን ነው።

ይህ ቃል በዚህ መልኩ በሉቃስ 19፥44 ላይ ተጠቅሷል። ሰዎች በክርስቶስ ሲያምኑ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፤ ያከብሩታልም። ምክንያቱም አስቸጋሪዎች በሆኑበት ጊዜ እንኳን ሳይቀር፥ በታማኝነት ስለመሰከርንላቸው ነው።

በ1805 በበጋ ወራት ብዙ የሕንድ የጎሳ አለቆችና ጦረኞች በኒውዮርክ ቡፋሎ ክሪክ በተካሄደው ጉባኤ ላይ የቦስተን ሚሽነሪ ሚስተር ክራም የሚያቀርቡትን ክርስቲያናዊ መልእክት ለመካፈል ተሰበሰቡ። ከስብከቱ በኋላ ሬድ ጃኬት ከተባለ የሕንዶች ዋነኛ የጎሣ አለቃ የሚከተለው ምላሽ ተሰጠ፤ «ወንድሞቼ ሆይ፥ ታላቁ መንፈስ የሚመለከበትና የሚገለገልበት ያለው አንድ መንገድ ብቻ ነው ብላችኋል። ያለውስ ኃይማኖት አንድ ብቻ ከሆነ እናንተ ነጮች እንደዚህ የምትለያዩት ለምንድን ነው? ሁላችሁም አንድ መጽሐፍ እስካነበባችሁ ድረስ ለምንድን ነው የማትስማሙት?» በመቀጠልም «ወንድሞቼ ሆይ፥ በዚህ ቦታ ላይ ለነጮች እንደምትሰብኩ ተነግሮናል። እነዚህ ሰዎች ጎረቤቶቻችን ናቸው፥ እንቀራረባለንም። የእናንተ ስብከት በእነርሱ ሕይወት ምን ዓይነት ለውጥ እንደሚያመጣ ጥቂት ጊዜ ቆይተን እናያለን። ስብከታችሁ መልካም ሰዎች፥ ታማኞችና ሕንዶችን የማያታልሉ ካደረጋቸው፥ እናንተ ያላችሁትን እንደገና ተመልሰን እናስብበታለን።»

## 2. ለእግዚአብሔር ስንል (2፥13–17)

በእርግጥ፥ የምናደርገው ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርና ለመንግሥቱ መስፋት ሊሆን ይገባል! ጴጥሮስ ክርስቲያኖች በኅብረተሰቡ ውስጥ

የክርስቶስ ወኪል መሆናቸውን ለማሳየት ጥሯል። «የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማስተዋወቅ» የእኛ ኃላፊነት ነው (1ኛ ጴጥ. 2፡9)። ከመንግሥትም ሆነ በሥልጣን ላይ ካሉ ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነትም ጌታን እናስተዋውቃለን።

እንደ ክርስቲያን ዜጋ በሰው አስተዳደር ውስጥ ላለ ሥልጣን መገዛት አለብን። «መሾም» ተብሎ የተተረጎመው ቃል የሚያመለክተው «የተቋምን» መኖር ወይም መፈጠር ነው። ይህ ሕጉን በተናጠል ሳይሆን፥ ሕግ አርቃቂውን እና አስፈጻሚውን አካል ነው የሚያመለክተው። ለተቋሙ እየተገዙ ሕጎችን አለመታዘዝ ይቻላል።

ለምሳሌ ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ ለንጉሡ የአመጋገብ ሥርዓት አልታዘዙም። ለሕጉ አንታዘዝም ሲሉ ግን ንጉሡን እና ባለሥልጣናቱን በማክበር ነው (ዳን. 1)። ዐመጸኞች አልነበሩም፤ ኃላፊውን ላለማሳፈርና ችግር ውስጥ ላለመጣል ተጠንቅቀው ነበር። በአቋማቸው በመጽናት እግዚአብሔርን ሲያከብሩ የንጉሡንም ሥልጣን አክብረዋል።

ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያት ከበዓለ ኀምሳ በኋላ ተመሳሳይ ችግር ገጥሟቸዋል (የሐዋ. ሥራ 4–5)። የአይሁዶች ጉባኤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዳይሰብኩ ቢያዛቸውም ጴጥሮስና ጓደኞቹ ግን ለመታዘዝ እምቢ አሉ (የሐዋ. ሥራ 4፡19፤ 5፡29)። እነ ጴጥሮስ ሳያምጹና የጉባኤውን ሥልጣን ሳያቃልሉ ምንም እንኳን የወንጌል ተቃዋሚዎች ቢሆኑም ለመሪዎቹ ክብር በማሳየትና ለተቋሙ በመገዛት ስብከት አቁሙ የሚለውን ትእዛዝ ተቃወሙ።

ግለሰቦች ሊከበሩ የማይችሉ ቢሆኑም እንኳን ሥልጣናቸውን እናከብር። በምንችለው ሁሉ ከመንግሥት ጋር እንተባበራለን፥ ለሕጉም እንታዘዛለን። ሕጉ ግን ሕሊናችንን ጥለን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳንታዘዝ እንዲያደርገን መፍቀድ የለብንም። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ የማያስተውሉ ክርስቲያኖች ይህንን ልዩነት ለግጭትና ለቅራኔ ምክንያት ያደርጉታል። በየስብከቶቻቸውም «ነጻነት» እና «ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ይለያዩ» የሚል ጩኸት ይሰማበታል።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ለመሥራት ከፈለገች መከተል የሚገባት ሕጋዊ አሠራር አለ። (በብዙ የግንባታ ሥራ ዕቅዶች ውስጥ ስላለፍኩ አውቀዋለሁ!) መንግሥት በስብከት መድረክ ላይ ወይም በሥራ ስብሰባዎች ላይ ጣልቃ የመግባት መብት ባይኖረውም፥ ከአሠራርና ከደኅንነት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጉዳዮች የመቆጣጠር ሙሉ መብት አለው። ሕጉ የመግቢያ በሮችን ቁጥር ቢወስን፥ የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያዎች፥ ለአደጋ ጊዜ የሚሆኑ መብራቶች በግንባታው ውስጥ እንዲካተቱ ቢጠይቅ፥ ቤተ ክርስቲያን መስማማት አለባት።

መንግሥት ሕግ ሲያረቅ ማሳደዱ አይደለም። ቤተ ክርስቲያንም ለዚያ ሕግ ስትገዛ በእምነቷ ላይ ማመቻመቿ አይደለም። ግን አንዳንድ ያለቅጥ ቀናተኛ የሆኑ ቅዱሳን በዚህ ጉዳይ ላይ ባላቸው አመለካከትና ድርጊት የጌታን ስም ያቃልላሉ።

ጴጥሮስ ልናከብራቸው የሚገቡንን ባለሥልጣናት ጠቅሷል። «ንጉሥ»ን ወይም ዐፄ ገዥ፥በዲሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ ውስጥ ደግሞ ፕሬዚዳንትንና ጠቅላይ ሚኒስትርን ማክበር ይገባናል። ጴጥሮስ የሮማን መንግሥት አልተቻም፤ መወገድ አለበትም አላለም። የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በማንኛውም ዓይነት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ መኖርና ማደግ መቻል አለባት። ገዦች በከፍተኛ ሥልጣን ሥር ሆነው፥ ሕግን የሚያስፈጽሙና ፍትሕ የሚያሰፍኑ ናቸው። እንደ ሕጉ አድራጊዎችን መቅጣት መልካም ያደረጉትን ደግሞ ማመስገን ይገባቸዋል። ይህ ግን በጴጥሮስ ዘመን ዘወትር አይሠራበትም ነበር (የሐዋ. ሥራ 24፡24–27)። በእኛም ዘመን ቢሆን ወደዚህ ፍጹምነት አልደረስንም። ለራሳችን ደግመን ማስታወስ ያለብን ነገር ቢኖር ባለሥልጣናትን ማክበር ባንችል እንኳን ሥልጣኑን ማክበር መቻል አለብን።

እዚህ ላይ ሁለት አስፈላጊ ሐረጎች አሉ። እነርሱም «የእግዚአብሔር ፈቃድ» (1ኛ ጴጥ. 2፡15) እና «የእግዚአብሔር ባሪያዎች» (ቁጥር 16) የሚሉት ናቸው። ነገሮችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና እንደ እግዚአብሔር ባሪያዎች ስናደርግ «ለጌታ ብለን» ማድረጋችን ነው። እግዚአብሔር ተቃዋሚዎችን ዝም እንድናሰኝ የሚፈልገው መልካም በማድረግ እንጂ ሥልጣንን በመቃወም አይደለም። በቁጥር 15 ላይ «ዝም» የሚለው ቃል «መሸበብ» ማለት ነው። ለመናከስ የሚጮኹን ውሻ ዝም እንደምናሰኝ የአሕዛብን ተቃውሞ ዝም እናሰኛለን እንደ ማለት ነው።

አንዳንዶች «እንደ ክርስቲያን ነፃ አይደለንም ማለት ነው» ብለው ሊሟገቱ ይችላሉ። እርግጥ ነው በክርስቶስ ነፃ ነን። ነጻነታችንን ግን ለራሳችን ሳይሆን፥ ሌሎችን ለመጥቀም እንጠቀምበት። ክፉ ሥራቸውን «በሃይማኖት» ስም ሸፍነው የቀሆችን የሚያጠምዱ እንዳሉ መናገሩ የሚያሳዝን ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ነጻነቱን የሚጠቀምበት ለመገንባት እንጂ ለማፍረስ አይደለም። መጀመሪያ ለጌታ ስለተገዛ ለባለሥልጣንም ይገዛል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ነህምያ ለሕዝቡና የፈረሰውን ግንብ ለማደስ ሲል የራሱን መብት አለመጠቀሙ ነው።

ለጌታ ብለን ለሰው ሥርዓት የምንገዛ ከሆነ፥ ክብር ለሚገባቸው ሁሉ ተገቢውን አክብሮት እናሳያለን። ምንም እንኳን ከፖለቲካዊ አቋማቸውና ድርጊታቸው ጋር ባንስማማም፥ ሥልጣናቸውን ግን

እናከብራለን (ሮሜ 13ን ተመልከቱ)። በመልእክቱ ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሰውን «የወንድማማች መዋደድ» (1፡22፤ 3፡8፤ 4፡8፤ 5፡14) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት የእግዚአብሔር ሰዎች የምንገልጸው «በበላይ ላሉት ባለሥልጣናት በመገዛት ነው። ምክንያቱም በክርስቲያናዊ ምስክርነታችን የተሳሰርን ስለሆንን ነው።

«እግዚአብሔርን ፍሩ» ና «ንጉሥን አክብሩ» የሚለው አባባል አብሮ ይሄዳል፤ ምክንያቱም «ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በስተቀር ሥልጣን ስለማይኖር» ነው (ሮሜ 13፡1)። ሰሎሞንም ተመሳሳይ ምክር አለው «ልጄ ሆይ፥ እግዚአብሔርንና ንጉሥን ፍራ» (ምሳሌ 24፡21)። ንጉሥን የምናከብረው እግዚአብሔርን ስለምንፈራ ነው። ፍራ የሚለው ግሥ በወደፊት ጊዜ የተገለጠ ስለሆነ ሁልጊዜ ልንጠብቀው የሚገባን አሳብ ነው። አዘውትራችሁ «ወንድሞችን ውደዱ! እግዚአብሔርን ፍሩ! ንጉሥን አክብሩ!»

አንድ ክርስቲያን በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለበት መለየት አለብን። አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛው ነገር መብታችንን መተው ይሆናል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ልንጠቀምበት እንችላለን። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መከራ ለመቀበል ፈቃደኛ ነበረ (የሐዋ. ሥራ 16፡16-24)። ያለ ፍርድ እንደ ወንጀለኛ «ከከተማ ውስጥ» አውጥተው እንዲጥሉት ግን አልፈቀደም (16፡35-40)። በሐሰት ተከሶ በተያዘበት ጊዜ፥ ራሱን ለመከላከልና ወደ ቄሣር አቤት ለማለት እንዲችል የዜግነት መብቱን ተጠቅሟል (22፡22-29፤ 25፡1-12)።

## 3. ለራሳችን ስንል (2፡18-25)

በዚህ ክፍል በክርስቲያን ኅብረት ውስጥ ያሉት ክርስቲያን ባሪያዎች መገዛት እንደሚገባቸው ይናገራል። አዲስ የተለወጡ ባሪያዎች መንፈሳዊ ነጻነታቸው ለፖለቲካዊና ሰብአዊ ነጻነታቸው ዋስትና የሚሰጥ አድርገው በማሰባቸው በራሳቸውና በቤተ ክርስቲያን ላይ ችግር ፈጥረው ነበር። ጳውሎስ ይህንን ጉዳይ በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፡20-24 ና ለፊልሞና በጻፈው መልእክት ላይ አንሥቶታል። ምንም እንኳን ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩን በመቃወም ባትሰብክበትም ወንጌል ቀስ በቀስ የሮማን የዘውድ አገዛዝና አስከፊውን የባርያ ሥርዓት አስወግዶታል።

ዛሬ በአዲስ ኪዳን ዘመን ባሪያዎች የሉም። የጴጥሮስ መልእክት ግን ተቀጥረው ለሚሠሩ ሠራተኞች መልእክት አለው። ከፉም ይሁኑ ደግ ለአለቆቻችን ልንታዘዝ ይገባል። ክርስቲያን ተቀጣሪዎች ከክርስቲያን አሠሪዎቻችን እጅ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መፈለግ

አይገባንም። እያንዳንዱ ሠራተኛ በቀን ውስጥ መሥራት ያለበትን ሠርቶ ዋጋውን መቀበል ያለበት በታማኝነት ለሠራበት ብቻ ነው።

አንዳንድ ጊዜ የሚያምኑ ሠራተኞች ክርስቲያን አሠሪዎችን ሊበድሏቸውና ሥራቸውን ሊያበላሹባቸው ይችላሉ። አሠሪው ለሕሊናው ሲል ጥፋታቸውን ተቀብሎ ሊተወው ይችላል፤ ምክንያቱም ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ከሰው ጋር ካላቸው ግንኙነት ስለሚበልጥ ነው። «ከፉን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ» (ማቴ. 5፡10–12)። ማንም ሰው የማያምኑትም ጭምር ስሕተት ከሠሩ፥ ነቀፋን በትዕግሥት ይቀበሉ ይሆናል፤ ትክክለኛ ነገር ሠርተው ሳለ፥ ነቀፋን መቀበል ግን የተሰጡ ክርስቲያኖች መሆንን ይጠይቃል። እግዚአብሔርን የምንታዘዝበትንና ነቀፋን በትዕግሥት የምንቀበልበትን ጸጋ ስለሚሰጠን በዚህ ጉዳይ ልናከብረው እንችላለን።

በእርግጥ ሰው በባሕርይው መብቱን ለማስከበር ይፋለማል። ይህ ግን የማያምኑ ሰዎች ተፈጥሮአዊ ምላሽ ሲሆን እኛ ግን ከዚህ የተሻለ ማድረግ ይኖርብናል (ሉቃስ 6፡32–34)። እያንዳንዱ ሰው መብቱን ለማስከበር መፋለም ይችላል፤ በመታዘዝ ውጊያውን ለእግዚአብሔር የሚተው ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን ነው (ሮሜ 12፡16–21)።

በመጽሐፍ ቅዱስ መደገፍ ያለበት ነገር ከእግዚአብሔር ትምህርት ጋር ተያይዞ ነው የሚቀርበው። ጳውሎስ ለባሮች የመከረውን ምክር ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር አገናኝቶታል (ቲቶ 2፡9–15)። ጴጥሮስም ምክሩን «መከራ ከተቀበለው የእግዚአብሔር ባሪያ» ከኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት ጋር አገናኝቶታል (2፡21–25፤ ኢሳ. 52፡13–53፡12 ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር ሰዎች *በመከራ ውስጥ እንደሚያገለግሉ*፥ ጴጥሮስ በሕይወቱ ተምሯል። በመጀመሪያ የኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል መሞት ተቃውሞ ነበር (ማቴ. 16፡21)፤ በኋላ ግን በማገልገል እየመራን በመከራ እንደምናገለግል ተማረ። በተጨማሪም የዚህ ዓይነቱ መከራ ሁልጊዜ ወደ ክብር እንደሚያደርስ ተማረ!

ጴጥሮስ መከራ የሚቀበሉትን ባሪያዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ሦስት ምሳሌዎችን በመጥቀስ ያበረታታቸዋል።

*ሀ. ሕይወቱ ምሳሌያችን ነው (2፡21–23)።* በወንጌል እንደተገለጸው ኢየሱስ በምድር ላይ ያደረገው ሁሉ ልንከተለው የሚገባን መልካም ምሳሌ ነው። በቃልና በሥራ አንዳች ኃጢአት ሳይገኝበት ከአለቆች እጅ መከራን ተቀበለ። ይህም፥ ጴጥሮስ በቁጥር 19 እና 20 ላይ ያስቀመጣቸውን አሳቦች ያገናኛል። ለመሆኑ ጴጥሮስ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢያልፍ ምላሹ ምን ይሆን? ለነገሩ ጴጥሮስ በአትክልት

ስፍራ ውስጥ ሰይፍ መምዘዙ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከመገዛት ይልቅ ፍልሚያን መምረጡን ያሳያል።

ኢየሱስ ያረጋገጠልን ነገር ቢኖር፥ ሰው በእግዚአብሔር እጅግ ተወዶና ፈቃዱንም እየጠበቀ ሳለ፥ መከራ ሊቀበል እንደሚችል ነው። ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ቢኖሩ መከራ አይቀበሉም የሚል ጥልቀት የሌለው ትምህርት በዚህ ዘመን የሚያስፋፉት የመስቀሉን ምሥጢር በሚገባ ያላሰላሰሉት ናቸው።

የጌታን መታዘዝና ትሕትናው የኃይል እንጂ የድካም ምልክት አይደለም። ኢየሱስ ሊረዱት የሚችሉትን ሰማያዊ ሠራዊት መጥራት ይችል ነበር። ይህንን ማድረግ መቻሉን ለጲላጦስ በተናገረው ቃል አረጋግጧል (ዮሐንስ 18፡33–38)። በፍርድ ፊት የቀረበው ጲላጦስ እንጂ ኢየሱስ አልነበረም! ኢየሱስማ በጽድቅ ለሚፈርደው አባቱ ራሱን አሳልፎ ሰጥቶ ነበር።

ሁላችንም የኢየሱስን ምሳሌ ከመከተል ይልቅ በቁጥር 22 ላይ እንደተጠቀሰው «ኃጢአት ባላደረገው» ተሰነካክለንበታል። ኃጢአተኞች የሚያስፈልጋቸው ምሳሌ ሳይሆን አዳኝ ነው። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከዳነ በኋላ የኢየሱስ ክርስቶስን ፈለግ መከተልና መንገዱንም አጥብቆ መከተል ያስፈልገዋል።

*ለ. በሞቱ ምትካችን ነው (2፡24)።* ኢየሱስ የሞተው በኃጢአተኞች ፈንታ ነው። ይህ ክፍል በኢሳይያስ 53፡5–7፥9፥12 ላይ ያለውን «ስለ አገልጋዩ» የሚናገረውን ምዕራፍ ያንጸባርቃል። ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው አዳኝ ሆኖ ነው እንጂ ሰማዕት ሆኖ አይደለም። «ተሸከመ» የሚለው ቃል «የኃጢአት መሥዋዕት በእርሱ ላይ መኖሩን» ለማመልከት ነው። አይሁዶች በእንጨት ላይ የሚሰቅሉት ወንጀለኛው እጅግ ክፉና የተረገመ መሆኑን ለማመልከት ነው። ውርደትን ለማመልከት ሬሳው እስከ ማታ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ይውላል (ዘዳ. 21፡23)። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን አዳነን (ገላ. 3፡13)።

የመስቀሉ ምሥጢር ሁልጊዜ ያስደንቀናል። እኛ እንድንፈወስ ክርስቶስ ቆሰለልን። በሕይወት እንድንኖርም ሞተልን። «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር» ከእርሱ ጋር ሞተናል (ሮሜ 6)። በቁጥር 24 ላይ ጴጥሮስ ስለ ሥጋዊ ሳይሆን፥ ስለ መንፈሳዊ ፈውስ ነው የሚናገረው [መዝ. (103)፡3]። አንድ ቀን የከበረ አካል ስናገኝ በሽታ ሁሉ ይወገዳል ለጊዜው ግን የእግዚአብሔር ምርጥ አገልጋዮች እንኳ ሳይቀሩ በበሽታ ሊሠቃዩ ይችላሉ (ፊልጵ. 2፡25–30፤ 2ኛ ቆሮ. 12፡1ን ይመልከቱ)።

ያዳነን ነውር የሌለበት የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ ነው (ዮሐ. 1፡29)። እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ኢየሱስ ያዳነን በአስተማሪነቱ ወይም በመልካም ምሳሌነቱ ሳይሆን መሥዋዕት ሆኖ በመሞት ነው።

*ሐ. በሰማይ ያለ የእኛ እረኛና ጠባቂ ነው (2፡25)።* በብሉይ ኪዳን በጎች ለእረኞቻቸው መሥዋዕት ሆነው ይቀርቡ ነበር። በቀራኒዮ ግን እረኛው ለበጎቹ መሥዋዕት ሆኖ ቀረበ (ዮሐ. 10)። እያንዳንዱ ኃጢአተኛ እንደ ጠፋ፥ እንደ ተቅበዘበዘ፥ ራሱን መርዳት እንደማይችልና ከአደጋ ውስጥ እንዳለ በግ ነው። እረኛው የጠፋውን በግ ለመፈለግ ሄደ፤ ሞተለትም (ሉቃስ 15፡1–7)።

አሁን ወደ መልካሙ መሰማሪያችን ተመልሰን በእረኛችን ጥበቃ ሥር አለን። በኃጢአት ውስጥ እንዳንገባ ይጠብቀናል። «ጠባቂ» የሚለው ቃል «የሚከታተልና የሚመለከት» ማለት ነው። ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የእግዚአብሔር መንጋ እንደሚጠብቁ (1ኛ ጴጥ. 5፡2)፤ የከበረው አዳኝም በጎቹን ይጠብቃል፥ ፍጹማንም ያደርጋቸዋል (ዕብ. 13፡20–21)።

እዚህ ላይ ጴጥሮስ ሊነግረን የፈለገው አስደናቂ እውነት በቅድስና ስንኖር፥ በመከራ ጊዜ ጭምር ስንታዘዝ የኢየሱስ ክርስቶስን ፈለግ እየተከተልንና *በይበልጥ እርሱን እየመሰልን መሆናችንን ነው።* የምንታዘዘው ለጌታና ለጠፉት ብቻ ብለን ሳይሆን ለራሳችንም ጭምር ነው። ምክንያቱም በመንፈሳዊ ሕይወታችን የምናድገውና ጌታን የምንመስለው በመታዘዛችን ስለሆነ ነው።

ያልዳኑት ሰዎች ይከታተሉናል፥ ሰማያዊው እረኛ ደግሞ ይጠብቀናል፤ ስለዚህ የሚያስፈራን ምንም ነገር የለም። ሁሉን ነገር ለክብሩና ለበጎ እንደሚያደርገው አውቀን ለእርሱ እንገዛለን።

# 6

# ጋብቻ ወይስ ፍቺ!

(1ኛ ጴጥሮስ 3፡1–7)

በዘመኑ ኅብረተሰብ ውስጥ እንግዳ ነገሮች እየተፈጸሙ ነው። ከምንጊዜውም ይልቅ ስለ ጋብቻ የሚያወሩ መረጃዎች ቢኖሩም፥ በርካታ ፍቺዎችና በትዳር ውስጥ ያሉ አለመግባባቶች የሚታዩት አሁን ነው። ችግር እንዳለ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ለእነዚህ ቤተሰቦች ያስፈልጋቸዋል ማለት ብቻውን በቂ አይደለም። ምክንያቱም የብዙ ክርስቲያኖች ትዳር እንኳ እየተፈረካከሰ ነው።

የባልና ሚስት ዳግም መወለድና መዳን ትዳራቸው የተቃና እንደሚሆን ዋስትና አይሰጥም። ጋብቻ መሠራት ያለበት በመሆኑ የተዋጣለት ትዳር በቅጽበት አይመጣም። በተለይ ከባለትዳሮቹ አንዱ ክርስቲያን ካልሆነ ችግሩን የባሰ ያደርገዋል። ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ያላመኑ ባሎች ያሏቸው ሚስቶች እንዴት አድርገው የትዳር ጓደኞቻቸውን ለክርስቶስ እንደሚማርኩ ጽፎላቸዋል። ቀጥሎም ለክርስቲያን ባሎች ተጨማሪ ምክር ለግሷቸዋል። በማንኛውም ዓይነት የጋብቻ ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ ለደስተኛና ለስኬታማ ትዳር መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን ከጴጥሮስ መማር ትችላላችሁ።

## 1. የክርስቶስ ምሳሌነት (3፡1–7)

«እንዲሁም» የሚለው ሐረግ የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌነት ለማስፋት በ2፡21–25 ወደ ተጠቀሰው ክፍል ያመለክታል። ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንደታዘዘና እንደ ተገዛ ክርስቲያን ባልና ሚስቶችም ይህንን ምሳሌነት ሊከተሉ ይገባል።

በሕይወታችን ዘመን ብዙ የምንማረው ሌሎችን በማየት ነው። አያቶች በማደግ ላይ ያሉ የልጅ ልጆቻቸው፥ አዳዲስ ክህሎቶችንና አዳዲስ ቃላትን ሲኮርጁ በማየት ይደሰታሉ። ጥሩ ምሳሌ የሆኑ ሰዎችን የምንኮርጅ ከሆነ የተሻለ ነገር መሥራት የምንችል ሰዎች እንሆናለን። መጥፎ ሰዎችን ብንኮርጅ ግን፥ ሕይወታችን ልፍስፍስ፥ ፀባያችንም ደግሞ ብልሹ ይሆናል። «አርአያ የሚሆኑልን» ሰዎች በሁሉም የሕይወታችን መስክ ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አላቸው።

በአንድ የገበያ መደብር መውጫ በር ላይ ተሰልፈን ሳለ ሁለት ሴቶች የጋዜጦችን የመጀመሪያ ገጽ በያዘው አሳፋሪ የሆሊውድ ትዕይንት ላይ ሲወያዩ ሰማኋቸው። ወዲያውም «ኃጢአት ስለሞላበት

ፊልምና ሙዚቃ መጫነቅ ምንኛ ሞኝነት ነው? አእምሮን እንደዚህ ርካሽ በሆነ ነገር ለምን ታስጨንቁታላችሁ? ስለምንስ ከመልካም ሰዎች መልካም ነገርን አትማሩም?» በማለት አስብ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ በአንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ስለታየ የጋብቻ ችግር ሲያወሩ ሰማሁና አሁንም ያ የቀድሞው አሳብ መጣብኝ።

ባለትዳር ክርስቲያኖች ዓለምን ለመምሰል ሲሞክሩና የኑሮ መመሪያቸውን ከሰማይ ሳይሆን፥ ከሆሊውድ ለማግኘት ሲሞክሩ በቤታቸው ችግር ይፈጠራል። ሁለቱም የትዳር ጓደኞች ኢየሱስ ክርስቶስን በመታዘዙ፥ በመገዛቱና ሌሎችን ለማገልገል ባለው ፍላጎት ቢመስሉት ድልና ደስታ በቤታቸው ይሰፋናል። አንድ የሥነ-አእምሮ ሐኪም የሆነ ጓደኛዬ ክርስቲያን ባል ማድረግ የሚገባው የተሻለ ነገር የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌነት መከተል እንደሆነ አስቀምጦታል። በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ድንቅ የሆነ የጥንካሬና የርኅራኄ ጥምረት እናያለን። ይህ ደግሞ ጥሩ ባል ለመሆን የሚያስፈልግ ነገር ነው።

ጴጥሮስ፥ ሣራ ለክርስቲያን ሴቶች ምሳሌ እንደሆነች ይጠቁማል። እውነት ነው ሣራ ፍጹም አልነበረችም፤ ይሁን እንጂ፥ ለአብርሃም ጥሩ ረዳት መሆኗን በማስመስከሯ በዕብራውያን 11 ላይ ስማቸው ከተጠቀሱት ጥቂት ሴቶች መካከል አንዷ ናት። አንድ ጊዜ በትዳሯ ውስጥ ችግር እንዳለ የነገረችኝን ሴት ለመጎብኘት ሄድኩ። በጠረጴዛዋ ላይ ብዙ የሲኒማ መጽሔቶችን ተመለከትኩ። የሴትየዋን ችግር ካደመጥኩ በኋላ የሰጠሁት ብያኔ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎችንና አርአያዎችን በመከተል ከአእምሮዋ ዓለማዊ ተምሳሌቶችን ታስወግድ በሚል ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን መሆኑን አውቀን ካልተገዛንለት ምሳሌነቱን መከተል አንችልም። በየቀኑ በመጸለይና ቃሉን በማጥናት ከእርሱ ጋር ጊዜ ሊኖረን ይገባል። ክርስቲያን ባለትዳሮች አብረው በመጸለይ በእምነታቸው እርስ በርሳቸው ሊበረታቱ ይገባል።

## 2. መገዛት (3፡1-6)

ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ውስጥ ሁለት ጊዜ ክርስቲያን ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዲገዙ አሳስቧቸዋል (3፡1 ና 5)። «መገዛት» የሚለው ቃል «በደረጃ መቀመጥን» ያመለክታል። እግዚአብሔር ለሁሉ ነገር ቦታ አለው። የተለያዩ የሥልጣን ደረጃዎችን አዘጋጅቷል (1ኛ ጴጥ. 2፡13-14 ይመልከቱ)። ባል ደግሞ የሚስት ራስ እንዲሆን ተሹሟል። እርሱ ለክርስቶስ እንደሚገዛ ሚስት ደግሞ ለእርሱ ትገዛለች (ኤፌ. 5፡21)። ራስ መሆን ፈላጭ ቆራጭነት ሳይሆን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ሥር መለኮታዊ ሥልጣንን በፍቅር መለማመድ ነው።

ጴጥሮስ (ባሏ ያላመነ ቢሆንም እንኳን)፥ ክርስቲያን ሚስት ለባሏ መገዛት የሚገባት ለምን እንደሆነ የሚገልጹ ሦስት ምክንያቶችን አስፍሯል።

*ሀ. መገዛት ግዴታ ነው (3፡1)።* እግዚአብሔር በጥበቡ ተገዙ ብሎ ያዘዘው ለደስተኛና ለተቃና ትዳር ትክክለኛው አሰላለፍ ይኸኛው በመሆኑ ነው። ሚስት የምትገዛው ከባል ስለምታንስ ወይም የበታች ስለሆነች አይደለም። ይህንን ጉዳይ ጴጥሮስ በቁጥር 7 ላይ ባልና ሚስት «አብረው የሕይወት ጸጋ ወራሾች» ናቸው በማለት በግልጽ አስቀምጦታል። ወንድና ሴት በአንድ ፈጣሪ፥ ከአንድ ዓይነት ነገርና በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል። እግዚአብሔር ሥልጣን የሰጠው ለአዳምም ለሔዋንም ነው (ዘፍ. 1፡28)፥ በኢየሱስ ክርስቶስም አንድ ናቸው (ገላ. 3፡28)።

መገዛት ከሥርዓትና ከሥልጣን ጋር እንጂ፥ ከሥራ አፈጻጸም ጋር አይያያዝም። መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ባላቸው የሮማውያን ቤተሰብ ውስጥ ባሮቻቸው ከጌቶቻቸው የሚበልጡበት ብዙ መንገድ ቢኖርም፥ አሁንም በጌቶቻቸው ሥልጣን ሥር ናቸው። በሠራዊቱ ውስጥ ያለ አንድ ተራ ወታደር ከአምስት ጄነራሎች ሊበልጥ ቢችልም ያው ተራ ወታደር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስም እንኳ ባርያ በመሆን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ተገዝቷል። በሥልጣን በመገዛትና እግዚአብሔር ያስቀመጠውን የሥልጣን ተዋረድ በመቀበል የሚያዋርድ ነገር የለም። ይልቁንስ የመስኩ የመጀመሪያ እርምጃ ነው። በኤፌሶን 5፡21 ላይ ባልም ሆነ ሚስት በቅድሚያ ለክርስቶስ መገዛት እንዳለባቸው ግልጽ አድርጎታል።

ባልና ሚስት የትዳር አጋሮች እንጂ፥ ተፎካካሪዎች መሆን አይገባቸውም። ሁልጊዜ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ፥ በግል ሙሽራዪቱንና ሙሽራውን «አስታውሱ፥ ከዚህ በኋላ *የእኛ እንጂ የእኔ ወይም የአንተ* የሚባል ነገር የለም» እላቸዋለሁ። ክርስቲያን ክርስቲያንን ብቻ የሚያገባበት ምክንያት ከማያምን ጋር ጥልቅ የሆነ አንድነት ሊኖረው ስለማይችል ነው (2ኛ ቆሮ. 6፡14-18)።

*ለ. መገዛት መልካም ዕድል ነው (3፡1-2)።* ለምን የሚጠቅም ዕድል ነው? ያላመነን ባል ለክርስቶስ ለመማረክ የሚጠቅም መልካም ዕድል ነው። እግዚአብሔር የመገዛትን ትእዛዝ መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ በቤተሰብ ውስጥ ትልቅ መንፈሳዊ ተጽዕኖ ለማምጣት ይጠቀምበታል። ክርስቲያን ሚስት ላልዳነ ባሏ የምትገዛለት የምትፈልገውን ነገር እንዲያደርግላት በተንኮል ልታታልለው አይደለም። እንደዚህ ዓይነቱ

ለራስ ጥቅም ሲባል ሌላውን በተንኮል የማሳመን ተግባር በክርስቲያን ልብም ሆነ በቤተሰብ ውስጥ ፈጽሞ መገኘት የለበትም።

ያልዳነ ባል፥ በስብከትም ሆነ በጭቅጭቅ አይለወጥም። «ያለ ትምህርት» የሚለው ሐረግ «ያለ እግዚአብሔር ቃል» ማለቱ አይደለም፥ ምክንያቱም ደኅንነት የሚመጣው ከእግዚአብሔር ቃል ነውና (ዮሐ. 5፡24)። «ያለ ትምህርት» ሲል ግን «ብዙ ንግግር» ያለማብዛት ለማለት ነው። ክርስቲያን ሚስት ይህንን በማድረጓ ባሏን ከጌታ ልታርቀው ትችላለች። አንዲት የማውቃት ሴት ባለቤቷ ክርስቲያን እንዲሆን ካላት ፍላጎት የተነሣ ማታ ማታ በሬድዮ የሚተላለፈውን ስብከት ድምፁን ከፍ በማድረግ ባለቤቷ «እውነትን እንዲያዳምጥ» ለማድረግ ትሞክር ነበር። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ሰውየው ቤቱን ትቶ ማታ ማታ ከጓደኞቹ ጋር እንዲያመሽ ምቹ መንገድ ከፈተለት።

ሚስት በጌታ ያልሆነ ባሏን ለጌታ የምትማርከው በጭቅጭቅ ሳይሆን በመገዛት፥ አሳብ ለአሳብ በመረዳዳት፥ በፍቅር፥ በደግነትና በትዕግሥት ነው። እነዚህ መልካም ባሕርያት በፋብሪካ የሚመረቱ ሳይሆኑ፥ ለክርስቶስና አንዳችን ለሌላችን ስንገዛ የሚመጣ የመንፈስ ፍሬ ነው። ክርስቲያን ሚስት «በንጽሕናና በፍርሃት» «የእግዚአብሔርን በጎነት» (1ኛ ጴጥ. 2፡9) በሕይወቷ በመግለጽ ባለቤቷን በጌታ እንዲያምን ልታደርገው ትችላለች።

የቅዱስ አግስቲን እናት ሞኒካ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ መልካም ምሳሌ ከሆኑትና እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ሴቶች መካከል የምትጠቀስ ናት። እግዚአብሔር የሞኒካን ጸሎትና ምስክርነት ተጠቅሞ ልጇንና ባሏን ለውጦአቸዋል። ባሏ የተለወጠው ለመሞት በተቃረበበት ጊዜ ሲሆን፥ አግስቲን «ኮንፌሽን» (ኑዛዜ) በሚለው መጽሐፍ እንደ ጻፈው «እንደ ጌታዋ አገልግላዋለች፥ እርሱን ለአንተ ለመማረክ ተጋች. . . አንተን ለእርሱ የሰበከችው ከባሏ ጋር በሚያስማማት አንተ ባስጌጥካት ባሕርይዋ ነው።»

በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ አንዱ ሌላውን ሊያገለግል ይገባል። ክርስቲያን ባል ሚስቱን በጌታ «ውብ እንድትሆን» ማገልገል አለበት (ኤፌ. 5፡25-30)። ክርስቲያን ሚስት ደግሞ ባሏ በጌታ እንዲበረታና እንዲያድግ ልታነሣሣው ይገባል። ወላጆችና ልጆች ሸክምን እና በረከትን በመከፋፈል መንፈሳዊ ደስታና ዕድገት ያለበት ቤተሰብ እንዲኖራቸው መሻት አለባቸው። በቤት ውስጥ ያላመነ ሰው ቢኖር ከምስክርነት ቃላታችን ይልቅ ሕይወታችንንና እርስ በርስ ያለንን ግንኙነት አይቶ ለጌታ ይማረካል።

*ሐ. መገዛት ጌጥ ነው (3፡3—6)።* «መሸለም» የሚለው ቃል በግሪኩ ኮስሞስ ማለት ነው። ይህም በሥርዓት የተቀመጠ አጽናፈ ዓለም ማለት ነው። የምስቅልቅል ተቃራኒ ነው። ጴጥሮስ የክርስቲያን ሚስት መታወቂያዋ ውጫዊ ጌጣጌጥ ሳይሆን ውስጣዊ ባሕርይዋ እንዲሆን ይመክራል። የሮማ ሰዎች እጅግ ዘመናዊ አለባበስን የሚወዱና በአለባበሳቸውና በፀጉር አሠራራቸውም እርስ በርሳቸው የሚወዳደሩ ነበሩ። በዚያን ዘመን ፀጉርን ሹርባ መሥራትና በወርቅና በብር ማስጌጥ እንዲሁም ውድ በሆነ መጎናጸፊያ በመሸለም አንዳቸው በሌላቸው ለመደነቅ መሞከር የተለመደ ነገር ነበር። አንዱ ሌላውን ለማስቀናት ሲሉ እጅግ የደመቁና ውድ የሆኑ ልብሶችን ይለብሱ ነበር።

ያላመነ ባል ያላት ሚስት ባለቤቷን ለመማረክ ዓለምን መምሰል አለብኝ ብላ ታስብ ይሆናል። ይሁን እንጂ እውነታው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። የሚያብለጨልጨው ውጫዊና ጊዜያዊ ነው፤ እውነተኛው ውበት ግን ከውስጥ የሆነና የሚገለጥም ነው። የውስጥ ውበት እንደ ውጭ ጌጥ የሚጠለቅና የሚወልቅ፥ የሚጠፋና የሚደበዝዝ ሳይሆን፥ ዓመታት ሲያልፉ የሚያብብና የሚያፈራ ነው። ስለ ውስጥ ውበቷ የምትጠነቀቅ ክርስቲያን ሴት ርካሽ በሆነ ውጫዊ ጌጥ አትታመንም። እግዚአብሔር ጉዳዩ በውስጣዊ እሴት ላይ እንጂ ገንዘብ ሊገዛው በሚችል ሸቀጥ ላይ አይደለም።

ይህ በእርግጥ ሚስት ራሷን መጣል አለባት በአለባበሷም ዘመናዊ መሆን የለባትም ለማለት ሳይሆን፥ የምትታወቀው «ከሌሎች ላለማነስ የፋሽን ማስታወቂያ» መስሎ በመታየት አይሁን ለማለት ነው። የትኛውም ባል ቢሆን ሚስቱ ውብ ብትሆን ይኮራባታል፥ ውበቷ የሚወጣው ግን ከውስጥ እንጂ ከግምጃ ቤት መሆን የለበትም። ከዚህ ዓለም ስላልሆንን ያልተገኘንበትን ዓለም መምሰል የለብንም!

ጴጥሮስ ጌጣጌጥ ማድረግን፥ ማንኛውንም ልብስ ከመልበስ በላይ እስካልተጋነነ ድረስ አልከለከለም። ቃሉ የሚያመለክተው በጌጥና በልብሶች መሽቀርቀርን ነው። ጌጥም አድርጎ እግዚአብሔርን ማክበር ስለሚቻል፥ በዚህ ጉዳይ ላይ እርስ በርሳችን መተቻቸትና መፈራረድ የለብንም።

ጴጥሮስ ይህንን ክፍል የሚያጠናቅቀው ለባሏ ትገዛ የነበረችውን የእግዚአብሔር ሰው ሣራን በማንሣት ነው (ዘፍጥረት 18ን ይመልከቱ)። በዚህ ዘመን ያሉ ክርስቲያን ሚስቶች ባሎቻቸውን «ጌታ» ብለው ሊጠሯቸው ሊያፍሩ ይችላሉ። በአመለካከታቸው ግን «ጌታ» ብለው ሊጠሯቸው የሚችሉ፥ ሌሎችም አይተው የሚያምኑበት

ሊሆን ይገባል። ለክርስቶስና ለባሏ የምትገዛ «የዋሕና የረጋ መንፈስ» ያላት ሴት ፈጽሞ መፍራት የለባትም። በዚህ ክፍል ፍርሃት የሚለው ቃል መሸበር ማለት ሲሆን፥ በቁጥር 2 ላይ ግን አክብሮትን የሚገልጽ ነው። በእግዚአብሔር የማያምነው ባለቤቷ ችግር በሚፈጥርባት ጊዜ ሳይቀር ይጠብቃታል።

## 3. ማስተዋል (3፡7)

ጴጥሮስ ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች የሰጠው መመሪያ የበዛበት ምክንያት ሴቶች የነበሩበት ሁኔታ አዲስ በመሆኑ ነው። በሮማ ግዛት ሴቶች ይጨቆኑ ስለነበር በክርስቶስ ያገኙት አዲሱ ነጻነታቸው አለመግባባትንና ችግርን ፈጥሮ ነበር። በተጨማሪም ብዙዎቹ ያላመኑ ባሎች ስለ ነበሯቸው ማበረታቻና መነቃቂያ ያስፈልጋቸው ነበር።

ጴጥሮስ ክርስቲያን ባሎች ከሚስቶቻቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ሊያስታውሱት የሚገባ አራት የኃላፊነት አቅጣጫዎችን ጽፎላቸዋል።

*ሀ. በአካል- «አብራችሁ ኑሩ»።* ይህ በአንድ ቤት ጣራ ሥር ከመኖር ያለፈ ነገርን ያመለክታል። በመሠረቱ ጋብቻ በአካል አንድ መሆን ነው። «ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉና» (ኤፌ. 5፡3) ይላል። ክርስቲያን ባለትዳሮች ጥልቅ መንፈሳዊ ኅብረት ቢኖራቸውም በአካልም አንድ መሆናቸው አብሮ መሄድ አለበት (1ኛ ቆሮ. 7፡1-5)። መንፈሳዊ የሆነ ባል በትዳር ውስጥ ያለበትን ኃላፊነት የሚወጣና ሚስቱን የሚወድ ነው።

ባል ከሚስቱ ጋር በቤቱ የሚያሳልፈው ጊዜ ሊኖረው ይገባል። ሠራተኛና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ ባሎች የሌሎችን ችግር ለመፍታት ደፋ ቀና ሲሉ፥ በራሳቸው ትዳር ላይ ችግር ፈጥረው ያርፋሉ። አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው ባልና ሚስት በአማካይ በሳምንት ሠላሳ-ሰባት ደቂቃ አብረው ያሳልፋሉ። ታዲያ ልጆች አድገው ቤቱን ለቅቀው ሲወጡ ትዳር ቢፈርስ ምን ያስደንቃል! ያኔ ባልም ሆነ ሚስት የሚኖሩት ከማያውቁት እንግዳ ሰው ጋር ነው ማለት ነው።

«አብራችሁ ኑሩ» የሚለው ባል ለኑሮ የሚያስፈልገውን እንደሚያሟላ የሚያመላክት ነው። ሴት ልጅ ሥራ ወይም አገልግሎት ቢኖራት ምንም ችግር የለውም፤ ቀዳሚው ኃላፊነቷ ግን ለቤቷ መጠንቀቅ ነው (ቲቶ 2፡4-5)። ባል ግን ለኑሮ የሚያስፈልገውን ሊያዘጋጅ ይገባል (1ኛ ጢሞ. 5፡8)።

*ለ. በእውቀት–«በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ»።* አንድ ሰው ወ/ሮ አንስታይንን ስለ ዶክተር አልበርት አንስታይን የአንጻራዊነት ጽንሰ አሳብ ያውቁ እንደሆነ ጠየቃቸው። እርሳቸውም «ጽንሰ አሳቡን አላውቅም፥ ዶክተርን ግን እረዳዋለሁ።» በማለት መለሱ። የቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንደ መሆኔ መጠን ከጋብቻ በፊት በምሰጠው የምክር አገልግሎት ላይ አንዳቸው በሌላው የማይደሰቱበትን ሦስት ነገሮች በወረቀት ላይ እንዲጽፉ እጠይቃቸዋለሁ። ሴቷ ዝርዝሮቿን ፈጥና ስትጽፍ፥ ወንዱ ግን ቁጭ ብሎ ያስባል። ብዙ ጊዜ ሴቶች ትክክለኛውን ነገር ሲጽፉ ወንዶቹ ግን ይሳሳታሉ!

ባልና ሚስቶች አብረው እየኖሩ አለመተዋወቃቸው የሚያስደንቅ ነገር ነው። አለማወቅ ሁሉንም የሕይወታችንን ክፍል ይጎዳል። በትዳር ላይ የሚያመጣው ጉዳት ግን ከሁሉም ይብሳል። ክርስቲያን ባል ሚስቱ መቼ ምን እንደሚሰማት፥ ፍላጎቷን፥ ፍርሃቷን፥ ተስፋዋን በማወቅ «ከልቡ ሊያደምጣትና» በመካከላቸው ትርጉም ያለው መግባባት እንዲኖር ማድረግ አለበት። በቤት ውስጥ ባልና ሚስት ላይስማሙ ቢችሉም፥ በፍቅር አብረው ለመኖር የሚያስችላቸውን አንድነት ሊጠብቅ የሚችል የፍቅርና የመገዛት ሕይወት ሊኖራቸው ይገባል።

«ፍቅር ያለ እውነት ግብዝነት ነው፥ እውነት ያለ ፍቅር ደግሞ ጭካኔ ነው» የሚል አባባል አለ።

እውነትን በፍቅር መናገር ለሚፈጠረው የመግባባት ችግር መፍትሔ ሊሆን ይችላል (ኤፌ. 4፡15)። አንዱ ሌላውን በመርዳት ለማደግ እውነትና ፍቅር ያስፈልጋል። ባል የሚስቱን ፍላጎትና ችግር ካላወቀ እንዴት ሊረዳት ይችላል? «እንደዛ እንደተሰማሽ እኮ አላወቅሁም ነበር!» ማለቱ አንዱ ሌላውን አግልሎት እንደነበር የሚያሳይ ኑዛዜ ነው። ሁለቱም በግልጽና በታማኝነት መነጋገርን የሚፈሩ ከሆነ፥ የሚለያያቸውን ግድግዳ እንጂ የሚያገናኛቸውን ድልድይ እየሠሩ አይደለም።

*ሐ. በስሜት– «ለሚስቶቻችሁ ክብርን ስጡ»።* ጴጥሮስ ሴትን «ደካማ ፍጥረት» ብሎ የጠራት በአእምሮ፥ በሥነ ምግባር፥ በመንፈሳዊነት ሳይሆን፥ በአካል ነው። በአብዛኛው በአካላዊ እንቅስቃሴ ለሚደረጉ ነገሮች ከሴቶች ይልቅ ወንዶች ጠንካራ ናቸው። ስለዚህ ባል ሚስቱን እንደ ውብ፥ የከበረች፥ ውድ መዝገብ ሊመለከታት ይገባል።

በእጮኛነት ጊዜ ወንዱ ሴቷን ያከብራታል፤ ጨዋነትም ያሳያል። የሚያሳዝነው ነገር ግን ከተጋቡ በኋላ እጮኛው በነበረችበት ጊዜ

የሚያደርግላትን ሁሉ መርሳቱ ነው። በቤት ውስጥ ደስታ የሚኖረው ትንንሽ የሚመስሉ እንደ አክብሮት ያሉ ነገሮች ተደምረው ነው።

ትልቅ ቅራኔ የሚፈጠረው ከትንሽ መቃቃር ነው። ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ሊቀባበሉ፥ አንዱ ሌላውን ማሳዘኑ ተሰምቶት ይቅርታንና ፈውስን ሊፈልጉ ይገባል። «ሚስትን ማክበር» ማለት «ለሚስት መገዛት» ማለት አይደለም። ባልና ሚስት በአሳብ ላይግባቡ ቢችሉም ሊያከብራት ግን ይገባል። በቤት ውስጥ መሪ እንደ መሆኑ መጠን አንዳንድ ጊዜ እንግዳ የሆነ ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይችላል። ይህንንም ሚስቱን በማክበር ሊያደርገው ይገባል።

«ክብር መስጠት» ማለት የሚስቱን ስሜት፥ አመለካከትና ፍላጎት ማክበር ማለት ነው። በአሳቧ ባይስማማም አሳቧን ሊያከብርላት ይገባል። እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ አንዱ ሌላውን እንዲጠቅም አድርጎ ነው የሚያጣምረው። የሚቻኩል ባል ረጋ ያለች ሚስት ብትኖረው ከችግር እንዲያመልጥ ትረዳዋለች!

ባል የሙቀትን መጠን እንደሚጨምርና እንደሚቀንስ መሣሪያ በቤት ውስጥ ያለውን መንፈሳዊና ስሜታዊ እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል። ሚስት ደግሞ እንደ ሙቀት መለኪያ መሣሪያ በቤት ውስጥ ያለው አየርና ሙቀት በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ታሳውቃለች። ስለዚህ ሁለቱም ጠቃሚ ናቸው። ባል የሚስቱን ሁኔታ ተገንዝቦ ደስተኛ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፥ ራሱ በመንፈሳዊ ሕይወቱ አድጎ ልጆቹን ደግሞ እግዚአብሔርን በሚያከብር ቤተሰብ ውስጥ እንዲያድጉ ያደርጋቸዋል።

*መ. መንፈሳዊ– «ጸሎታችሁ እንዳይከለከል»።* ጴጥሮስ ይህንን ሲጽፍ ባልና ሚስት አብረው ይጸልያሉ ብሎ በማሰብ ነው። ብዙ ጊዜ ግን አብረው አይጸልዩም። ይህ ደግሞ ለብዙ ውድቀት የሚዳርግ የደስታ ፀር ነው። የማያምኑት ያለ ጸሎት ደስተኛ ቤተሰብ ካላቸው፥ ጸሎት ያለበት የክርስቲያን ቤት የቱን ያህል ደስተኛ ይሆን! የባለትዳሮች የጸሎት ሕይወት በቤታቸው ያለው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ያመለክታል። አንዳች ትክክል ያልሆነ ነገር ካለ ጸሎታቸው ይከለከላል።

ባልና ሚስት በየቀኑ በግልና በጋራ የጸሎትና የጽሞና ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል። ጊዜው ከቤት ቤት፥ ልጆች ሲያድጉና የሥራ ፕሮግራሞች ሲለዋወጡ ሊቀያየር ይችላል። ይሁን እንጂ ለተቀደሰና ለደስተኛ ቤተሰብ የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት መሠረታዊ ነገሮች ናቸው (የሐዋ. ሥራ 6፥4)።

ባልና ሚስት «የሕይወትን ጸጋ የሚወርሱት አብረው ነው»። ሚስት ለባሏ ከተገዛች ባልም ደግሞ ሚስቱን ከተንከባከበ፥ ለክርስቶስ በመገዛታቸውና ምሳሌውን በመከተላቸው በመልካም ኑሮ የበለጸገ ትዳር ይኖራቸዋል።

ባልና ሚስት ትዳራችን እንዴት ነው በማለት ራሳቸውን የሚገመግሙበት ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል። ጴጥሮስ በጻፈው ላይ ተመሥርተን ትዳራችንን በሚከተሉት ጥያቄዎች መገምገም እንችላለን፦

1. እርስ በርሳችን የምንደጋገፍ አጋሮች ነን ወይስ ተፎካካሪዎች?

2. የበለጠ መንፈሳዊ ሰው ለመሆን እርስ በርስ እንረዳዳለን?

3. የምንደገፈው ውጫዊና አርተፊሻል በሆነው ነገር ነው ወይስ ውስጣዊና እውን በሆነው ነገር?

4. አንዱ የሌላውን አመለካከት ይገነዘባል?

5. አንዱ ለሌላው ስሜትና አመለካከት ትኩረት ይሰጣል ወይም የምንተያየው በግድ የለሽነት ነው?

6. እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሲመልስ እያየን ነው?

7. በትዳራችን ምክንያት እየተባረክን ነው ወይስ አንዳችን የሌላውን በረከት እያስቀረን ነው?

ለእነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው ትክክለኛ ምላሽ በሕይወታችን ለውጥ ሊያመጣ ይችላል!

# 7

# ለተሻለው ነገር መዘጋጀት!

(1ኛ ጴጥሮስ 3፥8–17)

አንድ ራሱን ለጌታ የሰጠ መጋቢ ከፍተኛ ቀዶ ጥገና ተደርጎለት ሳለ አንድ ጓደኛው ሊጠይቀውና ሊጸልይለት ወደ ሆስፒታል ሄደ። «ዛሬ አንድ አስደሳች ነገር ተከናወነ» በማለት መጋቢው ተናገረ። «ከአስታማሚዎቹ አንዷ የሕክምና መዝገቤን አይታ፥ ‹ራስህን ለከፋው ነገር አዘጋጅ› አለችኝ። እኔም መልሼ ‹እንደ እርሱ አይደለም፥ እኔ ራሴን ለተሻለው ነገር እያዘጋጀሁ ነው። እኔ ክርስቲያን ነኝ፥ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለበጎ እንደሚያደርገው ቃል ገብቷል› አልኳት። እርሷም ቻርቱን ጥላው ከዚህ ክፍል ተፈተለከች!»

ጴጥሮስ ይህንን መልእክት የጻፈው ክርስቲያኖችን «ለሚፈትን መከራ»ና ስደት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ቢሆንም፥ አቀራረቡ ግን ተስፋ እንዳለ የሚጠቁምና ቀና ነው። መልእክቱ «ለተሻለው ነገር ተዘጋጁ!» የሚል ነው። በዚህ ክፍል በአስቸጋሪ ወቅት የተሻለ በረከት ሕይወት እንዲያጣጥሙ ሊከተሏቸው የሚገቡ ሦስት መመሪያዎችን ሰጥቷቸዋል።

## 1. ክርስቲያናዊ ፍቅርን መንከባከብ (ማሳደግ) (3፥8–12)

በጴጥሮስ መልእክቶች ከእግዚአብሔር ፍቅር በተጨማሪ እርስ በርሳችን ሊኖረን የሚገባው ፍቅር ተደጋግሞ የሚታይ መሪ ሐሳብ ነው። ጴጥሮስ ራሱ ይህንን ጠቃሚ ትምህርት መማር የነበረበት ቢሆንም፥ ለመማር ተቸግሮ ነበር። ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ለመሆን ምን ያህል ታግሶት ይሆን!

*ለእግዚአብሔር ሕዝብ በሚኖረን ፍቅር መጀመር ይገባናል* (3፥8)። «በመጨረሻም» የሚለው ቃል «ሁሉን ለማጠቃለል» ማለት ነው። ሕግ ሁሉ በፍቅር እንደሚጠቃለል ሁሉ (ሮሜ 13፥8–10)፥ የሰዎች ኅብረትም የተሟላ የሚሆነው በፍቅር ነው። ይህ እውነት በእያንዳንዱ ክርስቲያንና በእያንዳንዱ የሕይወት ዘርፍ በሥራ ላይ የሚውል ነገር ነው።

ይህም ፍቅር *በልብ አንድነት* ይረጋገጣል (ፊልጵ. 2፥1–11ን ይመልከቱ)። አንድነት ማለት አንድ ዓይነት መሆን ማለት አይደለም። ነገር ግን ልዩነትን አጥብቦ መተባበር ማለት ነው። የሰውነት አካላት ልዩ ልዩ ቢሆኑም በአንድነት እንደሚሠሩ ሁሉ፥ ክርስቲያኖችም

አንዳንድ ነገሮች እንዴት መሠራት እንዳለባቸው ቢለያዩም ምንና ለምን እንደሚሠራ ግን መስማማት አለባቸው። አንድ ሰው የዲ.ኤል. ሙዲን የወንጌል የስብከት ዘዴ ተቃውሞ ሲናገረው ሙዲ «እኔ ለመሻሻል ዝግጁ ነኝ። የአንተ ዘዴ ምንድን ነው?» ብሏል። ይህን የጠየቀው ሰውየም ምንም እንደሌለው ተናግሮአል! ሙዲም «እንግዲያውስ ባለኝ የስብከት ዘዴ እቀጥላለሁ» አለው። ምንም ዓይነት መንገድ ብንጠቀምም ጥማታችን ክርስቶስን ማክበር፥ የጠፉትን ማዳንና ቤተ ክርስቲያንን መገንባት ነው።

ሌላው የፍቅር መግለጫ ርኅራኄ ሲሆን፥ ይህም የሌሎችን ፍላጎት ለማሟላት በቅን ስሜት አብሮ መሆን ነው። «ኀዘኔታን» የሚለው ቃልም የመጣው ከዚሁ ነው። እርስ በርሳችን መጨካከን የለብንም። ደስታንና መከራን አብረን መካፈል አለብን (ሮሜ 12፡15)። ለዚህ መሠረቱ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለን ወንድማማቾች መሆናችን ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡22፤ 2፡17፤ 4፡8፤ 5፡14ን ይመልከቱ)። እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ከእግዚአብሔር ተምረናል» (1ኛ ተሰ. 4፡9)።

ፍቅር *ለሌሎች በማዘን* ራሱን ይገልጻል፤ ለሌሎች የሚያዝን ልብ አለው። በሮም ግዛት ይህ ዓይነቱ ባሕርይ የብቃት መለኪያ ተደርጎ የሚደነቅ አልነበረም፤ ነገር ግን የክርስትና መልእክት ይህንን ሁሉ ለውጦታል። ዛሬም ብዙ ዓይነት አሳዛኝ ዜናዎችን ስለምንሰማ፥ ስሜታችንን በማገድ እንደማይሰማን እንሆናለን። ርኅራኄን በሕይወታችን በማሳደግ ስለ ሌሎች ግድ እንደሚለን ማሳየት አለብን።

«ትሑታን ሁኑ» ሲል ጨዋ ሁኑ ከማለት ያለፈ ነው። ዝቅ ማለት የትሕትና መሠረት ነው። ትሑት ሰው ደግሞ ሌሎችን ከራሱ በፊት ያስቀድማል።

መውደድ ያለብን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን *ጠላቶቻችንንም ጭምር* ልንወድ ይገባናል (1ኛ ጴጥ. 3፡9)። ይህ መልእክት የተጻፈላቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸማቸው ምክንያት በስደት ውስጥ እያለፉ ነበር። ጴጥሮስ ያስጠነቀቃቸው የባሰ መከራ እየመጣ በመሆኑ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ነው። አስቸጋሪ ጊዜያት ከፊት ለፊት ስላሉ፥ የዛሬዋም ቤተ ክርስቲያን ራሷን ብታዘጋጅ ይሻላታል። እንደ ክርስቲያን ከሦስቱ በአንደኛው ደረጃ ላይ እንኖራለን። በመልካም ፈንታ ክፋትን እንመልሳለን፥ ይህ ሰይጣናዊ ደረጃ ነው። ለመልካም መልካምን ለክፋት ደግሞ ክፋትን እንመልሳለን፥ ይህም ሰዋዊ ደረጃ ነው። በክፉ ፈንታ መልካምነትን እንመልሳለን፥ ይህ መለኮታዊው ደረጃ ነው። ኢየሱስ የመጨረሻው ደረጃ ምሳሌ ነው (2፡21–23)። እንደተወደዱ የእግዚአብሔር ልጆች

የፍትሕ መሠረት የሆነውን «ዓይንን በዓይን፥ ጥርስን ደግሞ በጥርስ» መመለስ የለብንም (ማቴ. 5:38-48)። እግዚአብሔር እኛን በሚያይበት *ምሕረት* ሌሎችን ልናይ ይገባናል።

ይህ ማስጠንቀቂያ ለጴጥሮስ የተለየ ትርጉም አለው። ምክንያቱም እርሱ ራሱ የክርስቶስን ጠላቶች በሰይፍ ሊመክት ሞክሯልና (ሉቃስ 22:47-53)። ጳውሎስም ሳይለወጥ በፊት ቤተ ክርስቲያንን ለመቃወም የቻለውን ሁሉ ሞክሯል። ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ ግን የእግዚአብሔርን ውጊያ ለመዋጋት የሰዎችን ጦር መሣሪያ አልተጠቀመም (ሮሜ 12:17-21፤ 2ኛ ቆሮ. 10:1-6)። ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት በተሰደዱ ጊዜ የታመኑት በራሳቸው ጥበብና ኃይል ሳይሆን፥ በጸሎትና በእግዚአብሔር ኃይል ነበር (የሐዋ. ሥራ 4:23ን ይመልከቱ)።

ሁል ጊዜ ለክርስትና *እንደተጠራን* ማስታወሳችን ጠላቶቻችን ሲጎዱን እንድንወዳቸውና በሚገባ እንድናስተናግዳቸው ይረዳናል። «በረከትን ልንወርስ» ተጠርተናል። ዛሬ በምድር የሚገጥሙን ስደቶች ወደፊት በመንግሥተ ሰማይ ለሚጠብቀን የተባረከ የክብር ርስት ይጨምሩልናል እንጂ አንዳች የሚያጎድሉብን ነገር የለም (ማቴ. 5:10-12)። ነገር ግን *ዛሬም* ጠላቶቻችንን በፍቅርና በምሕረት ስናስተናግዳቸው፥ በረከትን እንወርሳለን። በረከትን ለእነርሱ በማካፈል፥ እኛም በረከትን እንቀበላለን! ለአንድ አማኝ ስደት መንፈሳዊ ማዕድ ነው። በቤተ ክርስቲያን *ታሪክ* ውስጥ የምናያቸው ቅዱሳንና ሰማዕታት ይህንን እውነት ይመሰክራሉ።

እርስ በርሳችን ልንዋደድ፥ ጠላቶቻችንን ልንወድና *ሕይወትን ልናፈቅር* ይገባናል (1ኛ ጴጥ. 3:10-12)። የስደት አይቀሬነት አንድን አማኝ በሕይወት ተስፋ እንዲቆርጥ ሊያደርገው አይገባም። በሌሎች ዘንድ «ክፉ ቀናት» የተባሉት ከላይ የተጠቀሱትን ለሚያሟላ ክርስቲያን «በጎ ቀናት» ይሆኑለታል።

በመጀመሪያ፥ *ሕይወትን ለማፍቀር መወሰን አለብን።* ይህ ደግሞ የፈቃድ ጉዳይ ነው። «ሕይወትን ሊወድ. . .የሚፈልግ»። ይህም በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ የተሻለውን የሚያይ የእምነት ክፍል ነው። በመጽሐፈ መክብብ ከተገለጸውና «ሕይወትን ጠላሁ ሁሉም ከንቱ ነፋስንም እንደመከተል ነው» (2:17) በማለት ተስፋን ከሚያጨልመው አሳብ ጋር የሚቃረን ነው። ሕይወትን በመታገሥ ሸክም ልናደርገው ወይም ከጦርነት እንደሚሸሽ ሮጠን *ልናመልጠው*፥ ወይም እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚቆጣጠር በማወቃችን *ልንደሰትበት* እንችላለን። ጴጥሮስ ከእውነት የራቀና እውነታን የማይቀበል የሥነ

ልቦና ጂምናስቲክ አይደለም ያቀረበው። ነገር ግን አንባቢዎቹ ለሕይወት ቀና አመለካከት እንዲኖራቸውና በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ *በእምነት* የሚበልጠውን ነገር እንዲያገኙ ያደፋፍራል።

በሁለተኛ ደረጃ፥ *አንደበታችንን መግታት አለብን።* በሕይወታችን ችግር የሚፈጥሩት ነገሮች ምክንያታቸው በተሳሳተ መንፈስ ውስጥ ሆነን የምንናገራቸው ቃላት ናቸው። እያንዳንዱ ክርስቲያን ያዕቆብ 3ን በየቀኑ እያነበበ መዝሙር (141)፡3ን ደግሞ መጸለይ አለበት። ጴጥሮስ የጥድፊያ ንግግር የሚያስከትለውን በሚገባ ተረድቷል! በቅዱሳን ሕይወት ውሸት ስፍራ የለውም።

በሦስተኛ ደረጃ፥ *መልካምን እያደረግን ክፋትን መጥላት አለብን።* አንድን ነገር የማንፈልገውና ከሕይወታችን የምናስወግደው ስለምንጠላው ነው። አንድን ኃጢአት ገሸሽ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፥ ስለምንጠላው መራቅም አለብን።

በመጨረሻም፥ *ሰላምን ልንፈልግ ያሻናል።* «የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና» (ማቴ. 5፡9)። ወጣ ብለን ጠብን ብንፈልግ እናገኘዋለን፤ እንዲሁም ሰላምን ብንሻ እናገኘዋለን። ይህ ማለት ግን «የተከፈለው መሥዋዕትነት ተከፍሎ የሚገኝ ሰላም» ማለት ግን አይደለም። ምክንያቱም የሰላም መሠረት ጽድቅ መሆን አለበት (ያዕቆብ 3፡13–18)። በቀላል ቋንቋ ሲነገር፥ አንድ ክርስቲያን ከሰዎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት እኔ ያልኩት ካልሆነ በማለት ችግር የሚፈጥር ሳይሆን፥ ማዕከሉን የሚጠብቅ መሆን አለበት ማለት ነው። «ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ» (ሮሜ 12፡18)። አንዳንድ ጊዜ ግን ያስቸግራል! ሮሜ 14፡19ን አንብቡ፤ ባለንበት ሁኔታ ውስጥ ሰላምን ለማስፈን ጠንክረን መሥራት እንዳለብን ተነግሮናል። በሰላም መኖር ሳይታሰብ በድንገት የሚመጣ ነገር አይደለምና።

«ነገር ግን በስደት ውስጥ ያለ ክርስቲያን ጠላቶቻችን እኛን ለማጥቃት ይህን ሁኔታ ቢጠቀሙበትስ?» በማለት ይጠይቅ ይሆናል። «እኛ ሰላም ብንፈልግም እነርሱ ግን ሁልጊዜ ጠብ ቢፈልጉስ!»። ጴጥሮስ ሲመክራቸው የእግዚአብሔር ዓይኖች በሕዝቡ ላይ ጆሮዎቹም ለጸሎታቸው የተከፈቱ መሆናቸውን ያረጋግጥላቸዋል (ጴጥሮስ ይህንን የተማረው ኢየሱስን ሳያይ በውኃ ላይ ለመሄድ በሞከረ ጊዜ ነበር– ማቴ. 14፡22–33)። እግዚአብሔር እኛን ከጠላቶቻችን የመጠበቅና የሚያስፈልገንን የመስጠት ብቃት ስላለው በእርሱ ልንታመን ያስፈልጋል (ሮሜ 12፡17–21)።

ጴጥሮስ እነዚህን ዓረፍተ ነገሮች የወሰደው ከመዝሙረ ዳዊት (34)፡12–15 በመሆኑ፥ ሙሉውን መዝሙር ማንበቡ ይጠቅማችኋል። በእግዚአብሔር በኩል «በጎ ዘመን» ምን ማለት እንደሆነ ይገልጸዋል። ቀኖቹ የግድ ከችግር ነፃ የሆኑ ላይሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱም ዘማሪው ስለ ፍርሃቶች (ቁ. 4)፥ ችግሮች (ቁ. 6፥ 17)፥ ጭንቀቶች (ቁ. 19)፥ እና ስለተሰበረ ልብ ይናገራል (ቁ. 18)። «በጎ ዘመን» «ሕይወትን ለሚወድ» አማኝ ተከልሎና ተደላድሎ የሚኖርበት ኑሮ ሳይሆን፥ በሕይወቱ በሚገጥሙት ችግርና መከራ መሃል የእግዚአብሔርን ርዳታና በረከት ሲለማመድ ማለት ነው። በዚህም ወቅት ጌታን ያከብራል (ቁ. 1–3)፥ የጸሎቱን መልስ ያገኛል (ከቁ. 4–7)፥ የእግዚአብሔርን መልካምነት ያጣጥማል (ቁ. 8)፥ እንዲሁም እግዚአብሔር ቅርብ እንደሆነ ይረዳል (ቁ. 18)።

በሚቀጥለው ጊዜ «ክፉ ቀን» ያጋጠማችሁ ሲመስላችሁና ሕይወት ሲያስጠላችሁ መዝሙር (34)ን ስታነቡ ለእግዚአብሔር ክብር «በበጎ ዘመን» ውስጥ እንዳላችሁ ትረዳላችሁ!

## 2. የክርስቶስን ጌትነት ተለማመዱ (3፡13–15)

እነዚህ ቁጥሮች 1ኛ ጴጥሮስ በመከራ ውስጥ ስለሚገለጥ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያስተምረውን ሦስተኛ ክፍል ያስታውቁናል። እግዚአብሔርን መፍራት ማናቸውንም ፍርሃት ድል እንደሚነሣ የሚገልጠውን ጠቃሚ መርሆ ያስታውቃሉ። ጴጥሮስም ተግሣጹን ለማጠናከር ከኢሳይያስ 8፡13–14 ይጠቅሳል– «ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስን በልባችሁ ቀድሱት» (3፡15)።

የኢሳይያስ ትንቢት እዚህ ጋ መጠቀሱ በጣም ጠቃሚ ነው። የይሁዳ ንጉሥ የነበረው አካዝ በአሦር ሠራዊት ተከብቦ ግራ ተጋብቶ ነበር። እስራኤልና ሶርያ ከእነርሱ ጋር ይተባበር ዘንድ፥ አካዝን ጠይቀውት ነበር፤ እርሱ ግን አልተባበርም አለ። ስለዚህም እስራኤልና ሶርያ ይሁዳን ለመውረር ሞከሩ። ነገር ግን በድብቅ አካዝ ከአሦራውያን ጋር ተስማማ። ነቢዩ ኢሳይያስም ፥ አካዝ እግዚአብሔር የማይወደውን የኅብረት ስምምነት በማድረጉ አስጠንቅቆታል፤ በእግዚአብሔር ብቻ እንዲታመን መክሮታል። «የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን ቀድሱት፤ የሚያስፈራችሁና የሚያስደነግጣችሁም እርሱ ይሁን» (ኢሳ. 8፡13)።

እንደ ክርስቲያን አንዳንዴ አጣብቂኝ ውስጥ እንገባለን፥ በፍርሃትም ተንጠን የተሳሳቱ ውሳኔዎችን እናደርጋለን። ነገር ግን፥ በልባችን «ክርስቶስን ጌታ አድርገን ብንቀድሰው» ሰዎችንም ሆነ ሁኔታዎችን አንፈራቸውም። ጠላቶቻችን ሊያጠቁን ይችላሉ፥ ነገር ግን የበለጠ የምንጎዳው በእግዚአብሔር ከመታመን ስናቆም ነው። በጥቅሉ

ስናየው፥ ደግ የምናደርግ ከሆነ ሰዎች አይቃወሙንም፥ ሆኖም ግን ለተቃውሞ ቢነሡብንም እንኳ፥ ምስክርነታችንን ተመቻምቸን ከማበላሸት ይልቅ፥ ስለ ጽድቅ መከራ ብንቀበል ይሻለናል። ጴጥሮስ ይህንን መሪ አሳብ በምዕራፍ 4፡12–19 በዝርዝር አቅርቦታል።

ከጠላት ጋር ስንፋለም፥ ኢየሱስ ክርስቶስን በልባችን ካነገሥነው በፍርሃት ከመራድ ይልቅ እንባረካለን። በቁጥር 14 ላይ «ብፁዓን» ናችሁ የሚለው ቃል በማቴዎስ 5፡10 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህም «ከመነገር የሚያልፍ ክብር የሞላበት ሐሤት» አንዱ ክፍል ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡8)።

ጌታ ኢየሱስ የሕይወታችን ጌታ ሲሆን እያንዳንዱ የኑሮ ቀውስ ለምስክርነት የተሻለ ዕድል ይሰጠናል። «ዕቃቤ» የሚለው የአማርኛ ቃል መልስ መስጠትን እንጂ ንስሐ መግባትን አያመለክትም። ይህም የሚሰጠው በፍትሕ አደባባይ ነው። እምነታችንን የምንመለከትበት የሥነ መለኮት ጥናት ዘርፍ «አፖሎጀቲክስ» ይባላል። ተስፋ በተቆረጠባቸው ነገሮች ላይ እያንዳንዱ አማኝ በውስጡ ስላለው ተስፋ መልስ ለመስጠት የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል። አንድ ችግር ሲፈጠር፥ አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ቁጭ ብለው ፍጻሜውን ብቻ ስለሚጠባበቁ ይህ ሁኔታ አማኙ በእምነትና በተስፋ ተሞልቶ እንዲመሰክር በር ይከፍትለታል።

ይህ ምስክርነትም በፍርሃትና በአክብሮት የሚሰጥ እንጂ ሁሉን አውቃለሁ በሚል ባሕርይ ሊቀርብ አይገባም። እኛ ምስክሮች እንጂ ጠበቃዎች አይደለንም። መጠንቀቅ ያለብን ሕይወታችን ዕቃቤአችንን ማገዙ ላይ ነው። ጴጥሮስ የመከረን ክርስቲያኖች ከማያምኑ ጋር እንዲከራከሩ ሳይሆን፥ የምናምነውን ለምን እንደምናምን በፍቅር ላልዳኑት ማቅረብ ነው። ዋና ዓላማው በክርክር ማሸነፍ ሳይሆን፥ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ መንግሥት ማምጣት ነው።

«ክርስቶስን በልባችሁ ቀድሱት» ምን ማለት ነው? ሁሉን ነገር ለእርሱ አስረክቦ፥ እርሱን ለማስደሰትና ለማክበር መኖር ማለት ነው። ይህም ሰዎች የሚያደርጉብንን ከፋት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር የማይደሰትባቸውን ነገሮች መፍራት ነው። ይህ አቀራረብ በሚያስገርም ሁኔታ ሕይወታችንን የቱን ያህል የተስተካከለ ያደርገው ይሆን! የሚገኝበትን ትርፍ በመቀመር ሳይሆን ማቴዎስ 6፡33 ና ሮሜ 12፡1–2 ያጣመረ የእግዚአብሔር ቃል የሚታዘዝ የዕለት ተዕለት የእምነት ባሕርይ ነው። ይህም በሕይወታችን በሚፈጸመው የእግዚአብሔር ፈቃድ መርካት ነው (ዮሐ. 4፡31–34)። ጌታ ኢየሱስ የሕይወታችን ጌታ የመሆኑ አንደኛው ማረጋገጫ ለሌሎች ስለ እርሱ

በመንገር ወደ መንግሥቱ እንዲመጡ ለመመስከር ያለን ዝግጁነትና መሻት ነው።

## 3. በጎ ሕሊና ይኑራችሁ (3፡16–17)

«ሕሊና» የሚለው ቃል ከእውቀት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሕሊናችን ውስጣዊ ፍርድን የሚሰጠን ምስክር፥ በሥራችን የምንወድስበት ወይም ደግሞ የምንወቀስበት እንደሆነ እንድናውቅ የሚረዳን ክፍል ነው (ሮሜ 2፡14–15ን ይመልከቱ)። ሕሊናችን የእግዚአብሔርን እውነት በሚያስገባ መስኮት ሊመሰል ይችላል። ባለመታዘዝ ብንጸና መስኮቱ ብርሃን እስከማያሳልፍ ድረስ ይሆናል። ይህም «ለረከሰ ሕሊና» ይዳርገናል (ቲቶ 1፡15)። «የደነዘዘ ሕሊና» ደግሞ ደጋግሞ ኃጢአት በመሥራቱ፥ ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን መለየት እስከማይችል ድረስ የማይሰማው ነው (1ኛ ጢሞ. 4፡2)። ሕሊናችን ዓመፅን እያጸደቀ መልካም የሚያደርጉትን የሚኮንን ከሆነ ይመረዛል። መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ ዓይነቱን «ክፉ ሕሊና» ብሎ ይጠራዋል (ዕብ. 10፡22)። አንድ ወንጀለኛ በጓደኞቹ ላይ ቢጮኽ፥ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማዋል፥ ነገር ግን በሚሠራው ወንጀል ውጤታማ ከሆነ ይደሰታል።

ሕሊና በመስኮት አልፎ በሚመጣው የብርሃን እውቀት ይታገዛል። አንድ አማኝ ቃሉን ሲያጠና የእግዚአብሔርን ፈቃድ በተሻለ ሁኔታ ይረዳል፤ ሕሊናውም መልካምና ክፉን ለመለየት የሚያስችል ዐቅም ይኖረዋል። «በጎ ሕሊና» ክፉ ለማድረግ ስናስብ የሚወቅሰን፥ ትክክል ስንሠራ ደግሞ ሥራችንን የሚያጸድቅ ነው። ሕሊናን ጠንካራና ንጹሕ ለማድረግ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል (የሐዋ. ሥራ. 24፡16)። በመንፈሳዊ እውቀትና በመታዘዝ ካላደግን፥ በጥቃቅን ነገር የሚበሳጭ «ደካማ ሕሊና» እናዳብራለን (1ኛ ቆሮ. 8)።

በጎ ሕሊና አንድን አማኝ በፈተና ጊዜያት እንዴት ሊያግዘው ይችላል? በሰዎችና በእግዚአብሔር ፊት መልካምን እንዳደረገ ስለሚያውቅ ያበረታታዋል፤ ስለዚህ አማኙ አይፈራም። በጀርመን አገር በወርምስ በማርቲን ሉተር መቃብር መታሰቢያ ላይ የተጻፈው ሚያዝያ 18 ቀን 1521 ለቤተ ክርስቲያን ጉባዔ የተናገረው ቃል ነው፤ «በፊታችሁ ቆሜያለሁ፤ ከዚህ ሌላ ምንም ለማድረግ አልችልም። እግዚአብሔር ይርዳኝ። አሜን»! ሕሊናው በእግዚአብሔር ቃል ስለታጠረ፥ ያለአግባብ የምትጓዘውን ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ለመቃወም ድፍረትን ሰጠው!

በጎ ሕሊና ለልባችን ሰላምን ይሰጠናል፤ በውስጣችን ሰላም ካለን ደግሞ ከውጭ ያለውን ጦርነት ያለ ፍርሃት እንገጥማለን። ቅብጥብጥ ሕሊና ልብን በመከፋፈል የሰውን ድፍረት ይሰርቃል፤ ከዚህ የተነሣም

የሚገባውን ያህል ሠርቶ ውጤታማ አይሆንም። ሕሊናችን እየወቀሰን ስለ ክርስቶስ በድፍረት እንዴት መመስከር እንችላለን?

በጎ ሕሊና ሰዎች ስለ እኛ ምን ይላሉ፥ ምንስ ያውቃሉ፥ ምንስ ያደርጉናል የሚለውን ፍርሃት ከውስጣችን ይነቅላል። ክርስቶስ ጌታችን ሆኖ እግዚአብሔርን ብቻ የምንፈራ ከሆነ፥ የጠላቶቻችን ዛቻ፥ አሳብ፥ ወይም ድርጊት ልንፈራ አይገባም። «እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፤ አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?» እንላለን [መዝ. (118):6]። ጴጥሮስ በፈታና የወደቀው ጠላትን በመፍራቱና ጌታን በመካዱ ነው።

ጴጥሮስ በግልጽ እንዳስቀመጠው ክፉና በጎን መለያ መንገዱ ሕሊና ብቻ አይደለም። አንድ ሰው «በበጎ ሥራ» ወይም «ክፉ ሥራ» ሊሰማራ ይችላል። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሳይታዘዝ ሕሊናዬ ምንም ስላልወቀሰኝ ትክክል ነኝ የሚል ከሆነ፥ ይህ ሰው ሕሊናው በመሠረታዊ ቀውስ ውስጥ መሆኑን እያስረገጠ ነው። ሕሊና ትክክለኛ ምሪት የሚሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ አስተማሪው ሲሆን ነው።

በአሁኑ ዘመን በኅብረተሰቡ ውስጥ ብዙ ክርስቲያኖች በሐሰት ይከሰሳሉ። የእኛ መመዘኛዎች ባልዳነው ዓለም ያሉት አይደሉም። በመሠረቱ ክርስቲያኖች ችግር ፈጣሪዎች አይደሉም። ነገር ግን ያሉትን ችግሮች በትክክል ይገልጧቸዋል። አንድ ዳግም የተወለደ ሰው በአንድ ቢሮ መሥራት ቢጀምር፥ ወይም በአንድ ኮሌጅ ወዳለ መኝታ ክፍል ቢዛወር በአጭር ጊዜ ውስጥ ችግሮች ይገለጣሉ። ክርስቲያኖች ለጨለማው ዓለም ብርሃን ናቸው (ፊልጵ. 2:15)፥ ስለዚህም «ፍሬ የሌለውን የጨለማ ሥራ» ይገልጡታል (ኤፌ. 5:11)።

ዮሴፍ በጶጢፋራ ቤት ሲያገለግልና ኃጢአት ለማድረግ እምቢ ሲል በሐሰት ተከሶ በወኅኒ ተጥሏል። በባቢሎን የነበሩ የመንግሥት ባለሥልጣናት ሕይወቱና ሥራው የእነርሱን ክፉ ሥራ ስለሚገልጥና ምስክር ስለሆነባቸው፥ ዳንኤልን ችግር ውስጥ ለመክተት ዐቀዱ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ኑሮው የሰዎችን ኃጢአተኛ ልብና ሥራ ስለገለጠባቸው ሰቀሉት (ዮሐ. 15:18–25ን ይመልከቱ)። «በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ» (2ኛ ጢሞ. 3:12)።

በጎ ሕሊና እንዲኖረን ከፈለግን፥ በሕይወታችን ያለውን ኃጢአት መናዘዝ ያስፈልገናል (1ኛ ዮሐ. 1:9)። «መስኮቱን በንጽሕና መጠበቅ» አለብን። የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ ጊዜን በመስጠት «ብርሃኑን ማስገባት» አለብን። በሳል ሕሊና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ መታዘዝ

ሲሆን፥ አንድን ክርስቲያን ላልዳኑት እንዲመሰክር ያበረታታዋል። በስደትና በመከራ ወቅት ብርታትን ይሰጠናል።

ማንም ክርስቲያን ክፉ አድርጎ መከራን መቀበል የለበትም፤ ነገር ግን በጎ አድርጎ መከራን ቢቀበል መደንገጥ አይኖርበትም። ዓለማችን ምስቅልቅሷ የወጣ በመሆኑ ሰዎች «ክፉን መልካም፥ መልካሙን ደግሞ ክፉ» እንዲሁም «ጨለማውን ብርሃን ብርሃኑንም ጨለማ» ብለው ይጠራሉ (ኢሳ. 5፡20)። ኢየሱስ በኖረበት ዘመን የነበሩት የሃይማኖት መሪዎች ክርስቶስን «ክፉ አድራጊ» ብለው ጠሩት (ዮሐ. 18፡29-30)። ይህ ሰዎች ምን ያህል ሊሳሳቱ እንደሚችሉ የሚያሳይ ነው።

የችግር ዘመን በቤተ ክርስቲያን ሲመጣ፥ ክርስቲያናዊ ፍቅርን ማሳደግ አለብን፤ ምክንያቱም ከፊት ይልቅ የወገኖች ማበረታቻና ርዳታ ያስፈልገናልና ነው። በጎ ሕሊና ሊኖረንም ይገባል፥ ምክንያቱም በጎ ሕሊና እንደ ጀርባ አጥንት ጠንካራና ደፋር ምስክር ያደርገናል። ምሥጢሩም የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት በየዕለቱ መለማመድ ነው። እግዚአብሔርን የምንፈራ ከሆነ፥ ሰዎችን ልንፈራ አይገባም። «ኀፍረት የሚመጣው ሰዎችን ከመፍራት ነው» በማለት ሳሙኤል ጆንሰን ተናግሯል። «በጎ ሕሊና የሚገኘው ግን እግዚአብሔርን በመፍራት ነው።»

# 8

# ከኖኅ እንማር

(1ኛ ጴጥሮስ 3፥18–22)

አንድ መጋቢ በማቴዎስ 16፥18 ላይ ጌታ ለጴጥሮስ «አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም።» በማለት ስለተናገረው ቃል ሲያብራራ፥ አንዲት ሴት በትርጉሙ ብዛት ተደንቃ «መጋቢ፥ ኢየሱስ ይህንን ያህል ችግር እንደሚያመጣ ቢያውቅ ኖሮ እነዚህን ቃላት ባልተናገረ ነበር» አለችው።

ጴጥሮስም ይህንን ክፍል ሲጽፍ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉ አስቸጋሪ ምንባቦች አንዱ ሊሆን እንደሚችል አላሰበም ነበር። መልካምና የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች በዚህ ክፍል ትርጉም ተከራክረዋል፥ ሆኖም አልተግባቡም። እኛ በዚህ ምንባብ ላሉት ችግሮች ሁሉ መፍትሔ መስጠት ባንችልም፥ ጴጥሮስ በመከራ ወቅቶች ክርስቲያኖችን ለማበረታታት የሰጠውን ተግባራዊ ዕገዛ ለማየት እንሞክራለን።

ክፍሉ ሦስት የተለያዩ አገልግሎቶችን ያቀርብልናል። የእነዚህን አገልግሎቶች ምንነት ከተረዳን፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መከራ ለመቀበልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ለመኖር እንችላለን።

## 1. የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት

በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ነገር በሙሉ ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመናገር ከፈለገው ነገር ወጣ ያለ ቢሆንም፥ ከምዕራፍ 2፥21 ጋር ይመሳሰላል። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የታዘዘና ያለ አግባብ መከራን ለመቀበል ምሳሌ አድርጎ ጴጥሮስ ያቀርበዋል።

*ሀ. የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት (3፥18)።* በቁጥር 17 ላይ ከክፉ ይልቅ መልካም አድርጎ መከራ መቀበል እንደሚሻል ሲጽፍ፥ ጻድቅ ሆኖ ሳለ በኃጢአተኞች እጅ መከራ የተቀበለውን የኢየሱስን ምሳሌነት በመጥቀስ ነው (የሐዋ. ሥራ 3፥14)። ኢየሱስ ለሞት አልፎ የተሰጠበት ምክንያት አንድ ጊዜ ስለ ኃጢአተኞች መሥዋዕት ሆኖ እነርሱን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ ነው (1ኛ ጴጥ. 2፥24፤ ዕብ. 9፥24–28)። ስለ ራሱ ሳይሆን ለሌሎች ኃጢአት ምትክ በመሆን ሞተ፥ መልካም ነገርን በማድረግ መከራ ተቀበለ፤ እርሱ ምንም ኃጢአት አልሠራምና (1ኛ ጴጥ. 2፥22)።

«ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ» የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ስንቀርብ አድማጭ ማግኘታችንን የሚያሳይ ነው (ኤፌ. 2፡18፤ 3፡12፤ ዕብ. 10፡19፤ ሮሜ 5፡2)። የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች መቀደዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰው በር መከፈቱን ያመለክታል።

*ለ. የኢየሱስ ክርስቶስ ስብከት (3፡19–20)።* «በመንፈስ ሕያው ሆነ» በሚለው ሐረግ ውስጥ መንፈስ የሚለው ቃል ምንን እንደሚያመለክት ለመለየት ብንቸገርም፥ የግሪክ አዋቂ ምሁራን እንደሚያስረዱት በቁጥር 18 መጨረሻ ላይ «በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» ተብለው የተነጻጸሩት ሥጋና መንፈስ ናቸው። የዚህ ዓይነቱ ንጽጽር በማቴዎስ 26፡41 እና በሮሜ 1፡3–4 ላይም ቀርቧል። ስለዚህ ንጽጽሩ በኢየሱስ ሥጋና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ሳይሆን፥ በሚሞት ሥጋና ሕያው በሚሆን መንፈስ መካከል ነው።

ጌታችን ሥጋ (ማቴ. 26፡6)፥ ነፍስ (ዮሐ. 12፡27) እና መንፈስ (ሉቃ. 23፡46) አለው። ኢየሱስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው እንጂ አምላክ ያደረበት ሰው አይደለም። እግዚአብሔር ስለ እኛ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ኃጢአት አደረገው (ማር. 15፡34፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)። ክርስቶስም በመስቀል ላይ ነፍሱን ለአባቱ አሳልፎ ሰጠ (ሉቃ. 23፡46፤ ያዕ. 2፡26)።

ኢየሱስ የደኅንነቱን መልእክት ያመጣው ለእነማን ነው? ጴጥሮስ «ነፍሳት» ያለው ሰዎችን ነው እንጂ መናፍስትን አይደለም (3፡20) በአዲስ ኪዳን «መናፍስት» የሚለው ቃል መላእክትን ወይም አጋንንትን እንጂ ሰዎችን አያመለክትም። ቁጥር 22ም ይህንኑ ትርጉም ያዘለ ይመስላል። በተጨማሪም ኢየሱስ ሲኦልን ጎብኝቷል የሚል ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱሳችን አናገኝም። የሐዋ. ሥራ 2፡31 ኢየሱስ ወደ መቃብር እንደሚሄድ ይናገራል። ይህ ግን ሲኦልን የሚያመለክት አይደለም። «መቃብር» የሙታንን ዓለም የሚያመለክት ነው። እስከ ትንሣኤ ድረስ የሚቆዩበትን ጊዜያዊ ሥፍራ የሚያሳይ ነው (ራእ. 20፡11–15)። ከአዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (New American Standard Bible) እና ከአዲሱ ዓለም አቀፍ ትርጉም (New International Version) መጽሐፍ ቅዱሶች በመመልከት ልዩነቱን ማግኘት ትችላለህ። ሲኦል የመጨረሻና ቋሚ የሆነ ያላመኑት ሰዎች የሚቀጡበት ቦታ ነው። ክርስቲያን ሲሞት፥ ወደ ሲኦል አይሄድም፤ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ለመሆን ወደ ሰማይ ይሄዳል (ፊልጵ. 1፡20–24)።

ጴጥሮስ እንደ ጻፈው ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው መካከል «በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት» ሰብኳል። ጌታ የሰበከው ለእነማን ነው? የሰበከላቸው ምን ነበር? የሚሉ ጥያቄዎች መነሣታቸው አይቀርም። ቀድሞ እንደተገለጸው ይህ ክፍል አስቸጋሪ በመሆኑ አንድ ወጥ የሆነና ሁሉም የሚግባቡበት ትርጓሜ የለም። «ኢየሱስ ክርስቶስ የሰበከው ለእነማን ነው?» የሚለው ጥያቄ ሁለት ዓይነት ምላሽ ተሰጥቶታል። አንደኛው ምላሽ ኢየሱስ የሰበከው በሲኦል ውስጥ ለሚኖሩ በኃጢአታቸው ለጠፉ ሙታን ነው የሚል ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ኢየሱስ የሰበከው ምናልባት በሲኦል ላሉ የወደቁ መላእክት ሳይሆን አይቀርም (ይሁዳ 6) ይህም ከጥፋት ውኃ በፊት ከነበረው ዘመን ጋር የሚጋጠም ነው። «ሰበከላቸው» የሚለው ቃል ማወጁን እንጂ ወንጌል መስበክን አያመለክትም። ስለዚህ መልእክቱ ክርስቶስ በሰይጣንና በመላእክቱ ላይ ያገኘውን ድል ለማወጅ ነው። ጴጥሮስ ለታሰሩት መናፍስት ምን እንደሰበከላቸው ባይነግረንም፥ መላእክት ደኅንነት ስለማያገኙ፥ የደኅንነት መልእክት ሊሆን እንደማይችል የተረጋገጠ ነው (ዕብ. 2፡16)። (1ኛ ጴጥ. 3፡22 እና ቆላ. 2፡15 ይመልከቱ።)

ከጥፋት ውኃ ዘመን በፊት የነበሩት ከእነዚህ ጋር እንዴት እንደሚገናኙ ጴጥሮስ አይነግረንም። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ግን በዘፍጥረት 6፡1-4 «የእግዚአብሔር ልጆች» ተብለው የተጠቀሱትና የሰውን ልጆች አግብተው ስማቸው የታወቀ ኃያላንን የወለዱት የወደቁት መላእክት ናቸው ብለው ያምናሉ። በሌላ በኩል ደግሞ «የእግዚአብሔር ልጆች» የሚለው ቅዱሳን መላእክትን እንጂ ክፉ መላእክትን አያመለክትም (ኢዮብ. 1፡6፥ 2፡1) ይላሉ። ከጥፋት ውኃ በፊት የነበረው ዓለም እጅግ ክፉ ስለነበር እነዚህ መናፍስት ከዚያ ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው አይቀርም የሚል አመለካከትም አለ (ዘፍ. 6፡5-13፤ ሮሜ 1፡18ን ይመልከቱ)።

*ሐ. የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ (3፡21)።* ሞት የሚመጣው፥ መንፈስ ከሥጋ ሲለይ (ያዕ. 2፡26) እንደመሆኑ መጠን፥ ትንሣኤ ደግሞ መንፈስ ወደ ሥጋ መመለስ ነው (ሉቃስ 8፡55)። አብ ኢየሱስን ከሙታን አስነሥቶታል (ሮሜ 6፡4፥ 8፡11)፥ ነገር ግን ኢየሱስም ራሱን ከሞት የማስነሣት ሥልጣን ነበረው (ዮሐ. 10፡17-18)። ይህ ተአምር ነው! ክርስቲያኖች «ሕያው ተስፋ» ያላቸው በክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያት ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡3-4)። የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ከኖኅ ጋር ያለውን ግንኙነት ከፊት ባሉት ክፍሎች እንመለከታለን።

የትንሣኤን አስፈላጊነት ዝቅ አድርገን ማየት የለብንም። ትንሣኤ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር መሆኑን ያውጃል (ሮሜ 1፡4)። የደኅንነት ሥራ በእርሱ ተከናውኖ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ

ተቀባይነትን አግኝቷል (ሮሜ 4፡25)። ሞትም ድል ተነሥቷል (1ኛ ተሰ. 4፡13-18፤ ራእ. 1፡17-18)። የወንጌሉ መልእክት ትንሣኤን የሚያካትት ነው (1ኛ ቆሮ. 15፡1-4)። ሞቶ የቀረ አዳኝ ሌሎችን ማዳን አይችልም። በየዕለቱ በሕይወታችንና በአገልግሎታችን የሚያስፈልገንን ኃይል የሚሰጠን ሞትን ያሸነፈው ኢየሱስ ነው (ገላ. 2፡20)።

*መ. የኢየሱስ ክርስቶስ እርገት (3፡22)።* ጌታ ትንሣኤው ከሆነ ከአርባ ቀን በኋላ፥ በክብር ቦታው በአብ ቀኝ ለመቀመጥ ወደ ሰማይ አረገ [መዝ. (110)፡1፤ ፊልጵ. 2፡5-11፤ ዕብ. 12፡1-3፤ የሐዋ. ሥራ 2፡34-36]። አማኞችም ከእርሱ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጠዋል (ኤፌ. 2፡4-6)፤ በእርሱም በኩል በሕይወት ይነግሣሉ (ሮሜ 5፡17)። እርሱ የቤተ ክርስቲያን ሊቀ ካህን እና (ዕብ. 7፡25፤ 4፡14-16) ጠበቃ (1ኛ ዮሐ. 1፡9-2፡2) ሆኖ ያገለግላል። በሰማይ ለልጆቹ ቦታን ያዘጋጃል (ዮሐ. 14፡1-6)፥ አንድ ቀን ተመልሶም ልጆቹን ወደ እርሱ ይወስዳቸዋል።

በዚህ ምንባብ የጴጥሮስ ዋና ትኩረት ክርስቶስ «በመላእክት፥ በሥልጣናትና በኃይላት» ሁሉ ላይ ስለተቀዳጀው ሙሉ ድል ነው (1ኛ ጴጥ. 3፡22)፥ ይህም በክፋት የሰይጣን ሠራዊቶች ላይ ነው (ኤፌ. 6፡10-12፤ ቆላ. 2፡15)። ያልወደቁት መላእክት ምንጊዜም የእግዚአብሔር ናቸው። እንደ ክርስቲያኖች ለድል ሳይሆን የምንዋጋው ከድል ነው— ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ፥ በትንሣኤውና በእርገቱ ካስገኘልን ድል በመነሣት ነው የምንዋጋው።

## 2. የኖኅ አገልግሎት

ኖኅ በእነ ጴጥሮስ ዘመን በአይሁድም ሆነ በክርስቲያኖች ዘንድ የተከበረ ሰው ነበር። ከዳንኤልና ከኢዮብ ጋርም ተያይዞ ተጠቅሷል (ሕዝ. 14፡19-20)። በመዝሙርና በነቢያት መጻሕፍትም ስለ ጥፋት ውኃ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። ኢየሱስ ክርስቶስም ከምጽአቱ ትንቢታዊ ትምህርት ጋር አያይዞ ኖኅን ጠቅሶታል (ማቴ. 24፡37-39፤ ሉቃስ 17፡26-27)። ጴጥሮስ ደግሞ በዚህ ክፍልና በሁለተኛው መልእክቱ (2፡5፤ 3፡6) ላይ ጠቅሶታል። ኖኅ ከእምነት አርበኞችም ጋር ተጠቅሷል (ዕብ. 11፡7)።

ጴጥሮስ በኖኅና መልእክቱን በጻፈላቸው ሰዎች መካከል የተመለከተው ግንኙነት ምንድን ነበር? ኖኅ በአስቸጋሪ ወቅት ጽድቅን የሚሰብክ ሰው ነበር (2ኛ ጴጥሮስ 2፡5)። ይህ ሰው አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ የሰዎች መሳቂያና መሳለቂያ ቢሆንም፥ ለ 120 ዓመታት የእግዚአብሔርን እውነት ሰብኳል (ዘፍ. 6፡3)።

የጥንት ክርስቲያኖች ጌታ ኢየሱስ እንደተናገረው ዳግም ከመመለሱ በፊት ዓለም «እንደ ኖኅ ዘመን» እንደምትሆን ያውቃሉ (ማቴ. 24:37-39)። እነርሱም በዙሪያቸው ያለው ኅብረተሰብ አኗኗር መበላሸቱን ስለ ተመለከቱና ስደትም በመጀመሩ የጌታን ቃል አስበው ፈጥኖ እንደሚሆን ይጠባበቁ ነበር (2ኛ ጴጥ. 3:1-3)።

ኖኅ የሚሸነፍ በመሰለበት ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የታዘዘ የእምነት ሰው ነበር። ይህም ጴጥሮስ መልእክቱን ለጻፈላቸው ሰዎች አበረታች ነው። ታማኝነትን የምንለካው በስኬት ከሆነ፥ ኖኅ ያገኘው ውጤት እጅግ ዝቅተኛ ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከፍተኛ ደረጃ ሰጥቶታል።

ጴጥሮስ በኖኅ ዘመን የነበረውን ውኃ ከክርስቲያን ጥምቀት ጋር ያገናኘዋል። እናንተ የቱንም ዓይነት የጥምቀት ሥርዓት ብትከተሉ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ግን የምታጠምቀው በማጥለቅ ነበር። ይህ ደግሞ የጌታችንን ሞት፥ በመቃብር መቆየቱንና የትንሣኤውን ምሳሌነት ያዘለ ነው። ጥምቀት ካለፈው ታሪክ ጋር የነበረን ግንኙነት መቋረጥን ያመለክታል። የተለወጠው ሰው የሚለየው ከቤተሰብ፥ ከጓደኛና ከሥራ ሊሆን ይችላል። ለጥምቀት የሚዘጋጁት ሰዎች በጥንቃቄ መጠይቆች ይቀርቡላቸዋል። ምክንያቱም በመጠመቅ የሚያሳዩት መታዘዝ የቅድስናቸው አንድ ደረጃ እንጂ የቤተ ክርስቲያን «አባል» ለመሆን «የሚያስችል ሥርዓት» አይደለም።

የጥፋት ውኃ የክርስቶስ ሞት፥ የመቃብር ውስጥ ቆይታውና የትንሣኤው ተምሳሌት ነው። የጥፋት ውኃው መሬትን በፍርድ ሲውጣት ኖኅንና ቤተሰቦቹን ግን አንሳፍፎአቸዋል። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በኖኅ መርከብ ውስጥ የደኅንነትን ምሳሌ ታመለክታለች። ኖኅና ቤተሰቦቹ በእምነት መርከብ ውስጥ በመግባታቸው ዳኑ፥ ኃጢአተኞችም በክርስቶስ በማመንና ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን ይድናሉ።

ጴጥሮስ ኖኅና ቤተሰቦቹ «በውኃ ዳኑ» ብሎ ሲጽፍ፥ ይህ ምሳሌ ደኅንነት የሚገኘው በጥምቀት አለመሆኑን አብራርቷል። ምክንያቱም ጥምቀት «መዳን ያገኘንበት የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምሳሌ ነው» (1ኛ ጴጥ. 3:21)። ውኃ በሰውነት ላይ ወይም ሰውነት በውኃ ላይ ማረፉ የኃጢአትን እድፈት አያነጻም። ይህንን ማድረግ የሚችለው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው (1ኛ ዮሐ. 1:7- 2:2)። ይሁን እንጂ ጥምቀት ከአንድ ነገር- ከመጥፎ ሕሊና ያድነናል። ጴጥሮስ በጎ ሕሊና ለውጤታማ ምስክርነት እንደሚያስፈልግ ይነግራቸዋል (1ኛ

ጴጥ. 3፥16)። የ«በጎ ሕሊና» መኖር አንዱ ክፍል ደግሞ በጥምቀት ለጌታ የገነባነውን ቃል ኪዳን መጠበቅ ነው።

ጴጥሮስ ጥምቀት የበጎ ሕሊና ልመና መሆኑን ለአንባቢዎቹ በማሳሰብ፥ በጥምቀት ሥርዓት ውስጥ የገቡትን ካለፈው የኃጢአት ኑሮ የመለየት ቃል ኪዳናቸውን መጠበቅ እንደሚገባ ይጠቁማል።

የጥፋት ውኃ የጊዜ ቅደም ተከተል ከጌታችን የትንሣኤ ቀን ጋር የተቀራረበ ግንኙነት አለው። የኖኅ መርከብ በአራራት ተራራ ላይ ያረፈችው በ7ኛው ወር በ17ኛው ቀን ነው (ዘፍ. 8፥4)። የአይሁዶች ዓመታዊ አቆጣጠር በጥቅምት ሲጀምር፥ ኃይማኖታዊው የዓመት አቆጣጠር ደግሞ በሚያዝያ በቂጣ በዓል ይጀምራል (ዘጸ. 12፥6)። ይህ ግን እስከ ሙሴ ዘመን ድረስ ተግባራዊ አልሆነም ነበር። ከጥቅምት ጀምሮ 7ኛው ወር ሚያዝያ ነው። ጌታችን የተሰቀለው በ14ኛው ቀን የቂጣ በዓል ወቅት ነበር (ዘጸ. 12፥6)፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተነሣ። ይህ ደግሞ የኖኅ መርከብ በአራራት ተራራ ወደ አረፈችበት ወደ 7ኛው ወር 17ኛው ቀን ይወስደናል። ስለዚህ የኖኅን ምሳሌ አጽንዖት ከሰጠው ከጌታችን ትንሣኤ ጋር ልናስተያየው እንችላለን።

ጌታችን በመስቀል ላይ ያደረገው የፍርድ ጥምቀት ነው። ይህም ከጥፋት ውኃ ፍርድ ጋር ይመሳሰላል (ማቴ. 20፥22፤ ሉቃስ 12፥50)። ጌታችን ሞቱን፥ የመቃብር ቆይታውንና የትንሣኤውን ሂደት ለመግለጽ የዮናስን ምሳሌነት ተጠቅሟል (ማቴ. 12፥38-41)። ኢየሱስ ከዮናስ 2፥4 በመጥቀስ በእርሱ ላይ የደረሰበትን ነገር ከዮናስ ጋር በማነጻጸር «ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ በላዬ አለፉ» ማለት ይችል ነበር።

## 3. የዚህ ዘመን ክርስቲያኖች አገልግሎት

ጴጥሮስ ለአንባቢዎቹ ያካፈላቸው ዋና ዋና ትምህርቶች በዚህ ዘመን ለምንገኝ ክርስቲያኖችም ያስፈልጉናል።

በመጀመሪያ፥ *ክርስቲያኖች ተቃውሞ እንደሚገጥማቸው መረዳት አለባቸው።* የክርስቶስ ምጽአት እየቀረበ ሲሄድ፥ መልካም ሥራችን የሰይጣንንና እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎችን ቁጣ ያነሣሣል። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ነቀፋ የሌለበትን ኑሮ ቢኖርም፥ እንደ ወንጀለኛ ተሰቅሏል። ኃጢአት የሌለበትን ኑሮ ቢኖርም፥ ጌታ ከጨካኞች መከራን ከተቀበለ እኛ እንዴት መከራን እናመልጣለን? ይሁን እንጂ መከራን የምንቀበለው ባለመታዘዝ ምክንያት ሳይሆን ስለ ጽድቅና ስለ መልካም ሥራ ስለመሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

በሁለተኛው ትምህርት ደግሞ *ክርስቲያን ጌታን ማገልገል ያለበት በእምነት እንጂ በሚያገኘው ውጤት ታምኖ መሆን የለበትም።* ኖኅ

እግዚአብሔርን ታምኖ ሰባት ሰዎችን ብቻ አዳነ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አከበረው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት በአጠቃላይ የተሸነፈ ቢመስልም የእርሱ ሞት ግን ታላቅ ድል ነበር። ዛሬም የክርስቶስ ጉዳይ የወደቀ ቢመስልም፥ ጌታ በዚህ ዓለም ውስጥ ያለውን ይፈጽማል።

*ሦስተኛ፥ የክርስቶስ ድል የእኛ ድል በመሆኑ ልንበረታታ ይገባል።* በውኃ ጥምቀት ክርስቲያኖችም ከጌታ ጋር አንድ ይሆናሉ (ሮሜ 6፤ 1ኛ ቆሮ. 12፡12–13)። በጌታ የምንኖረውና ለስሙ የምንመሰክረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው (የሐዋ. ሥራ 1፡8)። ለተቃዋሚዎቻችን ኃይል የሚሰጠው ሰይጣን ነው። እርሱ ደግሞ ሥልጣናትና ኃይላትን ድል በነሳው በክርስቶስ ተሸንፎአል። ኢየሱስ በሰማይና በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን አለው» (ማቴ. 28፡18)፥ ስለዚህ እኛ በድልና በመታመን ወደፊት ልንጓዝ እንችላለን።

ሌላው ገቢራዊ ትምህርት *ጥምቀታችን አስፈላጊ የመሆኑ ጉዳይ ነው።* ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚያደርገን፥ ካለፈው ሕይወታችን ጋር ያለን ግንኙነት የመቋረጡና በጌታ ርዳታ አዲስ ሕይወት የመጀመራችን ምልክት ነው (1ኛ ጴጥ. 4፡1–4)። ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ያለንን ዝግጁነት መግለጫ ነው። ስለዚህ የጴጥሮስን ምሳሌ ለመጠቀም እንድንችል የውል ስምምነት የሚለውን ቃል ልንቀበል እንችላለን። ጥምቀትን ማቃለል ኃጢአት ነው። በእርግጥም አንዳንዶቹ ጥምቀት ደኅንነት ያስገኛል ብለው ያስተምራሉ፤ ሌሎች ደግሞ ያቀልሉታል። ሁለቱም ትክክል አይደሉም። አማኝ በጎ ሕሊና እንዲኖረው ካስፈለገ እግዚአብሔርን ሊታዘዝ ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ ግልጽ ማድረግ የምሻው ጥምቀትን የመንፈሳዊነትና የኅብረታችን መመዘኛ እንዳናደርገው ነው። ጌታን የሚወዱ ነገር ግን በጥምቀት ጉዳይ ከእኛ አመለካከት ጋር የማይስማሙትን ወንድምና እኅቶቻችንን ልናከብርቸው ይገባል። ጄኔራል ዊልያም ብዙ «የደኅንነት ሠራዊት» (Salvation Army) ከመሠረተ በኋላ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዳትሆን የጥምቀትን ሥርዓት ለመተው ወስኖ ነበር። ኩዌከርስ የሚባለው የክርስቲያኖች ኅብረት ደግሞ ስለ ጥምቀት ትምህርት ካላቸው አስተምህሮ የተነሣ የጥምቀትን ሥርዓት አይፈጽሙም። እኔ ስለ ጥምቀት ያለኝን አቋም ገልጫለሁ። ይህን አቋሜን ግን ለሌላ ነገር መመዘኛ አላደርገውም። «እንግዲያስ ሰላም የሚሰፍንበትና እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን እንከተል» (ሮሜ 14፡19)። «እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ» (14፡5)።

ቁም ነገሩ እያንዳንዱ ክርስቲያን ለጌታ ለመገዛት ቃል መግባቱ እና ይህንም ለመተግበር ቁርጥ ውሳኔ ማድረጉ ላይ ነው። ብዙዎች ይህን ቃል ኪዳን በጥምቀት ሥርዓት ቢፈጽሙትም በጊዜ ብዛት ሊዘነጉት ወይም ሊያቃልሉት ይችላሉ። ጌታን መከተላችንን የምናረጋግጠው ዕለት በዕለት መስቀሉን ስንሸከም ነው።

በመጨረሻም፥ *ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ አዳኝ በመሆኑ የጠፋው ዓለም ወንጌልን እንዲሰማ ያስፈልጋል።* አንዳንዶች ለመፍታት አስቸጋሪ የሆነውን ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል «ከሞት በኋላ የደኅንነት ሌላ ዕድል» እንዳለ ለማሳየት ይጠቀሙበታል። በእኛ ትርጉም «የታሰሩ መናፍስት» የሚለውን መልእክት ያመለከታል ብለናል። የሞቱ ሰዎችን ነፍስ እንኳ ቢያመለክት፥ ይህ ክፍል ለደኅነታቸው ሌላ መንገድ መኖሩን የሚያሳይ አይደለም። በኖኅ ዘመን ለነበሩት ኃጢአተኞች ብቻ ክርስቶስ መዳንን ከሰጠ፥ ጴጥሮስ ወንጌልን ሰበከላቸው ከማለት ፈንታ ለምን የድል ዐዋጅ ዐወጀ አለ? ዕብራውያን 9፡27 ከሞት በኋላ የደኅንነት ዕድል እንደማይኖር ግልጽ አድርጎታል። ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ስርጭት ትኩረት መስጠት ያለባትም ለዚህ ነው። ሰምተው እምቢ ካሉት በስተቀር ብዙ ሰዎች የመዳንን የምሥራች ሳይሰሙ እየሞቱ ነው። ያመንበት ነገር ወንጌልን ለሌሎች ለማካፈል የማይቀሰቅሰን ከሆነ፥ ትርጉማቸው በሚያስቸግር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ባሉን ልዩነቶች ላይ መጨቃጨቁ ምንም ትርጉም የለውም።

ጴጥሮስ አስቸጋሪ ጊዜያቶች ለመመስከር አመቺ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥሩ ግልጽ አድርጓል።

እንዲህ ዓይነቱን አጋጣሚ እየተጠቀምንበት ነው?

# 9

# በቀሪው ዘመናችን

(1ኛ ጴጥሮስ 4፡1–11)

በአፍሪካ ኢንላንድ ሚሽን ኮንፍራንስ ላይ በመቶዎቹ የሚቆጠሩ መጋቢዎችን ለማገልገል ከባለቤቴ ጋር ኬንያ ነበርን። በረጅሙ በረራ ብንደክምም በኮንፍራንሱ ላይ መገኘታችን በጣም ስላስደሰተን ፕሮግራሙ እስከሚጀምር ድረስ መታገስ አልቻልንም ነበር።

ትዕግሥት ማጣታችንን ያዩ የኮንፍራንሱ መሪ «አሁን ያላችሁት በአፍሪካ ውስጥ ስለሆነ፥ ማድረግ ያለባችሁ የመጀመሪያው ነገር ሰዓታችሁን አውልቃችሁ መጣል ነው» አሉን።

በኬንያና በዛየር ባገለገልንባቸው ቀጣይ ቀናት የዚያን ሰው ጥበብ የተሞላ ንግግር እውነተኝነት አረጋገጥን። የሚያሳዝነው ግን ወደ አገራችን ስንመለስ በፕሮግራም ቅደም ተከተልና የጊዜ ገደብን ማክበር በሚባል የሰዓት እስራት ውስጥ ተመልሰን ገባን።

ጴጥሮስ ስለ ጊዜ ብዙ የተናገረው ነገር አለ (1፡5፥11፥17፥20፤4፡2–3፤17፤5፡6)። ለጊዜ ያለው ትኩረት በቅርብ ከሚሆነው መሥዋዕትነቱ ጋር ግንኙነት አለው (ዮሐ. 21፡15–19፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡12)። በዘላለማዊነት የሚያምን ሰው ጊዜውን በአግባቡ ይጠቀማል። ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ የምናምን ከሆነ፥ ኢየሱስ ቀድሞ ቢመጣ ወይም እኛ ቀድመን ብንሞት በሚል እምነት በጥንቃቄ ተዘጋጅተን «ቀሪውን ጊዜአችንን» ለዘላለማዊነት እንኖራለን። ደግሞም እንችላለን!

አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ዓይነት ሕይወት ሊኖር ከወደደ፥ ሊያዳብራቸው የሚያስፈልጉትን አራት ባሕርያት ጴጥሮስ ገልጾአል።

## 1. ኃጢአትን ቆርጦ ለመዋጋት ቁርጠኝነት (4፡1–3)

ሥዕላዊ መግለጫው የጦር ዕቃውን ለብሶ ለሰልፍ ራሱን ያዘጋጀ ወታደር ነው። አመለካከታችን የጦር ዕቃችን ነው። አመለካከታችን ፍጻሜያችንን ይወስናል። የተሳሳተና ደካማ አመለካከት ሽንፈትን ያመጣል። አንድ አማኝ ትክክለኛ ሕይወት እንዲኖረው ከፈለገ አመለካከቱም መስተካከል አለበት።

ከንደኞዬ ጋር በምሳ ሰዓት ከአንድ ምግብ ቤት ውስጥ ተገናኘን። ደብዛዛ መብራት ካለባቸው ቦታዎች አንዱ በመሆኑ ጠረጴዛህን እንኳን ፈልገህ ለማግኘት ባለመብራት የማዕድን ቆፋሪ ቆብ ያስፈልግሃል።

የምግብ ዝርዝሩን ያየነው ከተቀመጥን ከብዙ ደቂቃዎች በኋላ ነበር። ለጓደኛዬ ጽሑፉን በማንበቤ መገረሜን ስነግረው «ልክ ነህ ከጨለማ ጋር ለመላመድ ጊዜ አይፈጅም» አለኝ።

በዚያ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ለክርስቲያን ከኃጢአት ጋር መለማመድ ቀላል ነው የሚል የስብከት ርእስ አለ። ኃጢአትን የመጥላትና የመቃወም አመለካከት ከሌለን ሳይታወቀን ቀስ በቀስ ተዘፍቀንበት ልንገኝ እንችላለን። ቀሪውን ዘመናችንን የሚያበላሽ አንድ ነገር ቢኖር ኃጢአት ነው። በኃጢአት የሚኖር ክርስቲያን በሰይጣን እጅ ውስጥ ያለ አደገኛ መሣሪያ ነው። ጴጥሮስ ኃጢአትን ከሕይወታችን መቃወም እንዳለብን ሊያስረዱ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶችን አቅርቦልናል።

*ሀ. ኃጢአት በኢየሱስ ላይ ያመጣውን ነገር አስቡ (4፡1)።* ኢየሱስ በኃጢአት ምክንያት መከራን ተቀበለ (2፡21፤ 3፡18)። ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ ተቀብሎ እንዲሞት ምክንያት በሆነው ኃጢአት እንዴት እንደሰታለን? ልጅህ በጩካኝ ተወግቶ የተገደለበትን ጩቤ በመስተዋት ውስጥ ፊት ለፊትህ ታስቀምጠዋለህን? አይመስለኝም። እንዲያውም ያንን ጩቤ ደግመህ ማየት አትፈልግም።

ጌታችን ኃጢአትን ለመዋጋትና ለዘለዓለም ድል ለመንሣት ወደ ምድር መጣ። የአለማወቅን ኃጢአት እውነትን በማስተማርና በሰዎች ፊት ያንኑ እውነት በመኖር፥ ኃጢአት ያስከተለውን እርግማን በፍቅሩና በምሕረቱ፥ የሞትን መውጊያ ኃጢአትን ደግሞ በመስቀል ላይ በመሞቱ ሽሯቸዋል። ለኃጢአተኞች የሚራራ ልብ ያለው ቢሆንም፥ ኃጢአትን ለመቃወም ግን የታጠቀ ቆራጥ ነበር።

የሕይወታችን ግብ «ከኃጢአት መታቀብ» ነው። በእርግጥ ጌታ እስኪመለስ ወይም እኛ ወደ እርሱ እስከምንሄድ ድረስ ወደዚህ ግብ አንደርስም፤ ይሁን እንጂ ለመድረስ መጋደል አይገባንም ማለት ግን አይደለም (1ኛ ዮሐ. 2፡28–3፡9)። ጴጥሮስ መከራ በራሱ አንድን ሰው ኃጢአት እንዳይሠራ ያደርገዋል አላለም። የግብፁ ፈርዖን በታላላቅ መቅሰፍቶች መካከል ቢያልፍም በእልከኝነት ኃጢአት መሥራቱን አላቆመም። እግዚአብሔርን የሚራገሙና በሥቃያቸው ምክንያት ከመጠን በላይ መከራ የሚቀበሉ ሰዎች አጋጥመውናል።

መከራና *የክርስቶስ በሕይወታችን* መኖር ተዳምረው በኃጢአት ላይ ድልን ይሰጡናል። በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ጭብጥ በሮሜ 6 ላይ ካለው በመከራውና በሞቱ ክርስቶስን ከመሰልን በኃጢአት ላይ የተገኘውን ድልም ተካፋዮች ነን ከሚለው አሳብ ጋር ይስማማል። ለእግዚአብሔር ስንገዛ፥ ክርስቶስ ኃጢአትን ለመቃወም የነበረውን

ዓይነት ቆራጥ ባሕርይ ቢኖረን፥ አሮጌውን ሕይወት ድል ነሥተን አዲሱን ሕይወት እንገልጣለን።

*ለ. በእግዚአብሔር ፈቃድ ደስ ይበላችሁ (4፥2)።* እዚህ ቦታ ላይ ያለው ንጽጽር በሰውና በእግዚአብሔር ፈቃድ መካከል ነው። ከድሮ ጀምሮ ጓደኞቻችን የነበሩ ሰዎች በሕይወታችን ያለውን ለውጥ ስለማይረዱት ቀድሞ ያስደስተን ወደነበረው «የዓመፅ አረንቋ» እንድንመለስ ይፈልጋሉ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናደርግ ከሆነ፥ «ቀሪውን ጊዜያችንን» የሚጠቅምና ዘለቄታ ያለውን ነገር ለመሥራት እንጠቀምበታለን። ነገር ግን በዙሪያችን ላለው ዓለም ፈቃድ ብንገዛ «ቀሪው ዘመናችን» ከንቱ ሆኖ በጌታችን ፊት ስንቆምም እናፍራለን።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሻለናል! የእግዚአብሔር ፈቃድ አብ በእኛ ላይ የሚጫነብን ሸክም ሳይሆን ሁሉን ሸክም ቀላል የሚያደርግ መለኮታዊ ደስታና ችሎታ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ከልቡ ስለሚወጣ የፍቅሩ መግለጫ ነው [መዝ. (33)፥11]። ምን እንደሚያደርግ ባይገባንም በጎውን ነገር እንደሚያደርግልን ግን እናውቃለን። በእያንዳንዱ ነገር ላይ በሚሰጥ ማብራሪያ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በሰጠን የተስፋ ቃል ኪዳን እንኖራለን።

*ሐ. ክርስቶስን የግል አዳኛችሁ አድርጋችሁ ከመቀበላችሁ በፊት የነበራችሁን ሕይወት አስቡ (4፥3)።* ያለፈ ሕይወትን መለስ ብሎ ማየት ስሕተት የሚሆንበት ጊዜ አለ። ምክንያቱም ሰይጣን እነዚያን ትዝታዎች ተጠቅሞ ተስፋ ሊያስቆርጣችሁ ስለሚችል ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በግብፅ ባርያ እንደነበሩ እንዲያስተውሉ ግድ ይላቸዋል (ዘዳ. 5፥15)። ጳውሎስ አማኞችን ያሳድድ እንደነበር ሲያስታውስ (1ኛ ጢሞ. 1፥12)፥ ለክርስቶስ የበለጠ እንዲሠራ ያበረታታው ነበር። አንዳንድ ጊዜ ተጭኖን የነበረውን የኃጢአት ቀንበር ዘንግተን በኃጢአት ያገኘነውን አላፊ ደስታ እናስታውሳለን።

«የአሕዛብ ፈቃድ» ማለት «ያልዳነው ዓለም ፈቃድ» ማለት ነው (1ኛ ጴጥ. 2፥12)። ኃጢአተኞች ይህንን ዓለም ይመስላሉ (ሮሜ 12፥2፤ ኤፌ. 3፥1–3)። «መዳራትና የሥጋ ምኞት» ወሲብን ብቻ ሳይሆን፥ ማንኛውንም ዓይነት ክፉ ምኞት ያመለክታል። «በስካር፥ በዘፈንና ያለ ልክ በመጠጣት» የሚለው፥ አሕዛብ ጣዖት ሲያመልኩ እየጨፈሩና በወይን እየሰከሩ ነውረኛ ነገርን በማድረግ የሚያሳልፉትን ሕይወት ለማመልከት ነው። ይህ ግን በሙሴ ሕግ የተከለከለ ቢሆንም በድብቅ አብዛኛውን ጊዜ ይፈጽሙ ነበር።

ከመለወጣችን በፊት እንደዚህ ዓይነት ኃጢአቶችን አላደረግንም ይሆናል። ነገር ግን እኛ የፈጸምነው ኃጢአትም ክርስቶስን ወደ

መስቀል ለማምጣት አስተዋጽኦ አለው። ወደዚህ የኃጢአት ኑሮ መመለስ ምንኛ ሞኝነት ነው!

## 2. ለሚጠፉት የሚኖረን ትዕግሥት የተሞላ አስተሳሰብ (4፡4–6)

ያልዳኑ ሰዎች ጓደኞቻቸው የእግዚአብሔር ልጆች ሲሆኑ በሕይወታቸው የሚታየውን ድንገተኛ ለውጥ አይገነዘቡትም። ሰዎች አካላቸውን፥ ቤተሰቦቻቸውንና ሕይወታቸውን ከአንዱ ኃጢአት ወደ ሌላው በመፉነን ሲያጠፉትና ሲያበላሹት እንግዳ ነገር አይሆንባቸውም። ነገር ግን ሰካራሙ ጭምት ሲሆን፥ ኃጢአተኛው በቅድስና ሲመላለስ፥ ቤተሰቦቹ አበደ ይሉታል። ፊስጦስም ጳውሎስን «አብደሃል እኮ!» ብሎታል (የሐዋ. ሥራ 26፡24)። ሰዎች ስለ ጌታችንም እንደዚሁ አስበው ነበር (ማር. 3፡21)።

ባላመኑ ሰዎች አኗኗር ባንስማማም፥ በኃጢአታቸውም ባንተባበርም፥ ለጠፉት ሰዎች ትዕግሥትን ማሳየት ግን ይገባናል። ምክንያቱም ያልዳኑ ሰዎች ለመንፈሳዊ እውነታ የታወሩ (2ኛ ቆሮ. 4፡3–4) እና ለመንፈሳዊ ደስታም የሞቱ (ኤፌ. 2፡1) ስለሆኑ ነው። በእርግጥ ለእነርሱ የሚያስፈልገው እውነት በእኛ ዘንድ ስላለ ከእኛ ጋር ያላቸው ግንኙነት ይጠቅማቸዋል። ጓደኞቻችን በሚቃወሙን ጊዜ ለምስክርነት በር ይከፍቱልናል (1ኛ ጴጥ. 3፡15)።

ያልዳኑት ሰዎች በእኛ ላይ ሊፈርዱ ይችላሉ። እግዚአብሔር ደግሞ አንድ ቀን በእነርሱ ላይ ይፈርዳል። ከምንከራከራቸው ይልቅ፥ ልንጸልይላቸው ይገባል፤ ምክንያቱም የመጨረሻው ፍርድ በእግዚአብሔር እጅ መሆኑን ስለምናውቅ ነው። እንደዚህ ዓይነቱ አሳብ ደግሞ በኢየሱስም ሆነ በጳውሎስ ዘንድ የነበረ ነው (1ኛ ጴጥ. 2፡23፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡6–8)።

ቁጥር 6ን መከራን መቀበል ከሚለው ጭብጥ ለይተን መተርጎም የለብንም። ያለበለዚያ ከሞት በኋላ ሌላ የመዳን ዕድል አለ ወደሚል አስተሳሰብ ይመራናል። ጴጥሮስ በእምነታቸው ምክንያት መሥዋዕት የሆኑትን ክርስቲያኖች ለአንባቢዎቹ ያስታውሳቸዋል። እነዚህ ሰዎች በሐሰት ቢፈረድባቸውም አሁን ግን ትክክለኛ ፍርዳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ተቀብለዋል። «ለሙታን ደግሞ ተሰብኮላቸው ነበር» የሚለው ጴጥሮስ በሚጽፍበት ወቅት ስለሞቱት ለማመልከት ነው። ወንጌል የሚሰበከው ለሕያዋን ብቻ ነው። ምክንያቱም ከሞት በኋላ የደኅንነት ዕድል የለም (ዕብ. 9፡27)።

ያላመኑ ጓደኞቻችን በእኛ ላይ ክፉ ሊናገሩብን እና ሊቃወሙን ይችላሉ፤ የመጨረሻው ፈራጅ ግን እግዚአብሔር ነው። በስደት ውስጥ ሕይወታችን ልትሠዋ ብትችልም፥ እግዚአብሔር ግን ያከብረናል፤ ይሸልመናልም። ስለዚህ መፍራት የሚገባን እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም (1ኛ ጴጥ. 3፥13-17፤ ማቴ. 10፥24-33)። ዛሬ በሥጋ ሳለን በሰዎች መለኪያ ይፈረድብናል። አንድ ቀን ከጌታ ጋር በምንሆንበት ጊዜ ግን፥ እውነተኛውን እና የመጨረሻውን ፍርድ እንቀበላለን።

## 3. ክርስቶስን የመጠበቅ ሕይወት (4፥7)

የጥንት ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ዘመን ይመጣል ብለው ይጠባበቁ ነበር (ሮሜ 13፥12፤ 1ኛ ዮሐ. 2፥18)። እነርሱ በጠበቁበት ጊዜ ባይመለስም የመምጣቱ ተስፋ ግን አልተሻረም (2ኛ ጴጥ. 3፤ ራእ. 22፥20)። ስለ ጌታ መመለስ የሚናገሩት ትንቢታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተለያዩ ትርጉሞችን ቢሰጡንም ሁላችንም ጌታን በመጠባበቅ ልንኖር ይገባል። አንድ ቀን ጌታችንን ፊት ለፊት እናየዋለን፤ በፊቱም እንቆማለን። ዛሬ የምንኖረው ኑሮና የምናገለግለው አገልግሎት ሽልማታችንን ይወስነዋል።

ጌታን መጠባበቃችን ግን ሰነፍ አላሚዎች ወይም ወግ አጥባቂዎች ሊያደርገን አይገባም (2ኛ ተሰ. 3፥6)። ጴጥሮስ የጌታን መመለስ በሚመለከት ሚዛናዊ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለአንባቢዎቹ አሥር ትእዛዛት ሰጥቷቸዋል።

1. እንደ ባለ አእምሮ አስቡ- ቁ. 7
2. ትጸልዩ ዘንድ በመጠን ኑሩ- ቁ. 7
3. አጥብቃችሁ ተዋደዱ- ቁ. 8
4. እንግዳ ተቀበሉ- ቁ. 9
5. በጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ- ቁ. 10-11
6. ድንቅ ነገር እንደመጣባችሁ አትደነቁ- ቁ. 12
7. ደስ ይበላችሁ- ቁ. 13
8. አትፍሩ- ቁ. 15-16
9. እግዚአብሔርን አክብሩ- ቁ. 16-18
10. ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አደራ ስጡ- ቁ. 19

«እንደ ባለ አእምሮ አስቡ» የሚለው ቃል «የተረጋጋና ግልጽ አእምሮ» ይኑራችሁ ማለቱ ነው። ሚዛናዊ ወዳልሆነ ሕይወትና አገልግሎት ስለሚመራ ስለ ትንቢት የተሳሳተ አስተሳሰብ እንዳይኖራቸው ያስጠነቅቃል። አልፎ አልፎ እንደምንሰማው አንዳንድ ቅን ሰዎች ሚዛናቸውን የሚስቱት በትንቢት ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አትኩሮት በመስጠታቸውና በተሳሳተ መንገድ በመተርጎማቸው ነው። የክርስቶስን የመመለሻ ቀን የሚወስኑ፥ በራዕይ 13 ያለውን የአውሬ ስም እንደሚያውቁ የሚናገሩ አሉ። ምንም እንኳን ጌታ በዚህ ጉዳይ ላይ ማስጠንቀቂያ ቢሰጥም (ማቴ. 25፡13፤ የሐዋ. ሥራ 1፡6–8)፥ በቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ በእግዚአብሔር ሰዎች የተጻፉ፥ ስለ ጌታ መመለስ ብዙ ነገርን ያካተቱ ግን ተፈጻሚነትን ባለማግኘታቸው ጸሐፊዎቻቸውን ያሳፈሩ መጻሕፍት አሉኝ።

«እንደ ባለ አእምሮ» የማሰብ ተቃራኒው «ልቅነትና እብደት» ነው። ጭምት አእምሮ ያለው ሰው በትምህርት ነፋስ አይገፋም፤ ሕይወቱን በዕቅድ ይመራል። ራሱን ይገዛል፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትምህርትና የሕይወትን እውነታ መመዘን ይችላል።

ራስን መግዛት የሚለው ቃል በመልእክቶች ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል። ራስን መግዛት የመጋቢም ሆነ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሕይወት መመዘኛ ነው (1ኛ ጢሞ. 3፡2፤ ቲቶ 2፡1–6)። ራስን መግዛት በሌለበት ዓለም ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በጭምትነት ልትኖር ይገባል።

አገልግሎት በጀመርኩበት አካባቢ ስለ ጌታ መመለስ በሚተነብየው ክፍል ላይ ሰበኩኝ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ያ ስብከት በፋይል ውስጥ ተቀምጦ ይኖራል (አንዳንድ ጊዜ ራሴን ለማዋረድና ትሑት ለማድረግ ስል ብቻ ገልጬ አየዋለሁ)። ያኔ ይህንን መልእክት ስሰብክ አንድ መጋቢ ጓደኛዬ ከፕሮግራም በኋላ ወደ እኔ መጣና «ወንድሜ፥ የጌታ ኢየሱስን መመለስ የሚያቅደው ኮሚቴ አባል መሆን አለብህ!» አለኝ። እርሱ ሊል የፈለገው ነገር ገብቶኛል። ቀጥሎም ረጋ ብሎ ነገሩን ጠበቅ በማድረግ «እኔ ግን ከዚህ ኮሚቴ ወጥቼ አቀባበል በሚያደርግ ኮሚቴ ውስጥ ገብቻለሁ» አለኝ።

ይህንን ስል ትንቢቶችን ማጥናት የለብንም፤ ከዚያም የተረጎምነውን ለሌሎች ለማካፈል መፍራት አለብን ማለቴ ሳይሆን፥ ትንቢትን በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ሚዛን በሚያሳጣ ትምህርት ሕይወታችን እንዳይጎዳ ማለቴ ነው። የትንቢት መጻሕፍትን በሕይወታችን ገቢራዊ የምናደርግባቸው መንገዶች አሉ። ጴጥሮስ በተስፋ ስለመቆየት እና ለእግዚአብሔር ክብር ስለ መኖር አጽንዖት መስጠቱ፥ እኛም

በታማኝነት ጌታ እንድንሠራው የሰጠንን ሥራ እየሠራን እንድንጠብቀው ያበረታታናል (ሉቃስ 12፡31–48)።

«ቀሪውን ዘመናችሁን» በሚገባ መጠቀም ከፈለጋችሁ፥ የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ በሚያሳስብ ብርሃን ውስጥ ሁሉም ክርስቲያን ጌታ በምን ዓይነት ሁኔታ ይመለሳል በሚለው ጉዳይ ላይ ላይስማማ ይችላል። ጌታን እንዴት እንጠባበቅ በሚለው ግን እንስማማለን። በእነዚህ ጥቅሶች ስላሉት ገቢራዊ ትርጉሞች ሁላችንም በጌታ ፊት እንቆማለን! (ሮሜ 14፡10–23፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡1–21)።

ጭምቶች ከሆንን ለመጸለይ እንነቃለን። ግራ የተጋባ የጸሎት ሕይወት ያለው ሰው አእምሮውም ግራ የተጋባ ነው። ዶክተር ኬኔት ውስት ለትርጉማቸው የሁለቱን ግንኙነት «ራሳችሁን በጸሎት ለመስጠት አእምሮአችሁን ሰብስባችሁ በጸጥታ ቅረቡ» በማለት ገልጸውታል። «መንቃት» የማንቀላፋትና የመስከር ተቃራኒ ነው (1ኛ ተሰ. 5፡6–8)። ይህ ማስጠንቀቂያ ለጴጥሮስ የተለየ ትርጉም ይሰጠዋል፤ ምክንያቱም «በጸሎት መትጋት» በነበረበት ወቅት አንቀላፍቶ ነበርና (ማር. 14፡37–40)።

በአዲስ ኪዳን «ትጉና ጸልዩ» የሚለውን ሐረግ ደጋግመን እናገኘዋለን (ማር. 13፡33፤ 14፡38፤ ኤፌ. 6፡18፤ ቆላ. 4፡2)። ትርጉሙም በጸሎት የነቃን፥ እንዲሁም በጸሎት የተገዛን እንሁን ማለት ነው። በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በስንፍናና በዘፈቀደ የሚደረግ የድግምት ጸሎት ቦታ የለውም። በነህምያ ጊዜ እንደነበሩት ሠራተኞች የነቃንና የተጋን ልንሆን ይገባል (ነህምያ 4፡9)።

የክርስቶስን መመለስ ስንጠባበቅ፥ ሚዛናዊና የነቃ አእምሮ እንዲሁም ትጉ የጸሎት ሕይወት ይኑረን። ለክርስቶስ መመለስ አስተምህሮ ያለን መስጠት የሚመዘነው፥ ምልክቶችን በመለየትና በዚህ ቀን ወይም በዚያ ቀን ይመጣል እያልን የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ሳይሆን በተስተካከለ አስተሳሰባችንና የጸሎት ሕይወታችን ነው። አስተሳሰባችንና ጸሎታችን ትክክል ከሆነ ኑሮአችንም ትክክል ይሆናል።

## 4. ስለ ቅዱሳን በትጋት ማሰብ (4፡8–11)

የክርስቶስን ዳግም መመለስ ስንጠባበቅ፥ ስለ ሌሎች በማሰብ ከቅዱሳን ጋር እንደሚገባ ልንኖር ያስፈልጋል። ፍቅር ለክርስቲያኖች እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። «ከሁሉም ነገር በላይ» ፍቅር የክርስቲያን መለያ ዓርማው ነው (ዮሐ. 13፡34–35)። በተለይ በመከራና በስደት ጊዜ ክርስቲያኖች በፍቅር የልብ አንድነት ሊኖራቸው ይገባል።

ይህ ፍቅር በትጋት ሊገለጥ ይገባል። የክርስቶስ ፍቅር አንድ ሾጭ ለማሸነፍ በጉጉት ችሎታውን ለማሻሻል እንደሚጥር ሁሉ እኛም በጥረታችን የምናሳድገው ነገር ነው። በትጋት ሊሆን ይገባል። ክርስቲያናዊ ፍቅር ማለት ስሜት ብቻ ሳይሆን፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድን የማስገዛት ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር ለእኛ እንደሚያደርግልን ሁሉ፥ ለሌሎች ማድረግና ለቃሉ መታዘዝ ማለት ነው። በዚህም የምንጠላቸውን ሰዎች እንኳን ማፍቀር እንችላለን።

ክርስቲያናዊ ፍቅር ይቅር ባይ ነው። ጴጥሮስ «ጥል ክርክርን ታስነሣለች፤ ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለች» የሚለውን ከምሳሌ 10፡12 ጠቅሶታል። ይህ ጥቅስ በቀጥታም ባይሆን በያዕ. 5፡20 ና በ1ኛ ቆሮ. 13፡4፥7 ተመልክቷል። ክርስቲያን ኃጢአትን ምንም ጉዳት እንደማያመጣ አይቆጥረውም። አንድን ሰው ከወደድነው ኃጢአት እያደረገ እርሱንና ሌሎችን ሲጎዳ ማየት ያሳዝነናል። ፍቅር የኃጢአትን ብዛት የሚሸፍነው የዚያን ሰው በደል ለሌሎች ባለማዳረስ ነው። ጥል ባለበት በዚያ ግን ሐሜት አለ፤ ሐሜት ደግሞ የጠላቱን ክብር የሚያዋርድ ነገር ነው (ምሳሌ 11፡13፤ 17፡9፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡1)። አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ስናማ «አውቀኸው በደንብ እንድትጸልይለት ብዬ ነው» በማለት መንፈሳዊ ለማድረግ እንሞክራለን።

ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ፊት ኃጢአቱን መሰወር አይችልም። ሆኖም አማኞች የወንድሞቻቸውን ኃጢአት ቢያንስ በማያምኑት ፊት መሸፈን ይገባቸዋል። የማያምኑት መልካም ሥርተን የሚያሳድዱን ከሆነ፥ ክርስቲያኖች መጥፎ እንደሚሠሩና እንደሚናገሩ ካወቁማ (1ኛ ጴጥ. 2፡19–20፤3፡14)እንዴት ያደርጉን ይሆን!

ዘፍጥረት 9፡18–27 ስለዚህ ጉዳይ ግሩም የሆነ ሥዕላዊ መግለጫ ያለው መመሪያ ይሰጠናል። ኖኅ ሰክሮ ራሱን በገለጠ ጊዜ፥ አንደኛው ልጅ የአባቱን ኃፍረት አይቶ ለወንድሞቹ ነገረ። ሁለቱ የካም ወንድሞች ግን በፍቅር ተጠንቅቀው የአባታቸውን ኃፍረት ሸፈኑ። የወንድሞቻችንን ኃፍረት መሸፈን ከባድ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ከኃጢአታችን ሊያጠራን አይደለም እንዴ!

ክርስቲያናዊ ፍቅር የሚተጋና ይቅር የሚል ብቻ ሳይሆን፥ በተግባርም የሚገለጽ ሊሆን ይገባል። ያለንን በደግነት በማካፈል ያለማጉረምረም እንግዶችን በመቀበል፥ በጸጋችን አንዳችን ሌሎችን በማገልገል ልንገልጸው ይገባል። በጥንት ዘመን የእንግዶች ማረፊያ (ሆቴሎች) ቁጥር አነስተኛ ስለነበረና ከፍያውም ከድሃ ክርስቲያኖች አቅም በላይ ስለነበር፥ በተለይም በስደት ምክንያት መጠጊያ

ያሚያጡትን ክርስቲያኖች መርዳትና ማበረታታት በጣም አስፈላጊ ነበር።

እንግዳን መቀበል በቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጠ ትእዛዝ ሲሆን፥ ሰዎችም በተግባር ላይ ሲያውሉት ኖረዋል (ዘጸ. 22:21፤ ዘዳ. 14:28–29)። ሰዎች ኢየሱስንና ሐዋርያትንም በእንግድነት ተቀብለዋቸዋል (የሐዋ. ሥራ 28:7፤ ፊልሞ. 22)። እንግዳ ተቀባይነት እግዚአብሔር እኛን የመቀበሉ ነጸብራቅ ነው (ሉቃስ 14:16)። በተለይ ክርስቲያን መሪዎች «እንግዳ ተቀባይ» ሊሆኑ ይገባል (1ኛ ጢሞ. 3:2፤ ቲቶ 1:8)።

አብርሃም ሦስት እንግዶችን ሲቀበል ጌታንና ሁለት መላእክትን ተቀብሏል (ዘፍ. 18፤ ዕብ. 13:2)። ቤታችንን ለእግዚአብሔር ሰዎች ስንከፍትላቸው እውነትን አከበርን ማለት ነው (3ኛ ዮሐ. 5–8)። ለሌሎች በራችንን የምንከፍተው መልሰው በእንግድነት እንዲቀበሉን በማሰብ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርን ለማክበር ስንል መሆን አለበት (ሉቃስ 14:12–14)።

እየተዘዋወርኩ ሳገለግል አብዛኛውን ጊዜ በክርስቲያኖች ቤት በማረፍ እጽናናለሁ። የቅዱሳንን በጎነት አንዳንድ ጊዜም በመሥዋዕትነት ያላቸውን በማካፈላቸው እደነቃለሁ። እኔና ባለቤቴ በተለያዩ አገሮች ብዙ ወዳጆች አሉን። እኛና ልጆቻችንም ደግሞ እንግዳ በመቀበላችን ተባርከናል።

በመጨረሻም፥ የክርስቲያን ፍቅር በአገልግሎት መገለጥ እንዳለበት እናያለን። እያንዳንዱ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ክብርና ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ሊያውለው የሚገባ ቢያንስ አንድ የጸጋ ስጦታ ይኖረዋል (ሮሜ 12:1–13፤ ኤፌ. 4:1–16፤ 1ኛ ቆሮ. 12)። እኛ ባለ አደራዎች ነን። እግዚአብሔር ደግሞ ይህንን የባለአደራነት ጸጋ በውስጣችን ያስቀመጠው ቤተ ክርስቲያንን እንድንጠቅም ነው። ሌላው ቀርቶ ጸጋችንን የምናሳድግበትን እና ቤተ ክርስቲያንን በታማኝነት የምናገለግልበትን መንፈሳዊ ችሎታ ይሰጠናል።

የንግግርም ሆነ የአገልግሎት ስጦታዎች ለቤተ ክርስቲያን ይጠቅሟታል። ሁሉም ሰው የክርስቶስ ምስክር ቢሆንም፥ ሁሉም ሰው ግን አስተማሪ ወይም ሰባኪ አይደለም። ሌሎች ደግሞ «ከመጋረጃ ጀርባ» ሆነው በአደባባይ የሚካሄደውን አገልግሎት የሚደግፉ አሉ። መንፈሳዊ ስጦታዎችን፥ የምናገለግልበትን ስጦታ፥ ችሎታ፥ ስጦታችንን የምንገልጥበትን ሁኔታ የሚሰጠው እግዚአብሔር ስለሆነ፥ ክብሩን ሁሉ ሊወስድ ይገባል።

በ1ኛ ጴጥ. 4፡11 ላይ «የእግዚአብሔር ቃል» የሚለው፥ ሰባኪ ወይም አስተማሪ የሚናገረው ሁሉ የእግዚአብሔር እውነት ነው ማለት አይደለም። ምክንያቱም በሰው ንግግር መሐል ስሕተት ሊኖር ስለሚችል ነው። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል የመናገር ስጦታ ያላቸው ነቢያት ነበሩ። ዛሬ ግን የእግዚአብሔር ቃል ተሟልቶ ቀርቦልናል። ስለዚህ የዚህ ዓይነቱ ስጦታ የለም። የእግዚአብሔርን ቃል የሚያካፍል ማንም ቢሆን ምን እና እንዴት እንደሚናገር መጠንቀቅ አለበት። ትምህርት ሁሉ ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር መስማማት አለበት።

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ እንደገለጽኩት ከአፍሪካ ወደ አገራችን ስንመለስ እንግሊዝ አገር ባጋጠመን ጭጋግ ምክንያት በረራውን መቀጠል ስላልቻልን፥ በለንደን ለመዘግየት ተገደድን። ለንደን ከምወዳቸው ቦታዎች አንዷ ናት። ስለዚህ በመዘግየታችን ብዙም ስሜቴ አልተጎዳም። ይልቁንስ በመዘግየታችን ከእኛ ጋር ይጓዙ ለነበሩ ባለትዳሮች የለንደንን ከተማና ብዙ አስደሳች ቦታዎቿን ለማስጎብኘት ዕድል አገኘን። በአንድ ቀን ያችን ውብ ከተማ ለማሳየት መሞከራችን አያስገርምም!

እኛ በተሰጠን ጊዜ በሚገባ መጠቀም ነበረብን፥ እናም ተጠቀምንበት። ባልንጀራዎቻችን በዚያች ከተማ ውስጥ የሚገኙትን ብዙ አስደሳች ቦታዎች ተመለከቱ።

«ቀሪው ዘመናችሁ» ምን ያህል ነው? ይህንን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

አታባክኑት! ቀሪ ዘመናችሁን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም አውሉት።

## 10

# የማንጠሪያው እቶን እውነታዎች

1ኛ ጴጥሮስ 4፡12–19

እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚኖር ክርስቲያን ሁሉ በሥራ ቦታው፥ በትምህርት ቤቱ፥ በጎረቤቶቹ፥ በቤተሰቡም ሳይቀር የክርስቶስን ወንጌልና እውነትን በሚቃወሙ ሰዎች ይሰደዳል። ምንም ይናገር ወይም ያድርግ እነዚህ ሰዎች ግን አቃቂር ማውጣታቸውና መንቀፋቸው የማይቀር ነው። ጴጥሮስ ስለ እንደዚህ ዓይነቱ ስደት በቀደሙት የመልእክቱ ክፍሎች ላይ አንሥቶ ነበር።

በዚህ ክፍል ግን ጴጥሮስ ለየት ስላለ የስደት ዓይነት ያነሣል። «እንደ እሳት የሚፈትን» ፈተና በቤተ ክርስቲያን ሁሉ ላይ ሊመጣ መሆኑን ይነግራቸዋል። የአሁኑ ፈተና በዙሪያቸው ካሉ ሰዎች የሚነሣ የግል ስደት ሳይሆን፥ ከበላይ ባለሥልጣኖች የሚነሣ ነው። በሮም ነገሥታት ዘንድ ክርስትና የአይሁድ እምነት አንድ ክፍል ተደርጎ ይወሰድ ስለነበር ይታገሏቸው ነበር። በኋላ ግን ይህ አመለካከት በመለወጡ፥ እንደ እሳት የሚፈትነው መከራ መጀመሪያ በኔሮ ከዚያ በኋላም በሮም ነገሥታት ተቀጣጠለ። ጴጥሮስ እንደ እሳት የሚፈትነውን መከራ አስመልክቶ አራት መመሪያዎችን ለአማኞች ሰጥቷቸዋል።

### 1. መከራ እንደሚመጣ ማወቅ (4፡12)

ስደት ለክርስቲያኖች እንግዳ ነገር አይደለም። ምክንያቱም በታሪክ ውስጥ ክርስቲያኖች ከማያምነው ዓለም መከራን ተቀብለዋል። ክርስቲያኖች በሕይወታቸውና በአኗኗራቸው ከዓለም የተለዩ ናቸው (2ኛ ቆሮ. 6፡14–18)። በዓለም ያለው አብዛኛው ነገር በውሸት፥ በትዕቢት፥ በሚያልፍ ደስታ ፍለጋ፥ በስግብግብነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ ጌታን የሚወድ ክርስቲያን ደግሞ ሕይወቱ በእውነት፥ በትሕትና፥ በቅድስናና፥ እግዚአብሔርን በማክበር ጥማት ላይ የተመሠረተ ነው።

ይህ ቅራኔ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቀርቧል። ቃየን ሃይማኖተኛ ሰው ነበር፥ ግን ወንድሙን ጠላው፥ ገደለውም (ዘፍ. 4፡1–8)። ዓለም የምታሳድደው ሃይማኖተኞችን ሳይሆን፥ የጽድቅን ኑሮ የሚኖሩትን ነው። ቃየን ወንድሙን አቤልን የገደለው የእርሱ ሥራ ክፉ የወንድሙ ግን መልካም ስለነበር ነው (1ኛ ዮሐ. 3፡12)። ጻፎችና የአይሁድ መሪዎች ሃይማኖተኞች ነበሩ፤ ነገር ግን ክርስቶስን ሰቀሉት፤ ቤተ ክርስቲያንንም አሳደዱ። ኢየሱስ በማቴዎስ 10፡17 ላይ «ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጧችኋል፥ በምኵራቦቻቸውም ይገርፉአችኋልና

ከሰዎች ተጠበቁ» ብሏል። የእግዚአብሔርን ባርያዎች በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሲገርፉአቸው ምን እንደሚመስል አስቡት!

ከሰው ልጅ ውድቀት በኋላ እግዚአብሔር በሰይጣን ላይ ጦርነት አውጇል (ዘፍ. 3፡15)። ሰይጣን ደግሞ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔርን በራሱ ሕዝብ በኩል ይቃወመዋል። ክርስቲያኖች፥ ሰይጣን አምላክና ገዢ በሆነበት ዓለም ውስጥ እንግዶችና መጻተኞች ናቸው (ዮሐ. 14፡30፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡3–4)። እግዚአብሔርን የሚያከብር ማንኛውም ነገር ሰይጣንን ያስቆጣዋል፤ ለበቀልም ያነሣሣዋል። ስለዚህ ለአማኞች ስደት ድንቅ ነገር አይደለም። የሚያስደንቀው የሰይጣን ተቃውሞ *ባይኖር* ነበር!

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ተቃውሞና ስደት ከዓለም የማይቀር መሆኑን እንዲያስቡ ነግሯቸዋል (ዮሐ. 15፡17–16፡4)። ነገር ግን የሚያበረታታቸውን ተስፋ ቃልም ሰጥቷቸዋል፦ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፥ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ» (ዮሐ. 16፡33)። በቀራኒዮ መስቀል ላይ በመሞቱና በትንሣኤው ኃጢአትንና ዓለምን ድል ነሥቷል (ዮሐ. 12፡23–33፤ ገላ. 6፡14)።

«እሳት» በዘመናዊው ንግግር ውስጥ ሳይቀር መከራን ወይም ስደትን የሚገልጽ ቃል ነው። «ይህ ሰው በእውነት በእሳት ውስጥ እያለፈ ነው» የሚለው ዓረፍተ ነገር ያ ሰው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ማለፉን ለመግለጽ ነው። በብሉይ ኪዳን እሳት፥ የቅድስናና የእግዚአብሔር ህልዎት ምልክት ነው። በመሠዊያው ላይ ያለው እሳት መሥዋዕቱን ይበላዋል (ዕብ. 12፡28–29)። ጴጥሮስ በዚህ ክፍል የእሳትን ተምሳሌት *የማጥራትን ተግባር* እንደሚፈጽም እንጂ እንደ እግዚአብሔር ፍርድ መግለጫ አልተጠቀመበትም (1ኛ ጴጥ. 1፡7፤ ኢዮብ 23፡10)።

በሕይወታችን የሚገጥመን ችግር ሁሉ እንደ እሳት ሊያጠራ የመጣ መከራ ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም ሁሉም ሰው የሚያልፍባቸው የሕይወት ክፍል የሆኑ አንዳንድ ችግሮች አሉ። የሚያሳዝነው ግን ጴጥሮስ እንደጠቀሰው ባለመታዘዝና በኃጢአት ምክንያት ወደ ሕይወታችን የምናመጣቸው ችግሮች መኖራቸው ነው (2፡18–20፥ 3፡13–17)። በ4፡12 ላይ የተጠቀሰውና እንደ እሳት የሚፈትነው መከራ የሚመጣብን ግን ለጌታ ታማኝ በመሆናችን እና በእውነት ላይ በመቆማችን ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በመሸከማችን ዓለም ይቃወመናል። ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ሰዎች እግዚአብሔርን ባለማወቃቸው እርሱን እንዳሳደዱት ሁሉ እነርሱንም እንደሚያሳድዷቸው ነግሮአቸዋል (ዮሐ. 15፡20–21)።

«ስለሚሆነው» የሚለው ቃል አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ስደትና መከራ በድንገት «የሚሆን» ሳይሆን ሁሉ ነገር በቁጥጥሩ ሥር በሆነው በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ነው። መከራው በሮሜ 8፡28 ላይ እንደተጻፈው እግዚአብሔር የወደደውን እንዲሠራ መንገድ ከለቀቅንለት ለበጎ ያደርገዋል።

## 2. በመከራ ደስ ይበላችሁ (4፡13-14)

ጴጥሮስ በቀጥታ ዘወትር ደስ ይበላችሁ ብሎ ነው የጻፈው። **ደስታ** የሚለውን ቃል በአንድ ወይም በሌላ መልኩ አራት ጊዜ ጠቅሶታል። በዓለም ያሉት ሰዎች አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንዴት አድርገው ታላቅ ደስታን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ሊገባቸው አይችልም፥ ምክንያቱም ዓለም የእግዚአብሔርን ጸጋ አልተለማመደም (2ኛ ቆሮ. 8፡1-5)። ጴጥሮስ እንደ እሳት በሚፈትን መከራ ውስጥ ለመደሰት የሚያስችሉንን ጠቃሚ ነጥቦች ጠቅሷል።

*ሀ. መከራ ስንቀበል ከክርስቶስ ጋር እንተባበራለን (4፡13)።* ከክርስቶስ ጋር መከራን መቀበልና ዓለም በእርሱ ላይ ያደረሰችውን በእኛም ላይ ስታደርስብን ታላቅ መታደልና ክብራችን ነው። የመከራው ተካፋይ መሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ፊልጵ. 1፡29፤ 3፡10)። ሁሉም ክርስቲያን እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ ያልፋል ብሎ እስከታመንበት ድረስ በሕይወቱ ሊያድግ ይችላል። ስለዚህ ይህ ዕድል ወደ እኛ ሲመጣ ልንደሰት ይገባል። «ሐዋርያትም ስለ ስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ከወጡ በኋላ ደስ አላቸው።» (የሐዋ. ሥራ 5፡41)።

በስደት እሳት ውስጥ ስናልፍ ክርስቶስ ከእኛ ጋር ነው (ኢሳ. 41፡10፤ 43፡2)። በእቶን እሳት ውስጥ ተጥለው የነበሩት ሦስቱ ዕብራውያን ልጆች ብቻቸውን እንዳልነበሩ አወቁ (ዳን. 3፡23-25)። በጳውሎስ መከራ ሁሉ፥ ጌታ ከእርሱ ጋር ነበር (የሐዋ. ሥራ 23፡11፤ 27፡21-25፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡9-18)። እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእኛ ጋር እንደሚሆንም ቃል ገብቶልናል (ማቴ. 28፡20)። ኃጢአተኞች እኛን ሲያሳድዱን የሚያሳዱዱት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው (የሐዋ. ሥራ 9፡4)።

*ለ. መከራ መቀበላችን የክብራችን መግቢያ ነው (4፡13)።* «መከራና ክብር» በጴጥሮስ መልእክት ውስጥ እንደ ድርና ማግ የተሳሰሩ መንታ እውነቶች ናቸው። ዓለም ክብር ነው ብሎ የሚያምነው መከራ የሌለበትን ሕይወት ነው። የክርስቲያን አመለካከት ግን ከዚህ የተለየ ነው። ዛሬ የእምነታችን መፈተን ጌታችን ሲመለስ የምንቀበለው

የክብር ማስረጃ ነው (1ኛ ጴጥ. 1:7–8)። ጌታችን ያለፈበትና እኛም ደግሞ የምናልፍበት ይኸው ነው (5:1)።

መገንዘብ ያለብን ነገር እግዚአብሔር መከራን በክብር እንደሚተካ ሳይሆን፥ መከራን በክብር እንደሚለውጥ ነው። ጌታ ኢየሱስ ምጥ የያዛትን ሴት ምሳሌ ተጠቅሞ ያስጨነቃት ሕፃን ደስታንም እንደሚሰጣት አስተምሯል (ዮሐ. 16:20–22)። ጳውሎስን ያስቸገረ የሥጋው መውጊያ ኃይልና ክብር ሰጠው (2ኛ ቆሮ. 12:7–10)። ኢየሱስ ክርስቶስን ያዋረደውና ያሠቃየው መስቀል ኃይልና ክብርን አመጣለት።

በሳል ሰዎች ሕይወት «የምታስተላልፈው ደስታ» እንዳላት ያውቃሉ። ወደ ፊት ለመደሰት ዛሬ ዋጋ ልንከፍል እንችላለን። የፒያኖ ተማሪ ልምምድ በሚያደርግባቸው ጊዜያት ብዙ አይደሰትም። አሰልቺ ሊሆንበት ይችላል። ሆኖም አንድ ቀን ግሩም የሆነ ሙዚቃ በሚጫወትበት ጊዜ ስለሚያገኘው ደስታ ያስባል። አንድ ሯጭ ፍጥነቱን ለማሻሻል የሚያደርገው ልምምድ አያስደስተው ይሆናል፤ ነገር ግን የተሻለውን ሁሉ በማድረግ ውድድሩን ለማሸነፍ ተስፋ ያደርጋል። ክርስቲያኖች ከዚህ የተሻለ ነገር አላቸው። መከራችን ሁሉ አንድ ቀን ወደ ክብር ይለወጣል፥ ደስታችንም ታላቅ ይሆናል (ሮሜ 8:17፤ 2ኛ ጢሞ. 3:11)።

*ሐ. መከራ ስንቀበል መንፈስ ቅዱስ ያገለግለናል (4:14)።* እርሱ የክብር መንፈስ ነው፤ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መከራ የሚቀበሉትን በተለየ መልኩ ያገለግላቸዋል። «የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋል» የሚለው የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያመለክታል (ዘጸ. 40:34፤ 1ኛ ነገ. 8:10–11)። እስጢፋኖስ ሲወገር ሰማያት ተከፍተው የእግዚአብሔርን ክብር አይቷል (የሐዋ. ሥራ 6:15፤ 7:54–60)። ይህ ጴጥሮስ በምዕራፍ 1:7–8 ላይ የጻፈው «ቃላት ሊገልጽ ከሚችለው የሚያልፍ ታላቅ ክብር» ነው።

በሌላ አነጋገር በመከራ ውስጥ የሚያልፉ ክርስቲያኖች ክብሩን የሚያዩት በሰማይ ብቻ አይደለም። አሁን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ክብሩን ያዩታል። ይህም የእምነት አርበኞች በእቶን እሳት ውስጥ በሰንሰለት ታስረው ሳሉ ለምን የምስጋና ዜማ ለእግዚአብሔር እንደ ዘመሩ ይገልጻል። በዘመናችንም ሳይቀር ብዙ ክርስቲያኖች አስጨናቂዎቻቸውን ተቋቁመው፥ ያለማንጎራጎርና ያለተቃውሞ ወደ ሞትና እስራት የሚሄዱትም ለዚህ ነው።

*መ. የምንቀበለው መከራ ስሙን እንድናስከብር ያስችለናል (4:14)።* ስለ ስሙ መከራ እንቀበላለን (ዮሐ. 15:21)። ለማያምኑ ጓደኞችህ አባል የሆንክበትን የቤተ ክርስቲያን ስም ስትነግራቸው

አይቃወሙህም፤ ነገር ግን በንግግራቸው ጣልቃ ክርስቲያን መሆንህን ስትነግራቸውና የክርስቶስን ስም ስታነሣ ተቃውሞ ይጀምራል። ሥልጣናችን በጌታ ኢየሱስ ስም ነው። ሰይጣን ደግሞ ያንን ይፈራል። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ምክንያት ተቃውሞ በደረሰብን ቁጥር፥ ስሙን እናስከብረዋለን። ዓለም በዚህ ስም ላይ በተቃውሞ ሊናገር ይችላል። እኛ ግን ይህንን ስም ለማክበርና እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንናገራለን፤ እንኖርማለን።

«ክርስቲያን» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው (1ኛ ጴጥ. 4፡16፤ የሐዋ. ሥራ 11፡16፤ 26፡28)። ክርስቲያን የሚለውን ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙት ተቃዋሚዎች በክርስቲያኖች ላይ ለመዘበት ሲሉ ነበር። ነገር ግን ዛሬ ይህ ስም የክብር ስም ሆኗል። በእርግጥ ዛሬም ቢሆን «ክርስቲያን» የሚለውን ቃል «የአረማውያን» ተቃራኒ አድርገው የሚረዱ ቢኖሩም፥ ቃሉ «የክርስቶስ የሆኑ፥ የክርስቶስ ወገኖች» የሚለውን አሳብ ይዟል። በእርግጥ ይህንን ታላቅ ስም መሸከምና ስለ እርሱም መከራ መቀበል ታላቅ መታደል ነው (የሐዋ. ሥራ 5፡41)።

በሁለተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ የሰምርኔስ ጳጳስ የነበረው ፖሊካርፕ በእምነቱ ምክንያት ተይዞ እምነቱን ካልተወ በስተቀር እንደሚገድሉት ሲዝቱበት «ሰማንያ ስድስት ዓመት ሙሉ ሳገለግለው አንድም ቀን ክፉ አድርጎብኝ አያውቅም፤ እንዴት አድርጌ አዳኜንና ንጉሤን እሰድበዋለሁ?» በማለት መለሰላቸው።

የሮማ ገዥም መልሶ «በዕድሜህ አከብርሃለሁ፥ ቄሳር ጌታ መሆኑን የማይቀበሉት ክርስቲያኖች ይጥፉ ብትል ግን በነፃ ትለቀቃለህ» አለው።

ሽማግሌውም በዙሪያው ወደተሰበሰቡት የሮም አሕዛብ እያመለከተ «እነዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ የሚክዱት ይጥፉ!» ብሎ ጮኸ። ፖሊካርፕ በእሳት ተቃጥሎ መሥዋዕት በመሆን የጌታ ኢየሱስን ስም አከበረ።

## 3. ሕይወታችሁን መርምሩ (4፡15–18)

በመከራና በስደት እሳት ውስጥ ሕይወታችንንና አገልግሎታችንን የምንመረምርበትን ብርሃን እናገኛለን። በመከራ እግዚአብሔር አጥርቶ ያነጻናል። ፍርድ በዓለም ሁሉ ላይ የሚሆንበት ቀን ይመጣል (2ኛ ጴጥ. 3፡7–16)። የእግዚአብሔር ፍርድ የሚጀምረው ከቤተ ክርስቲያን፥ «ከእግዚአብሔር ቤት» ነው (1ኛ ጴጥ. 2፡5)። ይህ እውነት ታዛዥና ንጹሕ እንድንሆን ሊያነሣሣን ይገባል (ሕዝ. 9 ላይ የምናየው ሥዕላዊ መግለጫ ይህ እውነት በብሉይ ኪዳንም መጠቀሱን ያመለክታል)።

ሕይወታችንን ስንመረምር የምናነሣቸው በርካታ ጥያቄዎች አሉ።

*ሀ. ለምን መከራ እቀበላለሁ? (4፡15)* ሁሉም መከራ ከእግዚአብሔር አለመሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል። በአፍ ብቻ ክርስቲያን ነኝ የሚል አንድ ሰው ሕግ ጥሶና በሰው ነገር ጣልቃ ገብቶ መከራ መቀበል የሚገባው አይደለም እንዴ! ክርስቲያኖች መሆናችን ከሠራነው ጥፋት ከመቀጣት አያድነንም። ነፍስ ባናጠፋም እንኳን ቁጣችን በልባችን ውስጥ የመግደል ያህል ነው (ማቴ. 5፡21–26)። መስረቅም ሆነ በሰው ነገር ጣልቃ መግባት ኃጢአት አይደለም እንዴ? አብርሃም፥ ዳዊት፥ ጴጥሮስና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ «ታላላቅ ሰዎች» ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ መከራ ተቀብለዋል። እኛም ከእነዚህ ሰዎች የተለየን አይደለንም። መከራ የምንቀበለው ወንጀል ሠርተን ሳይሆን፥ ክርስቲያኖች በመሆናችን መሆኑን ማረጋገጥ ይገባናል።

*ለ. በክርስቶስ አፍርበታለሁ ወይስ አያከበርኩት ነው? (4፡16)* ይህ ክፍል ጴጥሮስ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስን መካዱን ያስታውሰናል (ሉቃስ 22፡54–62)። ብዙ ጊዜ *ሥራችን* አሳፋሪ ቢሆንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አላፈረብንም (ዕብ. 2፡11)። አብ አባታችን ተብሎ ሊጠራ አላፈረብንም (11፡16)። ክርስቶስ ስለ እኛ በመስቀል ላይ ውርደትን ታግሷል (12፡2)። ስለዚህ እኛም ስለ እርሱ ስንነቀፍ ልንታገስ እንጂ ልናፍርበት አይገባም። በማርቆስ 8፡38 ላይ ያለውን ማስጠንቀቂያ መመልከት አስፈላጊ ነው።

«አይፈር» የሚለው አሉታዊ፥ «እግዚአብሔርን ያመስግን» የሚለው ደግሞ አዎንታዊ ነው። እግዚአብሔርን ማመስገንና በእርሱም አለማፈር ሁለቱም ሚዛናዊ ለሆነ ምስክርነት ያስፈልጋሉ። ጳውሎስ በክርስቶስ ላለማፈር ስለ ቀረጠ ወደ ሮም ሄደ (ሮሜ 1፡16)፤ በዚያም መከራን ተቀበለ (ፊልጵ. 1፡20–21)፥ መሥዋዕትም ሆነ (2ኛ ጢሞ. 1፡12)።

*ሐ. የጠፉትን ለክርስቶስ ለመማረክ እሻለሁ? (4፡17–18)።* ጴጥሮስ የጠፉትን ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል «ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ» በማለት ነው። የእግዚአብሔር ልጆች እንደ እሳት ሊፈትን ከሚመጣው መከራ በጭንቅ ከዳኑ፥ ያላመኑ ኃጢአተኞች ይህ መከራ ሲመጣ እንዴት ይሆናሉ?

አማኝ መከራ ሲቀበል ክብርን ይለማመዳል። ወደፊት ታላቅ ክብር እንደሚጠብቀውም ስለሚያውቅ ደስ ይለዋል። ያንን መከራ የሚያመጣው ኃጢአተኛ ግን የእግዚአብሔርን የቁጣ ጽዋ እንዲሞላ ከማድረግ ውጭ የሚፈይደው የለም (ማቴ. 23፡29–33)። ለራሳችን ብቻ ሳይሆን፥ በዙሪያችን ላሉትና ለጠፉት ግድ ሊለን ይገባል። ጌታ ሲመለስ ኃጢአተኞች በፍርድ ከሚቀመጡበት እሳት ጋር ሲወዳደር

የእኛ ጊዜያዊ መከራ ምንም አይደለም (2ኛ ተሰ. 1፡7-10)። በምሳሌ 11፡31 ላይ «እነሆ፥ ጻድቅ በምድር ላይ ፍዳውን የሚቀበል ከሆነ፥ ይልቁንስ ኀጥእና ዓመፀኛ እንዴት ይሆናሉ!» ይላል።

«በጭንቅ የሚድን ከሆነ»፥ የሚለው ሐረግ የመከራውን አስቸጋሪነት ለማሳየት እንጂ እግዚአብሔር ለማዳን ይደክማል ለማለት አይደለም። እግዚአብሔር ሎጥን ሰዶም ከመጥፋቷ በፊት ሊያድነው ቢፈልግም ሎጥ ፈቃደኛ አልነበረም! ከመላእክት ጋር በመከራከር ወደ ኋላ ስለ ዘገየ እጁን ተጎትቶ ከከተማዋ መውጣት ነበረበት! ሎጥ «ከእሳት ዳነ»፤ ነገር ግን ያከማቸው ንብረት ሁሉ ተቃጠለበት (1ኛ ቆሮ. 3፡9-15ን ይመልከቱ)።

ለሚያሳድዱን በፍቅር የምንመሰክርበት አጋጣሚ ስደት ነው (ማቴ. 5፡10-12፥ 43-48 ይመልከቱ)። የፊልጵስዩሱን የወኅኒ ቤት ዘበኛ ወደ ክርስቶስ ያመጣው አስፈሪው የመሬት መንቀጥቀጥ ሳይሆን፥ ጳውሎስ ለእርሱ ያሳየው ርኅራኄ ነው። የመሬት መንቀጥቀጡማ በፍርሃት እራሱን እንዲገድል ሊያደርገው ነበር። ክርስቲያን እንደ መሆናችን መጠን ጉዳት ያደረሱብንን ሰዎች ለመበቀል ሳይሆን ልንጸልይላቸውና ወደ ጌታ ልናመጣቸው መፈለግ አለብን።

## 4. ራስህን ለእግዚአብሔር ስጥ (4፡19)

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራ ስንቀበል፥ ራሳችንን ለእርሱ መስጠት እንችላለን። «መስጠት» የሚለው ቃል «ጉዳት በማይደርስበት ቦታ ማስቀመጥን» ያመለክታል (2ኛ ጢሞ. 1፡12ን ይመልከቱ)። አደራ በባንክ ሥራ ውስጥ የምንጠቀምበት ቃል ነው። ሕይወትህን በእግዚአብሔር ባንክ ውስጥ በአደራ ስታስቀምጥ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ዘላለማዊ ትርፍን ትቀበላለህ።

ይህ ደግሞ ለእግዚአብሔር ምን ያህል ውድ መሆናችንን ያሳያል። እርሱ ፈጠረን፥ ከሞት አዳነን፥ በሕይወታችን ይኖራል፥ ይጠብቀናል። በጋዜጣ ላይ የብድርና የቁጠባ አገልግሎት ማኅበር ያወጣው ማስታወቂያ የድርጅቱን የማይዛባ የገንዘብ አቅምና በፌደራል ኢንሹራንስ ኮርፖሬሽን የሚደረግለትን ድጋፍ ያረጋግጣል። የገንዘብ ዋጋ በሚዋዥቅበት ጊዜ፥ እንደዚህ ዓይነቱ መተማመኛ ለአስቀማጩ በጣም አስፈላጊ ነው። አንተ ግን ሕይወትህን በእግዚአብሔር ዘንድ ስታስቀምጥ የሚያስፈራህ ምንም ነገር የለም። እርሱ ይጠብቅሃልና።

ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚደረግ ሳይሆን፥ ሁልጊዜ የሚደረግ ነው። ያለማቋረጥ ራስን መስጠት በእግዚአብሔር ቃል በመታነጽ ብዛት የሚመጣ ነው። ይህንን የምናደርገው በክፉ ፈንታ መልካምን በመመለስ፥ መከራ ቢያሠቃየንም

ራሳችንን ለሚጠብቀን አምላክ አደራ ስለሰጠነው ጌታ ይጠነቀቅልናል። የምንሰጠው እያንዳንዱን የሕይወታችንን ክፍልና እያንዳንዱን ጊዜያችንንም ጭምር ነው።

ጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ ይመለሳል ብለን ካመንን፥ ተስፋ ካደረግነው፥ መዝገባችንንና ክብርን በሰማይ ማከማቸት እንጀምራለን። ያልዳኑ ሰዎች የዛሬ ሕይወት የሚወሰነው ባለፈው ሕይወታቸው ነው። የክርስቲያኖች የዛሬ ሕይወት የሚወሰነው በወደፊት ሕይወታቸው ላይ ነው (ፊልጵ. 3፡12–21)። በአገልግሎታችን ራሳችንን ለእግዚአብሔር በመስጠት አትራፊ ሀብት ለወደፊቱ እናከማቻለን።

ለዚህ እውነት ጥሩ ሥዕላዊ መግለጫ የሚሆነን ነገር በኤርምያስ 32 ላይ እናገኛለን። ነቢዩ ኤርምያስ ለሕዝቡ አንድ ቀን ሁኔታዎች ተለውጠው ወደ ምድራቸው እንደሚመለሱ ይነግራቸው ነበር። ይህንን በሚነግራቸው ወቅት ግን፥ የባቢሎን ሠራዊት ኢየሩሳሌምን ለመያዝ ተቃርቦ ነበር። የኤርምያስ አጎት አናምኤል የቤተሰብ ርስት የሆነውንና በጠላት ወታደሮች የተያዘውን እርሻ እንዲገዛ ጥያቄ አቀረበለት። ነቢዩም ገንዘቡን በአፉ አጠገብ ማኖር ነበረበት። ይህ የእምነት መግለጫ ነበረ። በዚህ ሁኔታ ከአጎቱ ላይ መሬቱን ገዛው። ይህን በማድረጉ ለኢየሩሳሌም ሰዎች መሳቂያ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። እግዚአብሔር ግን እምነቱን አከበረለት። ምክንያቱም ኤርምያስ እንደሰበከው ቃል ኖሯልና።

ጴጥሮስ «ለታመነ ፈራጅ ወይም ለታመነ አዳኝ» ከማለት ይልቅ «ለታመነ ፈጣሪ» ለማለት የመረጠው ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስፈልጋቸውን ስለሚያሟላ ነው (ማቴ. 6፡24–34)። ለተሰደዱት ክርስቲያኖች ምግብና ልብስን የሚያዘጋጅላቸውና በመከራ ጊዜ የሚጠብቃቸው ፈጣሪያቸው ነው። የጥንት ክርስቲያኖች ሲሰደዱ በአንድነት ተሰብስበው ሰማይና ምድርን፥ ባሕርንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ወደ ፈጠረ አምላክ ይጸልያሉ (የሐዋ. ሥራ 4፡24)።

የሰማዩ አባታችን «የሰማይና የምድር ጌታ ነው» (ማቴ. 11፡25)። ከእንዲህ ዓይነት አባት ጋር ከሆንን መጨነቅ አያስፈልገንም። አባታችን ታማኝ ፈጣሪ ነው። ታማኝነቱም የማይለወጥ ፈጣሪ ነው።

እግዚአብሔር በዓለም ላይ ቁጣውን ከማፍሰሱ በፊት፥ እንደ እሳት የሚፈትነን መከራ በቤተ ክርስቲያን ላይ ይመጣል። መከራ ቤተ ክርስቲያንን አንድ የሚያደርግ፥ የሚያነጻና ለሚጠፉት ጠንካራ ምስክር የሚያደርጋት ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ መከራ የምንቀበል ከሆነ፥ ምንም የሚያስፈራን ነገር አይኖርም። ታማኙ አባታችንና ፈጣሪያችን በድል ያሻግረናል!

## 11

# መልካም እረኛ መሆን እንዴት ይቻላል?

(1ኛ ጴጥሮስ 5፡1-4)

በስደት ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ብቃት ያለው አመራር ያስፈልጋቸዋል። ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት የሚጀምር ከሆነ (1ኛ ጴጥ. 4፡17)፥ ቤቱ በሥርዓት ካልተመራ ይፈርሳል። ጴጥሮስ ይህንን የተለየ መልእክት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጻፈላቸው ሥራቸውን በታማኝነት እንዲሠሩ ለማበረታታት ነው። በችግር ወቅት የሚሸሹ መሪዎች ቅጥረኞች እንጂ እውነተኛ እረኞች አይደሉም (ዮሐ. 10፡12-14)።

በአዲስ ኪዳን ጉባዔዎች የሚዋቀሩት በሽማግሌዎችና በዲያቆናት አመራር ሥር ነው (1ኛ ጢሞ. 3)። «ሽማግሌ» እና «ኤጲስ ቆጶስ» አንድ ዓይነት ሥልጣንን ያመለክታል (የሐዋ. ሥራ 20፡17፥28)። ኤጲስ ቆጶስ «የበላይ ጠባቂ» ተብሎም ተተርጉሟል (1ኛ ጴጥ. 5፡2ን ያስተውሉ፤ በ2፡25 ላይ ይህ ስም የተመለከተው ለኢየሱስ ነው)። «ሽማግሌ» የሚያመለክተው የባለሥልጣኑን ብስለት ሲሆን፥ ኤጲስ ቆጶስ ደግሞ ኃላፊነትን ያመለክታል። መጋቢ ደግሞ እረኛ ማለት ሲሆን፥ የዚሁ ሥልጣን ሌላ ስም ነው (ኤፌ. 4፡11)። ሽማግሌዎች ለዚህ ሥልጣን ይሾማሉ። «ሹመት» ማለት እጅ አውጥቶ በመምረጥ መሾም ማለት ነው። እያንዳንዱ ጉባዔ ብቁ የሆኑትን ሰዎች የመሾም መብት አለው።

በመከራው ዘመን በጉባዔው ያሉ አማኞች ምሪትና ማበረታቻ ከሽማግሌዎቻቸው ይሻሉ። የጴጥሮስ ትኩረትም መሪዎች በዚህ ወቅት መደረግ የሚገባውን ሁሉ እንዲያደርጉ ነው። አንድ መጋቢ ውጤታማ ለመሆን ምን ዓይነት ግላዊ ብቃት ሊኖረው ይገባል?

### 1. ከክርስቶስ ጋር የጠበቀና በግል የመተዋወቅ ተሞክሮ (5፡1)

በዚህ ክፍል ጴጥሮስ ራሱን ያስተዋወቀው ሐዋርያ ነኝ ብሎ ሳይሆን እንደ ማንኛውም ሽማግሌ ነው። ይሁን እንጂ የክርስቶስ መከራ ምስክር መሆኑን (ማቴ. 26፡36) ሳይጠቅስ አላለፈም። 1ኛ ጴጥ. ምዕራፍ አምስትን ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር ብናነበው ጥሩ ነው። ቁጥር አንድ ወደ ጌቴሴማኒና ወደ ቀራኒዮ ይወስደናል። «ሊገለጥ ካለው ክብር» የሚለው ደግሞ በተራራ ላይ ጌታ ራሱን በለወጠ ጊዜ ጴጥሮስ ከጌታ ጋር መሆኑን ያስታውሰናል (2ኛ ጴጥ. 1፡15-18፤ ማቴ. 17፡1-5)። በቁጥር 2 ላይ በእረኛና በበጎቹ

ላይ በማተኮሩ ዮሐንስ 10ንና ጌታ ለጴጥሮስ የሰጠውን ኃላፊነት ያስታውሰናል (ዮሐ. 21፥15—17)።

በቁጥር 3 ላይ «ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ» የሚለው ክርስቶስ ስለ እውነተኛ ታላቅነትና ስለ ትሕትና ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማረውን ያስታውሰናል (ሉቃስ 22፥24—30)። በቁጥር አምስት ላይ «ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ» የሚለው ኢየሱስ በላይኛው ክፍል በነበሩበት ጊዜ፥ ማበሻ ጨርቅ ታጥቆ የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበትን ወቅት ያስታውሰናል (ዮሐ. 13፥1—17)።

በቁጥር 8 ላይ ስለ ሰይጣን የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ጌታችን በሉቃስ 22፥31 ጴጥሮስንና ሌሎቹን እንደ ስንዴ ሊያበጥራቸው እንደፈለገ ከሰጠው ማስጠንቀቂያ ጋር ይመሳሰላል። ጴጥሮስ ለማስጠንቀቂያው ትኩረት ባለመስጠቱ ጌታን ሦስት ጊዜ ካደው።

በቁጥር 10 ላይ «ፍጹማን ያደርጋችኋል» የሚለው በማቴዎስ 4፥21 ላይ «መረባቸውን ሲያበጁ» ከሚለው ጋር በትርጉም ይመሳሰላል። ይህም አራቱ ዓሣ አጥማጆች ወደ አገልግሎት የተጠሩበት ታሪክ ነው።

ጴጥሮስ ይህንን በመንፈስ ተመርቶ የጻፈው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ካለው የግል ኅብረት የተነሣ ነው። ከጌታ ጋር የጠበቀና የሚያድግ ኅብረት ማድረጉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚገባ ለማገልገል አስችሎታል።

የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገና በመንፈሳዊ ሕይወቱም የሚያድግ ሊሆን ይገባል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክረው «ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ» (1ኛ ጢሞ. 4፥15) ይለዋል። ሽማግሌዎች በቃል እውቀት፥ በሥራ፥ በአገልግሎት ወደ አዲስ ግዛትና ድንበር ውስጥ ለመግባት እድገታቸው ሊገለጥ ይገባል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወደ ፊት ካልሄዱ አባሎቻም እልፍ አይሉም።

የአንድ ቤተ ክርስቲያን አባላት በአንድ ኮንፍራንስ ላይ «መጋቢያችንን እንወደዋለን፥ ነገር ግን ከመዝሙረ ዳዊትና ከራእይ በስተቀር ሌላ መጽሐፍ የማያውቅ ይመስል ተመሳሳይ ነገር ስለተደጋገመብን ተሰላችተናል» አሉኝ። ያ ሰው መንፈሳዊ መሪ በመሆን ወደ አዲስ ነገር ራሱንና የሚመራውን ሕዝብ ይዞ መግባት ያስፈልገዋል።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከራን በማምጣት እንድታድግና አዲስ እውነት የምታገኝበትን መንገድ

እንድትፈልግ ያደርጋታል። ጴጥሮስ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገው በኢየሩሳሌም ስለ ክርስቶስ መከራን በመቀበሉ ነው። ጴጥሮስ ፍጹም አልነበረም። አንድ ጊዜ ጳውሎስ ገሥጾታል (ገላ. 2፡11–21)። ጴጥሮስ ግን ለክርስቶስ በመገዛት እግዚአብሔር ያቀደለትን ሁሉ ተማረ።

ዛሬ ለእረኞች ልሰጥ የምችለው ምክር «ከጌታ ጋር ያለህ ግንኙነት እድገት የሚያሳይ ይሁን፤ ከእርሱ የተማርከውን ደግሞ ለምትመራው ሕዝብ አካፍል። ይህንን ስታደርግ እነርሱም ከአንተ ጋር ያድጋሉ።» የሚል ነው።

## 2. የእግዚአብሔርን መንጋ በፍቅር መጠበቅ (5፡2–3)

መንጋ የሚለው ምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ ተጠቅሷል። [መዝ. (23) እና (100)፤ ኢሳ. 40፡11፤ ሉቃስ 15፡4–6፤ ዮሐ. 10፤ የሐዋ. ሥራ 20፡28፤ ዕብ. 13፡20–21፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡25፤ ራእ. 7፡17)። እኛ እንደሚጠፉ በጎች ተቅበዝብዘን ነበር፤ መልካሙ እረኛ ግን ወደ መሰማርያችን መልሶናል።

በጎች ንጹሕ እንስሳት ናቸው እንጂ እንደ ውሻና አሳማ አይደሉም (2ኛ ጴጥ. 2፡20–22)። በጎች በአንድነት እንደሚሰማሩ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብም ኅብረት ሊኖራቸው ይገባል። በጎች እረኞቻውን ካልተከተሉ በስተቀር ያለ እውቀት ተቅበዝብዘው ይጠፋሉ። በጎች ብዙ ጊዜ አቅም ስለሌላቸው የእረኞቻው ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል [መዝ. (23)፡4]።

በጎች ጠቃሚ በመሆናቸው የአይሁድ እረኞች በጎችን የሚያረቡት ለሥጋ ሳይሆን ለሱፍ፥ ለወተትና ጠቦቶችን ለማግኘት ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦችም ወደ ክርስቶስ በማምጣት ማርባት፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምንፈጽም ሕያው መሥዋዕትም መሆን ይገባናል (ሮሜ 12፡1–2)።

ጴጥሮስ የመንጋው ጠባቂ የሆኑትን ሽማግሌዎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ኃላፊነት ያሳስባቸዋል።

*ሀ. የእግዚአብሔርን መንጋ መግቡ (5፡2)።* እረኛ መንጋውን ሲጠብቅ የሚያደርጋቸው ብዙ ሥራዎች አሉ። ከሌቦችና ከአጥፊዎች በጎቹን ይጠብቃል። መጋቢም እንደዚሁ የእግዚአብሔርን መንጋ ከሚያጠፉት መከላከል አለበት (የሐዋ. ሥራ 20፡28–35)። አንዳንድ ጊዜ በጎች የእረኞቻቸውን ተግሣጽና ማስጠንቀቂያ ባይወዱትም እንኳን ይህ አገልግሎት ለራሳቸው ጥቅም እንዲሆን ተብሎ ነው።

ታማኝ እረኛ መንጋውን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፥ በለመለመ መስክ እያሰማራም ይመግባቸዋል። ከመንጋው በፊት እየወጣ ሊጎዳቸው የሚችል እባብ ቢሆን፥ መርዛም ዕፅዋት ቢሆኑ ወይም አደገኛ አውሬ መኖሩን ይሰልላል። የእግዚአብሔር ሕዝብ መጋቢም ሕዝቡን በቃሉ ማሰማርያ ላይ እንዲመገቡና እንዲያድጉ ያደርጋቸዋል።

በጎችን በተናጠል መንከባከብም አስፈላጊ ነው። ዛሬ አንዳንድ መጋቢዎች ለግለሰቦች ትኩረት አይሰጡም። ኢየሱስ ግን ለብዙ ሕዝብ ሰብኳል፥ ደግሞ ከኒቆዲሞስና ከሰማርያዋ ሴት ጋር በተናጠል በመሆን መንፈሳዊ ጥያቄዎቻቸውን መልሷል (ዮሐ. 3 ና 4)። ጳውሎስም በተሰሎንቄ ሰዎችን *በግል* ያገለግላቸውና ይወዳቸውም ነበር (1ኛ ተሰ. 2፡11)።

አንድ በግ የሚያምጽና የሚያስቸግር ከሆነ፥ እረኛው ሊገሥጸው ይገባል፤ ቢደክም በእጆቹ ይሸከመዋል፤ ቢቆስል ቁስሉን በዘይት ይቀባለታል፤ እሾህ ቢወጋው ከጸጉሩ መሃል ፈልፍሎ ይነቅልለታል። መልካም እረኛ በጎቹን በስማቸው ለይቶ በማወቅ እንደሚያስፈልጋቸው መጠን ይንከባከባቸዋል።

ታማኝ እረኛ መሆን ቀላል ነገር አይደለም! የማያልቅ ሥራ በመሆኑ በትክክል መሥራት አለበት፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ መለኮታዊ ኃይል መቀበል ያስፈልጋል። እረኝነትን አስቸጋሪ የሚያደርገው ሌላው ጉዳይ በጎቹ የእግዚአብሔር እንጂ የእርሱ አለመሆናቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ መጋቢዎች «በእኔ ቤተ ክርስቲያን» ሲሉ ይደመጣሉ፥ ለነገሩ ግን ቤተ ክርስቲያን በልጁ ደም የዋጀት የእግዚአብሔር ናት (የሐዋ. ሥራ 20፡28)። እኛ መጋቢዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ በጥንቃቄ መመገብ አለብን። ምክንያቱም እንጠየቅበታለንና። በጎቹም ቢሆኑ መንፈሳዊ መሪዎቻቸውን ምን ያህል እንደታዘዙ ይጠየቃሉ (ዕብ. 13፡17)። ስለዚህ እረኞችና በጎች ኃላፊነታቸውን መገንዘብ አለባቸው።

*ለ. መንጋውን ጎብኙት (5፡2)።* «ኤጲስ ቆጶስ» ማለት «ጠባቂ» ማለት ነው። እረኛ ግን በበጎች «መካከል» የሚኖር በግ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ መሪ በመሆኑ ከመንጋው «በላይ» ነው። በጎች ይህንን ልዩነት ካልተገነዘቡት ችግር ይፈጠርባቸዋል። አንዳንድ ሰዎች በበጎች መካከል የሚኖር በግ መሆኑን ተቀብለው የእረኝነት ሥልጣኑን ለመከተል ግን እምቢ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ መጋቢውን ከሰው ጋር እንደማይቀላቀል ቅዱስ በመቁጠር ከፍ ያለ ስፍራ ላይ ያስቀምጡታል።

አንድ ጥሩ መጋቢ ግን ሁለቱም ዓይነት ግንኙነት ያስፈልገዋል። በመንጋው መካከል በመሆን ፍላጎታቸውንና ችግራቸውን

ይረዳላቸዋል። ከላይ በመሆን ደግሞ ችግሮቻቸውን መፍታት እንዲችሉ በመምራት ይረዳቸዋል። *በመጋቢነትና በሰባኪነት አገልግሎት* መካከልም ቅራኔ ሊኖር አይገባም። ሰባኪው መጋቢ በመሆን ለሕዝቡ የሚያስፈልገውን ቃል ያቀርባል። መጋቢው ደግሞ ሰባኪ በመሆን ለችግሮቻቸው መፍትሔ የሚሆነውን ነገር ለማካፈል ሥልጣን አለው። መጋቢ በየሳምንቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ የሚያስተላልፍ የሃይማኖት አስተማሪ ሳይሆን፥ መንጋውን አውቆ በቃሉ በኩል የሚረዳ እረኛ ነው።

መንፈሳዊ መሪዎች ሊያስወግዱቸው የሚገቡትን አደገኛ ኃጢአቶች ጴጥሮስ ይጠቁማቸዋል። የመጀመሪያው *ስንፍና* ነው። ስንፍና ደግሞ ከጉድለት ሳይሆን ከፈቃድ ነው የሚመጣው። አገልግሎቱን እንደ ሥራ ማየት ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያከናውን አውቆ ከልቡ መሥራት አለበት (ኤፌ. 6፡6)። በዳላስ ለአምሳ ዓመታት የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበሩት ዶክተር ጆርጅ ደብልዩ. ትሩይት በሌላ የሥልጣን ቦታ ላይ ተቀምጠው እንዲሠሩ በተደጋጋሚ ይጠየቁ ነበር። እርሳቸውም ጥያቄውን በመቃወም፥ «የመጋቢነትን ልብ ፈልጌ አግኝቼዋለሁ» በማለት ይመልሱ ነበር። አንድ ሰው የመጋቢነት ልብ ካለው በጎቹን ይወዳል፤ ያገለግላቸዋልም። ይህንን የሚያደርገው ግን ወዶ እንጂ በግድ አይደለም።

ሰው በጎ ሕሊና ከሌለው አገልግሎት ለስንፍና የተመቸ ቦታ ነው። የቤተ ክርስቲያን አባላት መጋቢዎቻቸው ምን እንደሚሠሩ ስለማይጠይቁ የጓደኛውንም ስብከት የራሱ አስመስሎ ሊሰብክ ይችላል። አንድ መጋቢ ሳምንቱን ሙሉ ኳስ ሲጫወት ሰንብቶ ቅዳሜ ሲደርስ በካሴት የተዘጋጀ የሌላ ሰው ስብከት ያዳምጥና ለእሑድ ስብከት ይቀርባል። የእሑድን ስብከት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ቢወጣውም የእረኞች አለቃ የሆነውን ጌታ በሚገናኝበት ጊዜ ምን ይመልስ ይሆን?

ከስንፍና ቀጥሎ እረኞች መጠንቀቅ ያለባቸው *«መጥፎውን ረብ ከመመኘት»* ነው። ቤተ ክርስቲያን ለመጋቢዎች መክፈል ይገባታል (1ኛ ቆሮ. 9፡1፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡17–18)። ገንዘብ ማካበት ግን የመጋቢው የአገልግሎቱ ዓላማ መሆን የለበትም። ጳውሎስ ለሽማግሌነት በሰጠው መመዘኛ ላይ «ገንዘብን የማይወድ» (1ኛ ጢሞ. 3፡3)፥ እና ነውረኛ ረብ የማይወድ (ቲቶ 1፡7) በማለት አስቀምጦታል። መጋቢ ገንዘብን በመውደድ ለማከማቸት መኖር የለበትም።

በቤተሰብ ወይም በቤተ ክርስቲያን ከሚኖሩ አንዳንድ ሁኔታዎች የተነሣ አንዳንድ አገልጋዮች ተጨማሪ ሥራዎችን ለመሥራት ይገደዳሉ። ጳውሎስም ያገለግል የነበረው ድንኳን እየሰፋ ነበር። ይሁን

እንጂ የቤተ ክርስቲያኗ አባላት ሙሉ ጊዜያቸውን ለቃሉ አገልግሎት እንዲያውሉ አገልጋዮቻቸው የሚያስፈልጋቸውን በማሟላት ከተጨማሪ የውጭ ሥራ ሊያሳርፏአቸው ይገባል። መጋቢዎች ደግሞ ለአገልግሎታቸው እንቅፋት ከሚሆን የገንዘብ ስብሰባ ተግባር ሊቆጠቡና ሊጠነቀቁ ይገባል። «የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም» (2ኛ ጢሞ. 2፡4)።

‹በበጎ ፈቃድ› የሚለው ሐረግ ጳውሎስ በሮሜ 1፡5 ላይ «ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቻለሁ» ከሚለው ጋር ይመሳሰላል። ይህ ማለት በልብ መዘጋጀትና በጉጉት ለማገልገል ፈቃደኛ መሆን ነው። በእውነተኛ እረኛና በሞያተኛ መካከል ያለው ልዩነትም እውነተኛው እረኛ በጎቹን ስለሚወድ ሲያገለግል ሞያተኛው ግን የሚያገለግለው ስለተከፈለው ነው። በሐዋ. ሥራ 20፡17–38 ያለው ክፍል የእውነተኛ እረኛ ልብ ምን እንደሚመስል ያሳያል።

*ሐ. ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ (5፡3)።* በዚህ ክፍል *መምራትና በአምባገነንነት መግዛት* ተነጻጽረዋል። በእስራኤል ባህል በጎችን ከፊት ሆነህ ትመራቸዋለህ እንጂ ከኋላ ሆነህ አትነዳቸውም። ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጓት የሚያገለግሉ መሪዎችና የሚመሩ አገልጋዮች ናቸው። አንድ ክርስቲያን መሪ «ዛሬ ችግራችን ብዙ ታዋቂ ሰዎች ቢኖሩንም፥ በቂ አገልጋዮች ግን የሉንም» አለኝ።

አንድ እረኛ ለመንጋው ምሳሌ በመሆን በበጎች መካከል እየኖረና የበላይ ሆኖ እየመራ ያለችግር ሊያገለግል ይችላል። ሰዎች የሰበከውን የሚኖርን መሪ ሊከተሉት ፈቃደኛ ናቸው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን ያለባትን የገንዘብ ችግር ምክንያት ማንም ማወቅ አልቻለም ነበር። የቤተ ክርስቲያኗ መጋቢ ከለቀቀ በኋላ ግን ሌሎች ገንዘብ እንዲያበረክቱ ከመስበክ በስተቀር ምንም አበርክቶ እንደማያውቅ ተደረሰበት። እኛ ወደማንኖረው ሕይወት ሌሎችን መምራት አንችልም።

የእግዚአብሔር ሕዝቦች «የእግዚአብሔር ርስት» ናቸው። [ዘዳ. 32፡9፤ መዝ. (33)፡12]። ይህ ቃል መሬትን ለመከፋፈል በዕጣ መደልደል ማለት ነው (ዘኁ. 26፡55)። እያንዳንዱ ሽማግሌ የሚጠብቀው መንጋ አለው፤ በጎች ሁሉ ግን የበጎች እረኛ በሆነው በጌታ ኢየሱስ ሥር ያሉ መንጋ ናቸው። ጌታ ሠራተኞቹን በምርጦቹ ቦታ ላይ አስቀምጧቸዋል፥ ስለዚህ ባስቀመጠን ቦታ ሆነን እናገለግላለን። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስታገለግሉ የውድድር ስሜት አይኖርም። ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ገዥ

እንደሆነ ሊሰማው አይገባም። መጋቢዎች «የበላይ ጠባቂ» እንጂ ገዥዎች አይደሉም።

## 3. ክርስቶስን ብቻ ለማስደሰት መጠማት (5፡4)

ይህ የተስፋ መልእክት ስለሆነ የጌታ ኢየሱስን የመመለስ ተስፋ ደግሞ ያነሣዋል። የጌታ መመለስ በመከራ ጊዜ የሚያጽናና (1፡7–8)፥ ለታማኝ አገልግሎትም የሚያነሣሣ ነው። አንድ መጋቢ ራሱንም ወይም ሌሎችን ለማስደሰት የሚያገለግል ከሆነ፥ አገልግሎቱ አስቸጋሪና ተስፋ አስቆራጭ ይሆንበታል። አንድ እንግዳ የሆነ ሰው ከአምልኮ በኋላ ወደ እኔ መጣና «እነዚህን ሁሉ ማስደሰት በጣም አስቸጋሪ ነው» አለኝ። እኔም «እነርሱን ለማስደሰት አልሞክርም፤ ጌታን ደስ ለማሰኘት ግን እሞክራለሁ፥ እርሱ ደግሞ ስለሌላው ጉዳይ ይጠነቀቃል» በማለት መለስኩለት።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለበጎቹ የሞተ *መልካም* እረኛ (ዮሐ. 10፡11)፥ ለበጎቹ የኖረ *ትልቅ* እረኛ (ዕብ. 13፡20–21)፥ ስለ በጎቹ የሚገለጥ የእረኞች *አለቃ* (1ኛ ጴጥ. 5፡4) ነው። የእረኞች አለቃ እንደ መሆኑ መጠን፥ የሰውን አገልግሎት መዝኖ ተገቢውን ሽልማት ይሰጣል። ጌታ የእያንዳንዱን አገልግሎት ሲመዝን መጀመሪያ የነበሩት መጨረሻ ሊሆኑ ይችላሉ።

በአንድ የበጋ ወራት ስኮትላንድ ውስጥ በአንዎት አጠገብ በምትገኝ የቤተ ክርስቲያን ፍርስራሽ መካከል ቆሜ ነበር። ሕንጻው በአንድ ወቅት አንድ መቶ አምሳ ሰዎችን ያስተናግድ ነበር። በእርግጥ በዘመናዊ የሕንጻ መስፈርት አንጻር የተዋጣለት ሕንጻ ላይባል ይችላል። የዚህች ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆኑ ሳሙኤል ሩዘር ፎርድ፥ የጻፉት መልእክት ከመንፈሳዊ ጽሑፎች መሐል የሚፈረጅ ነበር። ዛሬ የቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ቢፈራርስም፥ አገልግሎታቸው ግን ቀጥሏል። የእረኞች አለቃ የዚህን ሰው የአገልግሎት ድካም፥ በስደት ያሳለፉትን የሥጋ ጉስቁልና ሁሉ አስበ ዋጋቸውን ከፍሏቸዋል።

በጥንት ዘመን ልዩ ልዩ «አክሊሎች» ነበሩ። ጴጥሮስ ከአበባ ጉንጉን ስለሚሠራውና ፈጥኖ ስለሚጠወልገው የሯጮች አክሊል አንሥቷል። የታማኝ መጋቢ አክሊል ግን የክብር አክሊል ነው፥ ለማይጠፋ *ርስትም* የሚሰጥ ሽልማት ነው።

ዛሬ ክርስቲያን ሠራተኞች የተለያዩ ዓይነት ሽልማቶችን ለማግኘት ይደክሙ ይሆናል። አንዳንዶቹ ግዛታቸውን ለማስፋፋት፥ ሌሎች ዝናን ለማትረፍ፥ ሌሎች ደግሞ እድገት ለማግኘት ይተጋሉ። ይህ ሁሉ ግን አንድ ቀን ይጠወልጋል። እኛ የምንናፍቀው ግን «መልካም

አድርጎሃል» የሚለውን የጌታችንን ቃልና የማይጠፋውን የክብር አክሊል ነው። አክሊሉን በእግሮቹ ሥር ማኖር ምን ያህል የሚያስደስት ነገር ነው (ራእ. 4፡10)። ያደረግነው ሁሉ በጸጋውና በኃይሉ እንደሆነ እውቅና እንሰጣለን (1ኛ ቆሮ. 15፡10፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡11)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ፊት ለፊት ስናየው የራሳችንን ክብር አንፈልገውም።

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ከአመራር የተነሣ ሊለማ ወይም ሊጠፋ ይችላል። ኅብረቱ ትልቅም ይሁን ትንሽ መሪዎቹ ክርስቲያኖች የሆኑ፥ ከጌታ ጋር የጠበቀ ኅብረት ያላቸው፥ ለመንጋው የሚጠነቀቁና ኢየሱስ ክርስቶስን ደስ ለማሰኘት የቆረጡ ሊሆኑ ይገባል።

በማገልገል እንመራለን፤ በመከራ እናገለግላለን።

ኢየሱስ ያደረገው እንዲሁ ስለሆነ ይህ መንገድ እርሱ በእውነት የሚከብርበት ብቸኛ መንገድ ነው።

# 12

# ከጸጋ ወደ ክብር

(1ኛ ጴጥሮስ 5፡5–11)

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበርኩ። ጦርነቱ ከሰሜናዊ ኢንዲያና ከተማችን በርቀት ላይ የሚካሄድ ይመስል ነበር። በዚያን ጊዜ በእኛ ከተማ ከየጎረቤቱ የተውጣጣ ሲቪል የመከላከያ ኃይል እየተደራጀ ነበር። አባቴ የአንዱ ቡድን ካፒቴን ስለነበር የልምምዱን ፊልም ለማየትና ተናጋሪዎቹን ለማዳመጥ ከእርሱ ጋር እሄድ ነበር። የቱንም ያህል ፊልም ብንመለከትም ጎረቤቶቻችን በቦምብ ይመታሉ ብለን አስበን አናውቅም። ፍልስፍናችን «እዚህ ሊሆን አይችልም» የሚል ነበር።

ጴጥሮስ ግን እንደ እሳት የሚፈትነው መከራ ሊሆን መቅረቡን ያውቅ ስለነበር መላዋ ቤተ ክርስቲያን እንድትዘጋጅ ይፈልጋል። በደብዳቤው መዝጊያ ላይ ቤተ ክርስቲያን በመከራ ውስጥ እግዚአብሔርን ማክበር እንድትችል ሦስት ጠቃሚ ምክሮችን ለግሷታል።

## 1. ትሑታን ሁኑ (5፡5–7)

ጴጥሮስ ቅዱሳን ለመንግሥት ባለሥልጣናት፥ ባሪያዎች ለጌቶቻቸው፥ ሚስቶች ደግሞ ለባሎቻቸው እንዲገዙ መክሯቸዋል (2፡13–17፤ 2፡18–25፥ 3፡1–7)። አሁን ደግሞ ሁሉም አማኞች ለእግዚአብሔርና አንዱ ለሌላው እንዲገዛ ያዛቸዋል።

ጎበዞች ለሽማግሌዎች ይገዙ። ሽማግሌዎች በዕድሜያቸው ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ብስለታቸውም ሊከበሩ ይገባቸዋል። በክርስትና ውስጥ ብዙ ጊዜ መቆየት በእርግጥ በሳል ለሆነ ሕይወት ዋስትና አይሰጥም። ይህ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቆዩ አባሎች ቤተ ክርስቲያንን ይምሩ ወጣቶችንም አይስሟቸው ለማለት የታሰበ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በትውልድ መካከል የሚካሄድ ጦርነት አለ። ሽማግሌዎች ለውጥንና አዲስ ነገርን ሲቃወሙ፥ ወጣቶች ደግሞ ሽማግሌዎችን ይቃወማሉ።

ለዚህ ሁለት መፍትሔ አለው። 1) ሁሉም አማኝ ወጣትም ሆነ ሽማግሌ አንዱ ለሌላው ሊገዛ ይገባል። 2) ሁሉም ለእግዚአብሔር ሊገዙ ይገባል። «ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ።» የሚለው ለዚህ ችግር መልስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ

እንዳገለገለ እኛም አንዱ ሌላውን ለማገልገል እንደዚህ ዓይነት ዝቅ ብሎ የማገልገል አሳብ ሊኖረን ይገባል። እውነተኛ ትሕትና በፊልጵስዩስ 2፡1–11 ላይ ተገልጾአል። ትሕትና ማለት ስለ ራሳችን ምስኪንነትና የበታችነት ማሰብ ሳይሆን፥ በጭራሽ ስለ ራሳችን አለማሰብ ነው!

በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር ካልተገዛን አንዳችን ለሌላው ልንገዛ አንችልም። ጴጥሮስ በምሳሌ 3፡34 እና በያዕቆብ 4፡6 ላይ የተጠቀሰውን ክፍል እርሱም ጠቅሶታል። ለሌላው ለመገዛት ጸጋ ያስፈልጋል፤ ራሳችንን በፊቱ ስናዋርድ ደግሞ እግዚአብሔር ያንን ጸጋ ይሰጠናል።

እግዚአብሔር የትዕቢትን ኃጢአት ስለሚጠላ ትዕቢተኞችን ይቃወማል (ምሳ. 6፡16–17፤ 8፡13)። ሉሲፈርን ከሥልጣኑ አውርዶ ሰይጣን ያደረገው ትዕቢት ነው (ኢሳ. 14፡12–15)። እግዚአብሔርን ለመምሰል የመፈለግ ትዕቢት ሔዋንን የተከለከለውን ፍሬ ለመብላት አነሣሣት። «መመካት» የዓለማዊነት ምልክት ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡16)። የትዕቢት መከላከያ መድኃኒት የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን ጸጋ ለመቀበል ደግሞ ራሳችንን ለእርሱ ማስገዛት አለብን።

መገዛት የእምነት እርምጃ ነው። ሕይወታችንን እንዲመራና ዓላማውን በጊዜው በሕይወታችን እንዲፈጽም በእግዚአብሔር እንታመናለን። ለሌሎች ስንገዛ ሰዎች መጠቀሚያ ሊያደርጉን ይችላሉ። እግዚአብሔርን የምንታመንና አንዳችን ለሌላው የምንገዛ ከሆነ ግን ይህ አይሆንብንም። እራሱን ለእግዚአብሔር በእውነት የሚያስገዛና ክርስቲያን ወገኖችን ማገልገል የሚወድ ሰው ማንንም መጠቀሚያ ለማድረግ አይፈልግም። የእኛን ሕይወት የሚመራው «ኃይለኛው የእግዚአብሔር እጅ» የሌሎችን ሕይወት ይመራል።

«በጊዜው» የሚለው ቃል ቁልፍ ቃል ነው። እግዚአብሔር ያልተዘጋጀን ሰው አያከብርም። መጀመሪያ መስቀልና መከራ ሲቀድም አክሊልና ክብር ደግሞ ይከተላል። ሙሴ አይሁዶችን ከግብፅ ለማውጣት ከመላኩ በፊት በእግዚአብሔር እጅ ሥር አርባ ዓመት ቆይቷል። ዮሴፍ ወደ ዙፋን ከመውጣቱ በፊት ለአሥራ ሦስት ዓመታት ያህል በእግዚአብሔር እጅ ሥር ቆይቷል። ትዕቢታችን ከሚገለጽበት መንገድ አንዱ አለመታገሣችን ነው። መከራ የሚመጣበት አንዱ ምክንያት ደግሞ ትዕግሥትን ለማስተማር ነው (ያዕቆብ 1፡1–6)። ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ጌታ ሲናገር ወደአዳመጠው ክፍል ያመለክታል፥

«ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱንም የሚያዋርድ ከፍ ይላል።» (ሉቃስ 14፡11)።

ራሳችንን የማዋረድ ጥቅሙ ስለሚያስጨንቀን ነገር እግዚአብሔር ያስብልናል። በ1ኛ ጴጥሮስ 5፡5–6 ላይ ያለውን ሁኔታ ካላሟላን በቁጥር 7 ላይ ያለውን አስደናቂ ተስፋ መቀበል አንችልም። ሁኔታዎች አስቸጋሪ ሲሆኑብን መጨነቅና መጠበብ ይቀለናል። ይህ ግን በረከትን ያስቀርብናል፤ ደካማ ምስክሮችም ያደርገናል። በመከራ ውስጥ ድል ማድረግና እግዚአብሔርን ማክበር ከፈለግን የውስጥ ሰላም ያስፈልገናል። ዶክተር ጆርጅ ሞሪሰን «እግዚአብሔር ልጆቹ እንዲጨነቁ የማይፈልገው ግድ የለሾች እንዲሆኑ አይደለም።» ብለዋል።

በ1ኛ ጴጥሮስ 5፡7 *መሠረት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ* ያለፈውን የአሁኑንና የወደፊቱን ጭንቀታችንን ሁሉ ለጌታ መስጠት አለብን። እኛ እንችለዋለን የምንለውን ለራሳችን ብናስቀር ትንሽ ቆይቶ ትልቅ ችግር ይሆንብናል። በየጊዜው አዲስ ሸክም ሲመጣብን በእምነት ለጌታ አሳልፈን መስጠታችንን እናስታውስ።

እግዚአብሔር የራሱ ለሆኑት እንደሚጠነቀቅ የሚያውቅ ሰው ቢኖር ጴጥሮስ ነው። ወንጌልን ስናነብ ለጴጥሮስ የተደረጉለትን ተአምራት እናያለን። ኢየሱስ አማቱን ፈወሰለት፤ ብዙ አሳዎችን እንዲያጠምድ ረዳው፥ የቤተ መቅደስ ግብር ይከፍል ዘንድ አስቻለው፥ በውኃ ላይ አራመደው፥ የቆረጠውን የማልኮስን ጆሮ ቀጠለለት፥ ከወኅኒ አወጣው (የሚከተሉትን ጥቅሶች በቅደም ተከተል ተመልከቱ፥ ማር. 1፡29–31፤ ሉቃስ 5፡1–11፤ ማቴ. 17፡24–27፤ 14፡22–23፤ ሉቃስ 22፡50–51፤ ዮሐ. 18፡10–11፤ የሐዋ. ሥራ 12)።

ጭንቀታችንን ሁሉ በእርሱ ላይ ስንጥል፥ እግዚአብሔር ፍቅሩንና ጥበቃውን የሚያሳየን እንዴት ነው? በእኛ ፋንታ የሚያከናውናቸው አራት አስደናቂ አገልግሎቶች አሉ። (1) ከችግር ከመሸሽ ይልቅ ፊት ለፊት የምንጋጠምበትን ድፍረት ይሰጠናል (ኢሳ. 41፡10)። (2) ሁኔታዎችን የምንረዳበትን ጥበብ ይሰጠናል (ያዕቆብ 1፡5)። (3) ማድረግ የሚገባንን እንድናደርግ ጉልበት ይሰጠናል (ፊልጵ. 4፡13)። (4) የቀረውን ነገር እርሱ ሊጨርሰው እንደሚችል የምንታመንበትን እምነት ይሰጠናል [መዝ. (37)፡5]።

አንዳንድ ሰዎች ሸክማቸውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰጥተው ሁሉንም እርሱ እንዲሠራላቸው ይሻሉ! ምላሹ ሲመጣ ተዘጋጅተን ለመጠበቅ እንድንችል እግዚአብሔር በእኛ በኩል ለእኛ እንዲሠራ

እንፍቀድለት። «ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፥ እርሱም ይደግፍሃል» [መዝ. (55)፡22]።

2. ንቁ (5፡8—9)

ጠላት ስላለን እንጩነቃለን። ሰይጣን እንደ እባብ ያስታል (2ኛ ቆሮ. 11፡3)፤ እንደ አንበሳ ይውጣል። ሰይጣን ማለት «ጠላት፥ ተቃዋሚ» ማለት ነው፥ «ዲያብሎስ» ማለት ደግሞ «ከሳሽ» ማለት ነው። የዚህ መልእክት ተቀባዮች ተሰድበዋል (1ኛ ጴጥ. 4፡4፥ 14)። አሁን ደግሞ እንደ እሳት በሚፈትነው መከራ ከአንበሳ ጋር ይፋጠጣሉ። ጴጥሮስ በጠላቶቻቸው ላይ ድል የሚያቀዳጃቸውን በርካታ ጠቃሚ ምክር ይለግሳቸዋል።

*ሀ. አደገኛ መሆኑን አውቃችሁ አክብሩት።* የመካኒክነት ችሎታ ስለሌለኝ ይህንን የሚሠሩ ሰዎችን አከብራለሁ። የቤተ ክርስቲያንን ሕንጻ ሲሠራ የኤሌክትሪክ ሠራተኛው የተወሳሰቡ የኤሌክትሪክ መቆጣጠሪያዎችን ሲገጥም ኃይል ካላቸው የኤሌክትሪክ መስመሮች ጋር እንዴት በጸጥታ ሥራዎችን እንደሚሠራ ሳስበው ይገርመኛል» በማለት ለአንዱ ሠራተኛ ነገርኩት። እርሱም ፈገግ ብሎ «መጀመሪያ ማድረግ ያለብህ ኤሌክትሪኩን ማክበር ነው። ከዚያ መሥራት ትችላለህ።» አለኝ።

ሰይጣን አደገኛ ጠላት ነው። አነስተኛ ግምት ሰጥተን ስንጠብቀው ሊነክሰን የሚችል እባብ ነው። እርሱ አጥፊ ነው (ራእይ 12፡11)፥ ከሳሽም ነው (ራእይ 12፡9—11፤ ዘካ. 3፡1—5)። ሰይጣን ትልቅ ኃይልና እውቀት፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመዋጋት የሚረዱት የክፋት ሠራዊት አሉት (ኤፌ. 6፡10)። አስፈሪና ትልቅ ጠላት ስለሆነ፥ መቀለድም ሆነ ችሎታውን አቅልለን ማየት የለብንም። ከሰይጣን ጋር በሚኖረን ቅራኔና ግጭት በጭምትነት እንደ ባለ አእምሮ ማሰብ አለብን።

እንደ ባለ አእምሮ ስናስብ ለሁሉ ነገር ሰይጣንን የጥፋት ተጠያቂ አናደርገውም። አንዳንድ ሰዎች ከእያንዳንዱ ቁጥቋጦ በስተኋላ ሰይጣንን ያዩታል። ራሳቸውን ሲያማቸው፥ የመኪና ጎማቸው ሲተነፍስ፥ የቤት ኪራይ ሲጨምር ለሁሉ ነገር ሰይጣንን ተጠያቂ ያደርጉታል። ሰይጣን በሽታና ሥቃይ ሊያመጣ መቻሉ እውነት ቢሆንም (ሉቃስ 13፡16፤ ኢዮብ)፥ «የራስ ምታትና የጀርባ ህመም መናፍስት» እያልን ለማስወጣት ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን የለንም። አንድ ወይዘሮ ከሩቅ ቦታ ደወለችልኝና ሰይጣን 7 1/2 ኢንች አድርጎ እንደ ከረከማት ነገረችኝ። ለሰይጣን ተንኮልና ኃይል እውቅና ብሰጥም፥ ስለ ሰይጣን የሚኖረን እውቀትና መረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንጂ ከልምምዳችን መመንጨት እንደሌለበት ይሰማኛል።

*ለ. ሰይጣን እጅግ በጣም አስመሳይ መሆኑን ለይታችሁ ዕወቁ (2ኛ ቆሮ. 11፡13–15፤ ዮሐ. 8፡44)።* ሰይጣን ተንኮለኛ ጠላት ስለሆነ ንቅተንና ተግተን መጠበቅ አለብን። የሰይጣን አሠራር እግዚአብሔር የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር መቃወም ነው። በእንክርዳዱ ምሳሌ ላይ፥ እግዚአብሔር እውነተኛ ክርስቲያኖችን ሲተክል፥ ሰይጣን ግን የሚያሳስተውን ይዘራል (ማቴ. 13፡24–30፥ 36–43)። የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ባይኖሩ ኖሮ ሰይጣን ምንኛ ባሳተን ነበር (1ኛ ዮሐ. 18፡27)። የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ባወቅን ቁጥር የሰይጣንን ሥራ ለመለየት ንቁ መንፈስ ይኖረናል። መንፈስን ፈትነን እውነትን ከሐሰት ለይተን ማወቅ መቻል አለብን (4፡1–6)።

*ሐ. ተቃወሙት። ይህ ማለት በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመጽናት ፈቀቅ ላለማለት መቃወም ማለት ነው (ኤፌ. 6፡10–13)። ካልጸናን በስተቀር መቃወም አንችልም። የጦር ዕቃችን የእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት ነው። መከላከያችን ደግሞ እግዚአብሔር ያዘጋጀው የጦር ዕቃ ነው (ኤፌ. 6፡17–18)። ሰይጣንን «በእምነት» እንቃወመዋለን፥ እምነታችን ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ ነው። ዳዊት በእግዚአብሔር ታምኖ ጎልያድን እንደ ተቃወመ፥ እኛም በአሸናፊው በጌታ ኢየሱስ ስም ታምነን ሰይጣንን እንቃወማለን።*

እዚህ ላይ ያለው የማስጠንቀቂያ ቃል ከሰይጣንም ሆነ ከጭፍሮቹ በፍጹም አትወያይ የሚል ነው። ሔዋን ይህንን ስሕተት በመሥራቷ የደረሰውን አሳዛኝ ነገር ሁላችንም እናውቃለን። ሰይጣንን በራሳችሁ መንገድ ሳይሆን፥ ኢየሱስ በተቃወመበት መንገድ ተቃወሙት (ማቴ. 4፡1–11)። በእንደዚህ ዓይነት ጦርነት ውስጥ የምታልፉት እናንተ ብቻ እንደሆናችሁ አድርጋችሁ በፍጹም ማሰብ የለባችሁም። «በዓለም ያሉ ወንድሞቻችሁ» ይህንን መከራ እንደሚቀበሉ አውቃችሁ ለእነርሱ መጸለይና እርስ በርሳችሁ መበረታታት አስባችሁ። የእኛ ድል ሌሎችን፥ የሌሎች ድል ደግሞ እኛን ይረዳናል።

ጴጥሮስ እነዚህን ሦስት መመሪያዎች ተከትሎ ቢሆን ኖሮ፥ በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ አይተኛም ነበረ፤ የሊቀ ካህኑን አገልጋይ ጆሮ አይቆርጥም፥ ኢየሱስንም አይክድም ነበር። ጌታችን ለሰጠው ማስጠንቀቂያ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ ይከራከር ነበር! ሰይጣን «መንቃትና መጸለይ» እንደማያስፈልገውና ሰይፉን መጠቀም እንደሚችል እየነገረው ማንነቱን በትዕቢት ሲያንሳፍፍ፥ ጴጥሮስ የተቃዋሚው የሰይጣን አሳብ መሆኑን መለየት አልቻለም ነበር። ጴጥሮስ ጌታን ሰምቶና ጠላትን ተቃውሞ ቢሆን ኖሮ፥ ከእነዚህ ሁሉ ውድቀቶች ባመለጠ ነበር።

ጴጥሮስም ሆነ ያዕቆብ ለተሳካ መንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጡን መመሪያ «ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል» (ያዕቆብ 4፡7) የሚል ነው። ሰይጣንን ለመቃወም ከመነሣታችን በፊት ለእግዚአብሔር መገዛት አለብን። ጴጥሮስ እግዚአብሔርን ሊቃወም ለሰይጣን ተገዝቶ አረፈ!

### 3. ተስፋ አድርጉ (5፡9–11)

ጴጥሮስ አሳቡን ሲደመድም አንባቢዎቹን እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚያውቅና ሁሉም ነገር በቁጥጥሩ ሥር እንደሆነ ያሳስባቸዋል። እንደ እሳት ሊፈትን የሚመጣው ፈተና አስቸጋሪ ቢሆንም፥ ክርስቲያን ግን ሁልጊዜ ተስፋ አለው። ጴጥሮስ ለዚህ ተስፋ ምክንያት የሚሆኑትን ነገሮች ዘርዝሯል።

*ሀ. የእግዚአብሔር ጸጋ አለን።* መዳናችን በጸጋው ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡10)። እኛ እርሱን ከመጥራታችን በፊት እርሱ ጠርቶናል (1፡2)። ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሰናል (2፡3)፥ ስለዚህ ለእኛ የሚያቅደው ነገር መልካም ስለሚሆን አንፈራም። የእግዚአብሔር ጸጋ ልዩ ልዩ በመሆኑ ለተለያዩ የሕይወት ጥያቄዎቻችን መልስ አለው (4፡10)፤ ለእርሱ ስንገዛ ጸጋን ይሰጠናል፤ በሚያስፈልገን ሁሉ ሊረዳን የሚያስችል ጸጋ አለው (ዕብ. 4፡16)። ጸጋን አብዝቶ ስለሚሰጥ (ያዕቆብ 4፡6)፥ በዚህ ጸጋ ጸንተን ልንቆም ይገባል (1ኛ ጴጥ. 5፡12፤ ሮሜ 5፡2ን ይመልከቱ)።

*ለ. ወደ ክብር እንደምንገባ እናውቃለን።* ሁለተኛ የተወለድነውና የተጠራነው ለማያልፍና ዘለዓለማዊ ለሆነ ርስት ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡4)። በእግዚአብሔር ጸጋ የተጀመረ ነገር ወደ እግዚአብሔር ክብር ያመራል [መዝ. (84)፡11]። በመከራችን ጊዜ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ከተደገፍን መከራችን ወደ ክብር ያመራል (1ኛ ጴጥ. 4፡13–16)። መንገዱ አስቸጋሪ ቢሆንም፥ ወደ ክብር ያመራል፤ የሚፈለገውም ደግሞ ይኸው ነው።

*ሐ. የአሁኑ መከራችን ለጊዜው ነው።* የሚገጥሙን የተለያዩ መከራዎች «ለተወሰነ ጊዜ» ብቻ ነው (1ኛ ጴጥ. 1፡6)፥ ክብሩ ግን ለዘለዓለም ነው። ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡17–18 ላይ «ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው።» ብሏል።

*መ. መከራችን ፍጹማን እንደሚያደርገን እናውቃለን።* በግሪክ ቋንቋ «ፍጹማን» የሚለው ቃል ትርጉም «መሙላት፥ ማስተካከል፥

አንድ ላይ ማያያዝ» ማለት ነው። በማቴዎስ 4፡21 ላይ «መረቦቻቸውን ሲያበጁ» የሚለው ቃል የተተረጎመው ከተመሳሳይ ቃል ነው። እግዚአብሔር ልጆቹን ለሕይወታቸውና ለአገልግሎታቸው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች የሚሞላበት መሣሪያ አለው፤ መከራ አንዱ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሌላው መሣሪያ ነው (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17)፤ እንዲሁም የክርስቲያኖችን ኅብረትና አገልግሎትን ይጠቀምበታል (ኤፌ. 4፡11-16)። በሰማያዊ ስፍራ ያለው አዳኛችን ልጆቹ የእርሱን ሥራና ፈቃዱን እንዲያሟሉ ፍጹማን ያደርጋቸዋል (ዕብ. 13፡20-21)።

ጴጥሮስ እግዚአብሔር እንዲኖረን የሚፈልገውን ሦስት ዓይነት ባሕርይ ለመግለጽ ሦስት ቃላትን ተጠቅሟል።

*«ያጸናችኋል»* ማለት እንዳትነቃነቁ አድርጎ ያቆማችኋል ማለት ነው። ክርስቲያኖች ለኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው አቋም መወላወል የለባቸውም። ልባችን ሊጸና ይገባል (1ኛ ተሰ. 3፡13፤ ያዕቆብ 5፡8)። ጸንቶ የቆመ ክርስቲያን በስደትም ሆነ በስሕተት ትምህርት አይናወጥም (3፡17)።

*«ያበረታችኋል»* ማለት የተሰጠን የእግዚአብሔር ብርታት በሕይወታችን ውስጥ የሚገጥመንን ነገር የምንወጣበት አቅማችን ነው። የምንቆምበት አቅም ባይኖረን ኖሮ ተደላድላችሁ ቁሙ የሚለው ምን ይጠቅመን ነበር?

*«ይመሠርታችኋል»*። የዚህ ቃል ትርጉም «መሠረት መጣል» ማለት ነው። ይህንን ቃል የዕብራውያን ጸሐፊ ምዕራፍ 1፡10 ላይ ተጠቅሞበታል። በዓለት ላይ የተመሠረተው ቤት ማዕበሉን ተቋቋመ (ማቴ. 7፡24-27)። እግዚአብሔር ያስታጠቃቸው ክርስቲያኖች «ተደላድለውና ተመሥርተው በሃይማኖት ጸንተው ይኖራሉ» (ቆላ. 1፡23)። በትምህርት ነፋስም እየተፍገመገሙ ወዲህና ወዲያ አይገፉም (ኤፌ. 4፡14)።

የማያምን ሰው በመከራ ውስጥ ሲያልፍ ተስፋ ይቆርጣል። ለሚያምን ግን መከራ ተስፋውን ያጎላለታል፤ በመከራችንም እንደሰታለን። ምንያቱም «መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን፥ ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ» እናውቃለን (ሮሜ 5፡3-4)። ለሚታመኑበት እግዚአብሔር ተስፋን ይሰጣል፤ ፍጹማንም ያደርጋቸዋል። ከዚህም የተነሣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብሩን ይወስዳል።

ቁጥር 12 እና 13ን በመግቢያው ላይ አይተናል።

ጳውሎስ መልእክቶቹን የሚደመድመው በጸጋ ቡራኬ ነው (2ኛ ተሰ. 3፡17–18)። ጴጥሮስ ደግሞ መልእክቱን በሰላም ሰላምታ ጀምሮ በሰላም ቡራኬ ዘግቷል (1ኛ ጴጥ. 1፡2)፥ መልእክቱ ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው «በእግዚአብሔር ሰላም» የተሞላ ነው። የሚፈትን መከራ እንደሚመጣ የሚያስታውቀውን መልእክት በዚህ ሁኔታ ጀምሮ መጨረሱ እጅግ የሚያስደንቅ ነው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ አራት ጊዜ «በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ እንዲለዋወጡ» የሚናገሩ ምክሮችን እናገኛለን (ሮሜ 16፡16፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡20፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡12፤ እና 1ኛ ተሰሎ. 5፡26)። ጴጥሮስ «የፍቅር አሳሳም» ይለዋል። ልብ በሉ ወንዶች ወንዶችን፥ ሴቶች ደግሞ ሴቶችን ይስሙ ነበር። የዚህ ዓይነቱ የሰላምታ ልውውጥ በዚያን ዘመን የስንብት ሰላምታ ነበር። ክርስቲያን ባሪያዎችና ጌታዎች «በኢየሱስ ክርስቶስ» የፍቅር ሰላምታ ይለዋወጡ ነበር። እንዴት ድንቅ ነው!

ጴጥሮስ በጻፈልን በዚህ መልእክት ያለንበት ሁኔታ የቱንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን፥ በእግዚአብሔር እንድንታመን ያበረታታናል። በታሪክ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ መከራዎች ውስጥ አልፋለች፤ ይሁን እንጂ፥ ሰይጣን ሊያጠፋት አልቻለም። ዛሬም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን በመከራ ውስጥ ስለምታልፍ ራሳችንን ልናዘጋጅ ይገባል።

ምንም ይምጣ ምን፥ ጴጥሮስ እያንዳንዳችንን ተስፋ አድርጉ! ክብር የሚገለጥበት ጊዜ ቀርቧል ነው የሚለን።

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ

## ክርስቶስ ባለበት ሁሉ ተስፋ አለ

(1ኛ ጴጥሮስ 1፡1፤ 5፡12–14)

1. ስለ ክርስትና እምነትህ መከራ የተቀበልከው መቼ ነው?
2. 1ኛ ጴጥሮስ 1፡1 እና 5፡12–14ን አንብብ። ስለ መጽሐፉ ጸሐፊ የምታውቀው ነገር ምንድን ነው? (ዮሐንስ 1፡35–42፤ 21፡15–17፤ የሐዋ. ሥራ 4፡13 እና ገላትያ 2፡10ን በተጨማሪ ይመልከቱ)።
3. ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈው ለማን ነው?
4. አማኞች ዛሬ «መጻተኞች» የሆኑት እንዴት ነው?
5. ጴጥሮስ ይህን መልእክት ሲጽፍ የት ነበረ? ስለነበረበት ቦታ የሚታወቅ ነገር አለ?
6. ጴጥሮስ ይህንን መልእክት ለምን ጻፈው?
7. ጴጥሮስ በዚህ መልእክት ፈተናን 15 ጊዜ ጠቅሶታል። ይህ መልእክት የተጻፈላቸው ሰዎች በመከራ ውስጥ ለምን እንዳለፉ መልእክቱን በማንበብ መልስ።
8. የእግዚአብሔር ጸጋ ከመከራ ጋር የተያያዘው እንዴት ነው?
9. በዓለም ዙሪያ ያሉ አማኞች ዛሬ የሚሰደዱት እንዴት ነው?
10. የእግዚአብሔርን ጸጋ አሁን እያለፍክበት ካለው መከራ ጋር የምታዛምደው እንዴት ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ሁለት

# የክብር መንገድ!

(1ኛ ጴጥሮስ 1፥2–12)

1. በታሪክ ውስጥ ብዙ ክብርን የተጎናጸፉ ሰዎችንና አሁን ግን የተዘነጉትን ሥም ዘርዝሩ።
2. 1ኛ ጴጥሮስ 2፥1–12ን አንብብ። ጴጥሮስ መንፈሳዊ ልደታችንን የገለጸው እንዴት ነው?
3. እያንዳንዱ የሥላሴ አካል በደኅንነታችን ያለው ድርሻ ምንድን ነው?
4. እግዚአብሔር ለምን አዳነን?
5. ጴጥሮስ ስለምናልፍባቸው መከራዎች ምን አስተማረን?
6. መከራ እንደማያም መካድና ማስመሰሉ መከራችንን የባሰ የሚያደርገው እንዴት ነው?
7. በመከራ ውስጥ ስናልፍ እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚቆጣጠር ማወቃችን እንዴት ሊያጽናናን ይችላል?
8. የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከዛሬው ደኅንነታችን ጋር የሚዛመዱት እንዴት ነው?
9. ጴጥሮስ ለመከራ ምን ዓይነት ምላሽ እንድንሰጥ ነው የሚነግረን?
10. ይህ ምላሽ በመከራ ውስጥ ክብርን እንዴት ያመጣል?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ሦስት

## *በቆሸሸ ዓለም ውስጥ በንጽሕና መኖር*

(1ኛ ጴጥሮስ 1፡13–21)

1. «ቅዱስ ሰው» የሚለውን ስትሰማ ወደ ሕሊናህ የሚመጣው ምንድን ነው?
2. 1ኛ ጴጥሮስ 1፡13–21ን ቅዱስ ማን እንደሆነ መልስ ለመስጠት አንብብ። ቅዱስ መሆን ማለት ለአንተ ምን ትርጉም አለው?
3. በቅድስና ለመኖር ጴጥሮስ የሰጣቸው አነሣሾች ምን ምን ናቸው?
4. ቅድስና የተሞላበትን ኑሮ ለመኖር፥ እነዚህን ማነቃቂያዎች እንዴት ወደ ሕይወት መመሪያነት እንለውጣቸዋለን?
5. «የልቡናችንን ወገብ የምንታጠቀው» እንዴት ነው?
6. ጴጥሮስ የገለጠው ፍርድ በቅድስና ለመኖር ምን አስተዋጽኦ አለው?
7. ደኅንነታችንንና እግዚአብሔር እኛን ለማዳን የከፈለውን ዋጋ ማሰቡ ምን ጥቅም አለው?
8. በዚህ ሳምንት የበለጠ በቅድስና ለመኖር ምን ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ ትችላለህ?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አራት

## የክርስቲያኖች አንድነት

(1ኛ ጴጥሮስ 1፡22–2፡10)

1. አብዛኛውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላት እርስ በርስ የማይስማሙት ለምንድን ነው?
2. 1ኛ ጴጥሮስ 1፡22–2፡10ን አንብብ። ጴጥሮስ በዚህ ምንባብ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ አንድነት ለማጠናከር የገለጸው እንዴት ነው?
3. ሰዎች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሚሆኑት እንዴት ነው?
4. አማኞች በጋራ ያላቸው ነገር ምንድን ነው?
5. መንፈስ ቅዱስን መመልከት ሊከፋፍለን የሚተጋውን ሥጋ እንድንቋቋመው የሚረዳን እንዴት ነው?
6. አማኞች ከሕይወታቸው ሊያስወግዱቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድን ናቸው? ለምን?
7. አማኞች በእግዚአብሔር ቃል የሚያድጉባቸው ደረጃዎች ምንድን ናቸው?
8. የአማኝ ካሕናት ዕድል ፈንታና ኃላፊነት ምንድን ናቸው?
9. ለእግዚአብሔር ልናቀርባቸው የምንችላቸው መሥዋዕት ምንድን ናቸው?
10. ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት የማታደርግ ከሆነ፥ በዚህ ሳምንት ከእነርሱ ጋር ኅብረት ለመፍጠር ምን ለማድረግ አስበሃል?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አምስት

# የሚያይህ አለ!

(1ኛ ጴጥሮስ 2፥11–25)

1. መታዘዝ የሚለውን ቃል ስትሰማ፥ ምን ታስባለህ? ለምን?
2. 1ኛ ጴጥሮስ 2፥11–25ን አንብብ። ለባለሥልጣናት ለመታዘዝና በክርስትና ሕይወታችንም ታዛዦች እንድንሆን ጴጥሮስ ያነሣሣን በምንድን ነው? ለምን?
3. ማንነታችንን ማወቅ በእኛ ላይ ባለሥልጣናት ለሆኑት ለመገዛት የሚረዳን እንዴት ነው?
4. ቁጥር 13ን ለመታዘዝ ዳንኤልን ሦስቱ ጓደኞቹ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት እንዴት ነው?
5. ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት ለመንግሥት ታዛዥ መሆን እንደሚቻልና አንዳንድ ሕጎችን ደግሞ አለመታዘዝ እንደሚቻል የገለጹት እንዴት ነው?
6. በአሳባቸው ከማንስማማው የአገራችን ፕሬዚዳንቶችና ባለሥልጣናት አንጻር ያለብን ኃላፊነት ምንድን ነው?
7. ከክርስቲያን ባሪያዎች ተምረን ዛሬ በመሥሪያ ቤታችን ካለው ሁኔታ ጋር ልናዛምዳቸው የምንችላቸው መመሪያዎች ምን ምን ናቸው?
8. ለባለሥልጣናት በመገዛት አንጻር ጌታችን ክርስቶስ ምሳሌ የሚሆነን እንዴት ነው?
9. ከምን ዓይነት ባለሥልጣናት ጋር ነው ከፍተኛ ችግር የሚገጥምህ?
10. ራስህን ከጴጥሮስ መመሪያዎች ጋር በዚህ ሳምንት ማዛመድ የምትችለው እንዴት ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ስድስት

## *ጋብቻ ወይስ ፍቺ?*

(1ኛ ጴጥሮስ 3፥1–7)

1. ለተሳካ ትዳር መኖር መሠረታዊዎቹ ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. አንደኛው የትዳር ወገን የማያምን ቢሆን፥ ያመነው ምን ማድረግ እንዳለበት ጴጥሮስ ተናግሯል። 1ኛ ጴጥሮስ 3፥1–7ን አንብብ። ሴቶች በትዳር ውስጥ ምን ሚና መጫወት እንዳለባቸው ነው ጴጥሮስ የተናገረው?
3. ጴጥሮስ፥ ባሏ ያልዳነ ቢሆንም ሚስት ለባሏ መገዛት ያለባት በምን ምክንያት ነው ይላል?
4. ያልዳነ ባል ላላት ሴት መታዘዝ ምን ዕድል ይሰጣታል?
5. ያልዳነን ባል ወደ ጌታ የሚያመጣው የጌታ ተስፋ ምንድን ነው የሚያደርገው? ለምን?
6. በሴቶች ዘንድ ፋሽን አልባ ልብስ መልበስ እንደ ትልቅ ጥፋትና ጅልነት የሚታየው ለምንድን ነው?
7. መታዘዝ እንደ ጌጥ የሚሆነው እንዴት ነው?
8. «በፍርሃት ሳትናወጥ» አንድ ሚስት ባሏን ለጌታ ለመማረክ ስትተጋ በራሷ ልትተማመን የምትችለው እንዴት ነው?
9. ክርስቲያን ባል ለሚስቱ የሚጠነቀቀው እንዴት ነው?
10. የቁጥር 7 የመጨረሻ ክፍል ጥቅሙ ምንድን ነው?
11. በዚህ ሳምንት ለትዳር አጋርህ የተሻለ ሆነህ መቅረብ የምትችለው እንዴት ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ሰባት

## *ለተሻለው መዘጋጀት!*

(1ኛ ጴጥሮስ 3፡8–17)

1. 1ኛ ጴጥሮስ 3፡8–17ን አንብብ። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ የእግዚአብሔርን ታላቅ በረከት የምንለማመደው እንዴት ነው?
2. የዚህ ዓይነቱን ፍቅር በየዕለቱ በሕይወታችን የምናሳየው እንዴት ነው?
3. በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አንድነትን አንድ ዓይነት በመሆን ለመተካት በመጣር የተሳሳቱት በምን ምክንያት ነው?
4. ርኅራኄ ማድረግን መማር በሕይወታችን ስደት ከመነሣቱ በፊት ራሳችንን የሚያዘጋጀን ለምንድን ነው?
5. እግዚአብሔርን የሚቃወም አገዛዝ ባለበት አገር፥ ለሚኖሩ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችንን ርኅራኄ ልናሳይ የምንችለው እንዴት ነው?
6. ራስን ዝቅ ማድረግ የመከባበር መሠረት የሚሆነው እንዴት ነው?
7. ጠላቶቻችንን ስንቃወም ልንኖርባቸው የሚገቡን ሦስት ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?
8. ከፍርድ ይልቅ በምሕረት ላይ ተደግፈን የምንኖረው እንዴት ነው?
9. ፍርሃትን በተመለከተ፥ ጴጥሮስ የሰጠን መንፈሳዊ መመሪያዎች ምን ምን ናቸው?
10. በመከራና በተቃውሞ ወቅት በጎ ሕሊና አንድን አማኝ የሚረዳው እንዴት ነው?
11. በዚህ ምንባብ መሠረት፥ መጥፎ ጊዜ ሲያጋጥምህ ምን አመለካከትና እርምጃ ነው መለወጥ ያለብህ?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ስምንት

## ከኖኅ እንማር

(1ኛ ጴጥሮስ 3፡18–22)

1. አማኞችን በአንድነት የሚያስተሳስሯቸው የእምነት መሠረቶች ምን ምን ናቸው?
2. 1ኛ ጴጥሮስ 3፡18–22ን አንብብ። ከክርስቶስ ሞት ስለ አገልግሎቱ ምን እንማራለን? ለነፍሳት ከሰበከውስ? ከትንሣኤውስ? ከዕርገቱስ?
3. ክርስቶስ የሰበከላቸው ነፍሳት እነማን ነበሩ?
4. ኖኅ በቅዱሳት መጻሕፍት ትልቅ ስፍራ የተሰጠው ለምንድን ነው?
5. በጴጥሮስ መልእክት ተቀባዮችና በኖኅ አገልግሎት መካከል ያለው ኅብረት ምንድን ነው?
6. የጥፋት ውኃ ከክርስቲያን ጥምቀት ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?
7. ጴጥሮስ በዚህ ምንባብ እንደ ክርስቲያን ለመኖር የሰጣቸው ዋና ዋና ትምህርቶች ምን ምን ናቸው?
8. ይህንን ምንባብ በመጠቀም ላልዳነ ሰው ደኅንነትን እንዴት ታስረዳለህ?
9. ይህንን የደኅንነት ገለጻ በዚህ ሳምንት የምትተገብረው እንዴት ነው?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## *በቀሪው ዘመናችን*

(1ኛ ጴጥሮስ 4፡1–11)

1. በየቀኑ በሥራ ቦታህ ምን ያህል ጊዜ ታሳልፋለህ? ከቤተሰብ ጋርስ? ከእግዚአብሔር ጋርስ? በመኝታስ? በመዝናናትስ? ቴሌቪዥን በማየትና በመሳሰሉትስ?
2. 1ኛ ጴጥሮስ 4፡1–11ን አንብብ። ጊዜያችንን ልንጠቀምበት እንችላለን?
3. በኃጢአት ላይ አቋም መውሰድ የምንችለው እንዴት ነው?
4. የማያምኑትን የምንታገሳቸው ለምንድን ነው?
5. ለክርስቶስ ምጽአት የሚኖረን ምላሽ ምን መሆን አለበት? ለምን?
6. የጌታን ምጽአት በተመለከተ፥ ጴጥሮስ አማኞች ሊኖራቸው የሚገባ ማዕከላዊ አቋም ነው ብሎ ያዘዘው ምንድን ነው?
7. እነዚህን ትእዛዛት ዛሬ በተግባር እንዴት ልናውላቸው እንችላለን?
8. ስለ ጌታ ምጽአት የሚያወራውን ትምህርትና ለምጽአቱ የሚኖረንን ዝግጅት የምናስታርቀው እንዴት ነው?
9. ለቀሪ ሕይወት ዘመናችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ምን ያደርግልናል?
10. የዚህ ሳምንት ጊዜህ ለዘላለም ዋጋ የሚኖረው እንዲሆን ምን ለማድረግ አስበሃል?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ 10

## የማንጠሪያው እቶን እውነታዎች

(1ኛ ጴጥሮስ 4፡12–19)

1. በምኝነትህ ምክንያት የተሰደድከው መቼ ነበር? እንደ እግዚአብሔር ቃል በመኖርህ?
2. 1ኛ ጴጥሮስ 4፡12–19ን አንብብ። በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ሰዎች ስለ እምነታቸው የተሠቃዩት በምን መንገድ ነበር?
3. አማኞች ስለ መከራ ሊኖራቸው የሚገባው አቋም ምንድን ነው? ለምን?
4. በመከራ መሃል አማኞችን የሚያስደስታቸው ምንድን ነው?
5. የዛሬው መከራችን ውጤቱ ምን ይሆናል?
6. ክርስቲያን የሚለው ስም በታሪክ ውስጥ ትርጉሙ እንዴት ተለወጠ?
7. ስለ እምነታችን መከራ ስንቀበል ራሳችንን መጠየቅ ያለብን ነገር ምንድን ነው?
8. በመከራ ውስጥ ሳለን፥ ራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን የምንሰጠው እንዴት ነው?
9. ወደ አገራችን መከራ ቢመጣ ምን ትላለህ?
10. ከዚህ ክፍል ምን ዓይነት ተግባራዊ ትምህርቶችን አገኘህ?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

## መልካም እረኛ መሆን እንዴት ይቻላል?

(1ኛ ጴጥሮስ 5፡1–4)

1. የቤተ ክርስቲያንን ሁኔታ በጥቅሉ እንዴት ትገልጠዋለህ?
2. ቤተ ክርስቲያን አሁን ላለችበት ሁኔታ ትልቅ ሚና የተጫወቱት ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. 1ኛ ጴጥሮስ 5፡1–4ን አንብብ። በምንባቡ ውስጥ ጴጥሮስ ማንነቱን የገለጠው እንዴት ነው? ለምን?
4. አንድን መጋቢ ስኬታማ የሚያደርገው ምንድን ነው?
5. የመጋቢ ሚና ምንድን ነው?
6. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመግለጽ ጴጥሮስ በግን በምሳሌነት የተጠቀመው ለምንድን ነው?
7. መጋቢዎች/ሽማግሌዎች በመንጋው ላይ «ገዥዎች» የሚሆኑት እንዴት ነው?
8. መጋቢ ልቡ መነሣሣት የሚገባው በምንድን ነው? ለምን?
9. መንጋው ለእረኞች ምላሽ መስጠት ያለበት እንዴት ነው?
10. መጋቢያችሁን ግልጽና ተግባራዊ በሆነ መልኩ እንዴት ልትረዳው ትችላለህ?

# የጥናት ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## *ከጸጋ ወደ ክብር!*

**(1ኛ ጴጥሮስ 5፡5–11)**

1. ስደትን በራስህ አገላለጽ አስቀምጥ ብትባል፥ ምን ትለዋለህ?
2. 1ኛ ጴጥሮስ 5፡5–11ን አንብብ። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች መሐል ጴጥሮስ እግዚአብሔርን ለማክበር የሰጣቸው ምክሮች ምንና ምን ናቸው?
3. በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ያለውን የትውልድ ክፍተት ለመሙላት አማኞች መውሰድ ያለባቸው ርምጃዎች ምን ምን ናቸው?
4. እግዚአብሔር የትዕቢትን ኃጢአት እንደ አጥፊ ኃጢአት የያየው ለምንድን ነው?
5. መታዘዝ የእምነት እርምጃ የሚሆነው እንዴት ነው?
6. በቁጥር 7 ላይ ያለውን ተስፋ ለማግኘት የሚቀድመው ነገር ምንድን ነው?
7. እግዚአብሔር ለጴጥሮስ እንደሚጠነቀቅለት ያረጋገጠበት የጴጥሮስ ልምምድ ምንድን ነው?
8. ሥጋት የሚፈጥሩብን የጠላታችን ዘዴዎች ምንድን ናቸው?
9. በሰይጣን ላይ ባለድል እንደሆንን የምናውቀው እንዴት ነው?
10. ለእግዚአብሔር አሳልፈህ በመስጠት ፋንታ ራስህ የተሸከምካቸው ጭንቀቶች ምን ምን ናቸው?
11. በዚህ መልእክት የተማርከውን ተግባራዊ ለማድረግ በዚህ ሳምንት ምን ዓይነት የመታዘዝ እርምጃ ትወስዳለህ?